ሬታና ቤተሰቡ
ቤተ መጻሕፍት

# አናቅጸ ሲኦል

በብርሃኑ ጎበና

ሚያዝያ 1997 ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

4.3 የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን........................... 75
4.4 ሞርሞኒዝም............................................. 78
4.5 አድቬንቲስት............................................. 85
4.6 ባሃኡላህ................................................. 87
4.7 የይሖዋ ምስክሮች........................................ 89
♦ የይሖዋ ምስክሮች እምነትና አስተምህሮ.. 91
4.8 «ኢየሱስ ብቻ»........................................... 95
4.9 ፕሮቴስታንት በታላቅ ቀውስ........................ 96
♦ ብልጽግናን ማዕከል ያደረገው
የእምነት እንቅስቃሴ........................... 97
♦ የካሪዝማቲክ እንቅስቃሴ....................... 100

## ምዕራፍ አምስት

5.1 የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ............................ 106
♦ የመጨረሻው ነጥብ............................... 107
♦ ዳግም ልደት........................................ 109
♦ ሞኒዝም............................................... 111
♦ ግላዊነት............................................... 112

## ምዕራፍ ስድስት

6.1 የሰይጣን አምላኪዎች.................................. 116



## መግቢያ

«በጠበበው ደጅ ግቡ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ መንገዱም ትልቅ ነውና ወደ እርሱም የሚገቡት ብዙዎች ናቸው:: ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ መንገዱም የቀጠነ ነውና የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው::» ማቴ. ፯÷፲፫ና፲፬::

እንደ ጌታችን ቃል ሰፊውን መንገድ መርጠው በእርሱ ላይ እየተጓዙ ያሉ በቁጥር ብዙዎች ናቸው:: የጥፋት ትምህርት እንደ ሰደድ እሳት እየተያያዘ ዓለማችንን በማካለል ላይ ነው:: በተለይ ባለንበት በዚህ ዘመን ክህደቱ ከመጽናቱ የተነሣ በትምህርተ መለኮት መለያየት ብቻ ሳይሆን ፈጣሪን ከነመኖሩ መካድ፣ የክፋት አበጋዝ፣ የጽድቅ ተፃራሪ የሆነው ሰይጣንን፣ ያለ ጠባዩ ያለግብሩ የመልካም ነገሮች መገለጫ አድርገው በአምልኮ መንበር ላይ ማስቀመጥና እርሱንም ማምለክ በገሀድ እየተከሰተ ነው::

«አናቅጸ ሲኦል» በሚል ስያሜ ያዘጋጀሁት ይህ መጽሐፍ ወደ ዘላለማዊ ሕይወት የሚያስገባውን ጠባብ በር ዙሪያውን አጥረው ወደ እርሱ የሚገቡትን ግራ በማጋባትና በማሳሳት ላይ ያሉትን ወደ ሲኦል የሚያመሩ የጥፋት በሮችን ማንነት የሚገልጽ ነው::

ክርስትና በምድረ ፍልስጤም ከተወለደበት ጊዜ አንስቶ በቤተ ክርስቲያን ላይ የኑፋቄ ጦራቸውን ሰብቀው ዲያብሎስን ጋሻ አድርገው የዘመቱ መናፍቃን እያሌ ናቸው:: በዚህ መጽሐፍ ላይ በቤተ ክርስቲያን ጉዞ የተነሱና የተከሰቱ ኑፋቄዎችን ሁሉ ለመተረክ አልተፈለገም፣ የማይቻልም ነውና:: ጸሑ ግን ዋና ዋናዎቹን ለመዳሰስ ተሞክሯል:: በተለይ በቅርብ ጊዜዎቹ ላይ አተኩሬያለሁ:: ከክርስትና አስተምህሮ ፍጹም የራቀው «የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ» ሰፋ ባለ መልኩ የተገለጸ ሲሆን በቤተ ክርስቲያን ስም ስለተቋቋመው «ሰይጣኒዝም» በስፋት ታትቷል::

*በማስተዋል እንድታነቡ ምክሬ ነው::*

www.ethiopianorthodox.org

ተንሠራፍቶ ነበር:: ቅድመ ልደተ ክርስቶስ የዓለም ገጽታ በግርድፉ ከላይ የተገለጸውን ይመስል ነበር::

## 1.2 የብርሃን መገለጥ

*«ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር» ዮሐ. ፩÷፱*

ባስነገረው ትንቢት፣ ባስቆጠረው ሱባዔ መሠረት ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ከምሥራቅ ኆኅት ድንግል ማርያም ተወልዶ ብርሃኑን በዓለም ዘረጋ:: የሰው ልጅን ውጦት የነበረው ጽልመት ተወገደ:: በጨለማና በሞት ጥላ የነበረ ሁሉ ብርሃን አየ:: የኃጢአት መጋረጃ ዓይኑን ጋርዶት የአምላኩ ገጽታ ጠፍቶት የነበረው የሰው ልጅ መጋረጃው ስለተገለጠ ገጹ አምላኩን አየ:: «እነሆ በኤፍራታ ሰማነው በዱር ውስጥም አገኘነው»[1] ተብሎ በነብዩ አንደበት እንደተነገረው:: በቤተልሔም ዋሻ በጨርቅ ተጠቅሎ በግርግም ውስጥ ተኛ:: አድግና ላህም በመካከላቸው የተገኘውን የይሁዳ አንበሳ ሳያስደነብራቸው ይልቁንም በደስታ ተውጠው ትንፋሻቸውን ገበሩለት:: ቤተልሔም ሰላማዊ መድረክ ሆና ለዘመናት ተጠልተው የነበሩ ታረቁባት፣ ተለያይተው የነበሩ ምድራውያንና ሰማያውያን የአንድነት ማኅበር መስርተው ዘመሩባት::[2]

ይህ ሁሉ ሲሆን የመሲሁን መምጣት በጽኑ ጉጉት ይጠባበቁ የነበሩት አይሁድ መሲህ ትንቢተ ነብያትን መሠረት አድርጎ በመካከላቸው መገኘቱን አላወቁም ነበር:: የእነርሱ አጠባበቅና የእርሱ አመጣጥ ለየቅል ሆኖ:: እነርሱ የሰማዩን ደመና፣ የተራሮችን ጫፍ ሲያማትሩ እርሱ ደግሞ ጨርሶ ባልጠበቁትና ባልገመቱት ሁኔታ በቤተልሔም ዋሻ ተገኘ:: ለነገሩማ «አንቺ ቤተልሔም የይሁዳ ምድር ከይሁዳ ገዥዎች ከቶ አታንሺም ሕዝቤን እሥራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወጣልና» የሚል ትንቢት ተጽፎላቸው ነበር:: ዳሩ ግን ነብዩ ሚኪያስን ማን

1. መዝ. ፻፴፩÷፮
2. ሉቃ. ፪÷፳::



www.ethiopianorthodox.org



ከቁብ ይቁጠረው::[1]

ለአይሁድ ግልጽ ያልሆነው የመሲህ መምጣት ለይሁዳ ንጉሥ ለሄሮድስ «የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው?» ብለው በኮከብ ተመርተው ከምሥራቅ በመጡት ሰብዓ ሰገል አማካኝነት ግልጥ ሆኖ ስለነበር:: ከጸፎች ባገኘው ትንቢታዊ መረጃ መሠረት እነርሱን ወደ ቤተልሔም መርቶ እርሱ ግን ጨቤውን መሳል ጀምሮ ነበር:: ወደ ሄሮድስ እንዳይመለሱ በሕልም የተረዱት ሰብዓ ሰገል በሌላ መንገድ ወደመጡበት መመለሳቸውን የሰማ ሄሮድስ ሁለት ዓመትና ከዚያ በታች ያሉትን የቤተልሔም ሕፃናትን አሳረደ:- የተወለደውን የአይሁድ ንጉሥ አገኛለሁ ብሎ:: ጌታ ግን ከእናቱ ጋር ወደ ምድረ ግብጽ ተሰዶ ነበር::

ከሦስት ዓመት ከመንፈቅ የስደት ዓመታት በኋላ[2] ኑሮውን በገሊላ አውራጃ በናዝሬት ከተማ አደረገ:: ግዕዘ ሕፃናትን ሳያፋልስ ቀስ በቀስ አደገ:: አሳዳጊው ዮሴፍን በአናጢነት ሙያ፣ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምን ውኃ በመቅዳት፣ እንጨት በመስበር እየተራዳ፤ በሰንበትና በበዓላት ቀናት ደግሞ በምኩራብ እየተገኘ ከረቢዎች ጋር የመጻሕፍትን ምሥጢር ሲጠይቅ ከእነርሱ ጋር ሲወያይ ያሳልፍ ነበር::

በበሰለ ንግግሩ፣ በርቱዕ አንደበቱ በመልኩ ማማር ያዩት ሁሉ ይደነቁበት ነበር:: ከእርጋታው የተነሣ የተቀጠቀጠ መቃ አይሰበርበትም፤ ከአነጋገሩ ልዝብነት የተነሣ የሚጤስ የጧፍ ኩስታሪ አይጠፋበትም ነበር::[3]

ጌታ ተወልዶ ሠላሳ ዘመን ሲሞላው መንገድ ጠራጊው ዮሐንስ ከምድረ በዳ ስለ እርሱ እየመሰከረ መጣ «ከእኔ በፊት የነበረው ከእኔ በኋላ ይመጣል:: እኔ የጫማውን ክር ልፈታ የማይገባኝ ነኝ:: እኔ በውኃ አጠምቃችኋለሁ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ በእሳት ያጠምቃችኋል»[4] እያለ መሲሁን በዙሪያው ላሉና በትጋትና በንቃት ይጠባበቁ ለነበሩት አይሁድ አስተዋወቀ::

1. ትን. ሚኪያስ ፭÷፪
2. ራእይ ፲፪÷፮፣፲፬
3. መዝ. ፵፭÷፪፣ ኢሳ. ፵፪÷፪-፬
4. ማቴ. ፫÷፲፩-፲፪

ክንዱ የሚያደቅ፣ ዓይኑ እሳት የሚተፋ በጦር ኃይል የተደራጀ ጦረኛ መሲህ ሲጠባበቁ የነበሩት ፈሪሳውያን ለእግሩ ጫማ፣ ለእጁ በትር የሌለው፣ በዚህ ላይ በእነርሱ ግምት የጠራቢ ልጅ መሲሃችን ነው ብለው ለመቀበል ህሊናቸው አልፈቀደውም:: ለዓይናቸው አልሞላምና::

የማስተማር ሥራውን በጀመረበት ጊዜ ግብዝነታቸውን እንዲሁም የሕጉና የሥርዓቱ ጠበቆች ነን እያሉ በአደባባይ ሲለፍፉ በሥራቸው ግን ሕግ አፍራሾች ሥርዓት ጣሾች ሆነው መገኘታቸውን በግልጽ ይነቅፉ ስለነበር ለዓይናቸው አስጠላቸው:: ትምህርቱም ጆሮአቸውን የሚያሳክክ ሆነባቸው:: በተለይም ታላቁን ቤተ መቅደስ መነገጃ መሸቀጫ የውንብድና ሥራ የሚሠራበት ስላደረጉት:: ቤተ መቅደሱን ከወንበዴዎች ነፃ ለማድረግ በወሰደው የማጽዳት እርምጃ እጅጉን ከመበሳጨታቸው የተነሣ ተደፈርን ሥልጣናችንን ተቀማን በሚል በጌታ ላይ ጥርሳቸውን አፏጨበት::

እርሱ ግን ርኁባነ ሥጋን በምግብ፣ ርኁባነ ነፍስን በትምህርት እያጠገበ:: ድውያነ ሥጋን በተአምራት ድውያነ ነፍስን በትምህርት እየፈወሰ ወደ ፍኖተ መስቀል የሚያደርገውን ጉዞ ቀጠለ:: ማኅበረ አይሁድ በዓለም ላይ የተገለጠውን ብርሃን ለማጥፋት ሤራ መኀንኀን ጀመሩ:: በአነጋገሩ ግድፈት፣ በሥራው ሕፀጽ ቢፈልጉበት ሊያገኙ ስላልቻሉ:: የሐሰት ምስክሮች አዘጋጁ «ሕግ አፍርሷል ሥርዓት ጥሷል» ብለው በሀሰት የሚመሰክሩበት::

በዕለተ ዓርብ በአንደበቱ ክፋት በሥራው ጉድለት የሌለበትን ምክንያተ ኃጢአት ያልተገኘበትን ጌታ በጲላጦስ አደባባይ ከሰው አቆሙት:: «በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል በመንግሥቱም ላይ ድፍረት ተናግሯል» ሲሉ በጲላጦስ ፊት ከሰሱት ሮማዊው ጲላጦስ ሲመረምረው አይሁድ እንደሚሉት ሆኖ ስላላገኘው በነፃ ሊያሰናብተው ፈልጎ ነበር:: ዳሩ ግን አይሁድ «ይህ ገሊላዊ ሕዝቡ ለሕግ እንዳይታዘዝ ይሰብካል» ሲሉ ክሳቸውን ወደ ፖለቲካ አቅጣጫ ቀይረው ቀረቡ:: ጲላጦስም «ገሊላዊ ከሆነ እኔ ዘንድ ሳይሆን በገሊላዊ ገዥ በሄሮድስ አንቲፓስ ዘንድ መመርመር አለበት» ብሎ ወደ ሄሮድስ ዘንድ ላከው:: ሄሮድስም መርምሮ ወደ ጲላጦስ መለሰው:: ጲላጦስም የሞት ፍርድ ፈረደበት::





በነበረው ልምድ አገረ ገዥ በሚያከብረውና በሚደግሰው በዓል አገሪቱ ውስጥ ከሚገኙት የሞት ፍርድ ከተፈረደባቸው እስረኞች አንዱ ይማር ነበር:: በርባን የተባለ በሮማ መንግሥት ላይ ዓመፅ ያስነሣ ሰው ተይዞ የሞት ፍርድ ተፈርዶበት ነበር:: ጲላጦስም ክርስቶስንና በርባንን አቅርቦ በፍርድ ሸንጎ የነበሩትን የካህናት ለቆችን ከእነዚህ ከሁለቱ ማንኛቸውን ልፈታላተሁ ትወዳላችሁ? ብሎ ጠየቀ:: አይሁድም በቅንዓት መንፈስ ተነሣሥተው አሳልፈው ሰጥተውታልና ድምጻቸውን እንደ መብረቅ አሰምተው «በርባንን» አሉ:: «ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን ምን ላድርገው?» ሲላቸው «ስቀለው፣ ስቀለው» ብለው ጮኹ:: «ወስዳችሁ እንደ ሕጋችሁ ፍረዱበት» ባላቸው ጊዜ «ለእኛስ ማንንም ልንገድል አልተፈቀደልንም» አሉት:: ፊታቸውን ጸፍቶ አፋቸውን ከፍቶ ይህን ያናገራቸው መንፈስ ቅዱስ ነበር:: «ኢየሱስ በምን ዓይነት ሞት ሊሞት እንዳለው ሲያመለክት የተናገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው»[1] ነብያት የመሲህ ሞት በመስቀል ላይ እጆቹንና እግሮቹን በመቸነከር የሚፈጸም መሆኑን አስቀድመው ትንቢት ተናግረዋል::[2] አይሁድ ጲላጦስ «እንደ ሕጋችሁ ፍረዱበት» እንዳላቸው ቢወስዱት ኖሮ በድንጋይ ደብድበው በእሳት ጠበሰው በገደሉት ነበር:: ዳሩ ግን ትንቢተ ነብያት ይፈጸም ዘንድ በሮማውያን ልምድ መሠረት የሞት ፍርዱ እንዲፈጸም አይሁድ ግድ አሉ::

የስቅላት ፍርድ የተፈረደባቸው ሰዎች የሚሰቀሉበትን መስቀል መሸከም በዚያን ጊዜ በሮማውያን ዘንድ ልማድ ነበር:: የጌታ መስቀል ደግሞ አብረውት እንዲሰቀሉ ከተፈረደባቸው ከሁለቱ ወንበዴዎች መስቀል ተለይቶ በጣም ከባድ ነበር:: ይህም የሆነበት ምክንያት በርባን በኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ የሮማውያንን አገዛዝ በመቃወም አድማ አስነስቶ በነበረ ጊዜ ብዙ ሕዝቦች ተገድለው ነበር:: ከተገደሉትም ውስጥ አንዱ በኢየሩሳሌም ይኖር የነበረ የአንድ አናጢ ልጅ ነበር:: ብቸኛ ልጁን በርባን ባስነሳው አመጽ ምክንያት አጥቷልና በርባንን ለመበቀል አስቦ ሳለ በርባን ተይዞ

1. ዮሐ. ፲፰÷፴፪
2. መዝ. ፳፩(፳፪)÷፲፮

www.ethiopianorthodox.org

ሞት የተፈረደበት በመሆኑ ምንም ለማድረግ ሳይችል ቀርቶ ነበር። በልጁ ሞት የተጎዳው አባት በርባን በስቅላት እንደሚቀጣ እርግጠኛ ስለነበር ወደ ሮማውያን ወታደሮች ሄዶ ሁለቱ ወንበዴ ዎችና በርባን የሚሰቀልበትን መስቀል እንዲሠራ ፍቀዱልኝ ሲል የወይን ጠጅና ሌላም ስጦታ ሰጥተዋቸው ስለነበር ፈቀዱለት። ይህም ሰው መስቀሎቹን ሲሠራ በርባን ራሱ የሚሰቀልበትን መስ ቀል ተሸክሞ ጐልጐታ ድረስ ሲሄድ በተጨማሪ እንዲሠቃይ ለማ ድረግ የበረባንን መስቀል በተለይ በጣም ከባድ አድረጎ ሠርቶት ነበር። ነገር ግን ይህ ሰው እንዳሰበው ሳይሆን ቀርቶ በርባን በአይ ሁድ ግፊት ነፃ ወጥቶ ጌታ በበርባን ፈንታ መስቀሉን ተሸክሞ እየወደቀ እየተነሣ ሰውነቱ በላብ ተጠምቆ እስከ ቀራንዮ ተጓዘ። ቀድሞም አመጣጡ በወንጀለኛ ምትክ እርሱ ወንጀለኛ ተብሎ ወንጀለኛውን ነፃ ለማውጣት ነውና የበረባንን መስቀል እርሱ ተሸከመ። የበርባንን ሞት እርሱ ሞተ። «የእኛን ሞት ተቀብሎ የእርሱን ሕይወት ለእኛ ሰጠን»[1]

አይሁድም የልባቸው አሳብ ሞላ፤ ጌታም የመጣበትን ዓላማ ፈጸመ። ነፍሱን በገዛ እጁ አሳልፎ ሰጠ። የሲዖል መሠረቶች ተና ወጡ። ለዘመናት በነፍሳት ላይ ነግሦ የነበረው ዲያብሎስ ተሻረ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአካለ ነፍስ ወደ ሲዖል ወርዶ በሲዖል ለነበሩት ነፍሳት ነፃነትን ሰበከላቸው። ሲዖልንም መዘበራት። ሙስና መቃብርንም አጠፋ። በሦስተኛው ቀን መቃብር ክፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል ከኅቱም መቃብር ተነሣ። እስከ ዐርባኛው ቀንም ለደቀመዛሙርቱ እየተገለጠ ምሥጢረ መጻሕፍትን ገለጠላቸው። በዐርባኛው ቀን ወደ ባሕርይ አባቱ ወደ ቀደመ ክብሩ ዐረገ። በአብ ቀኝ ተቀመጠ።

1. ውዳሴ ማርያም





# 1.3 የክርስትና ማበብ

*«በለሱ ጎመራ፤ ወይኖችም አበቡ መዓዛቸውንም ሰጡ»*
*መኃ. ፪፥፲፫።*

የጌታ ዕርገት በሆነ በአሥረኛው ቀን የጌታ ቤተሰዎች የሚባሉት መቶ ሃያው[1] በአይሁድ ዘንድ ከሚከበሩት ሰባቱ በዓላት በአንዱ በሆነው በበዓለ ሃምሣ አንድ ልብ አንድ መንፈስ ሆነው በማርቆስ እናት ቤት ተሰብስበው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ። ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው። መንፈስ ቅዱስ በጸጋው አጥለቀለቃቸው። «መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ»[2] በማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተናገራቸው መሠረት ፍሩሐን የነበሩት ጥቡዓን /ደፋሮች/ ሆነው የሞት መው ጊያን ሰብሮ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ የተነሣውን ጌታ ያለ ፍርሀት በድፍረት ይሰብኩ ጀመር። በበዓለ ሃምሳ ዕለት ብቻ በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ሦስት ሺ አይሁድ በክርስቶስ አምነው ተጠመቁ። በዚህች ዕለትም የቤተ ክርስቲያን መሠረት ተጣለ።

በሐዋርያት እጅ ብዙ ድንቅ ተአምራት ይፈጸም ስለነበር በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ አይሁድ ከዕለት ዕለት በቁጥር እየበረከቱ መጡ። ኢየሩሳሌም በክርስቶስ አማኞች ልትጥለቀለቅ መሆኑን ያስተዋሉ የአይሁድ ካህናት ሥጋት ውስጥ በመግባታቸው ዕለት ዕለት እየበዙ የሚሄዱትን ክርስቲያኖች ለማጥፋት ቀኝ እጅ ይሆናቸው ዘንድ በሲሲሊያ ውስጥ ባለችው በጠርሴስ ከተማ ወደ ሚኖረው የሲሴይ ልጅ ሳውል ዘንድ የድረስልን ጥሪ መልእክት ላኩ። «ረቢ ጳውሎስ ሆይ የሙሴ ህግና የእስራኤል የመልእክት ሥራ በአንተ ዘንድ የተቀደሰ ሆኖ የሚቆጠር እንደሆነ ክርስቲያን

1. መቶ ሃያ የተባሉት አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት፣ ሰባ ሁለቱ አርድዕትና ሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት ናቸው።
2. የሐዋ. ሥራ ፩፥፰

www.ethiopianorthodox.org

የተባሉ ናዝራውያን ቁጥራቸው በየጊዜው እየበዛና እያደገ በመሄዱ እንደዚሁም ሕግን የሚቃወሙበት ኃይላቸው እየበረታ በማስቸገሩ እነሱን ለማጥፋት በቶሎ መጥተህ ርዳን»

ሳውል አባቱ ምንም እንኳን ከብንያም ነገድ የሆነ አይሁዳዊ ቢሆንም ቅሉ የሮማዊ ዜግነት ዕድል አግኝቶ ነበር:: እርሱም በውልደት ሮማዊ በመሆኑ ጳውሎስ በሚለው በሮማውያን ስም ይጠራ ነበር:: አብዛኛውን የልጅነት ጊዜውን ያሳለፈው ባለጸጋ ከነበረው አባቱ ጋር በጠርሴስ ቢሆንም ወላጆቹ የአይሁድን እምነትና ሥርዓት ተምሮ ረቢ /መምህር/ እንዲሆንላቸው ከነበራቸው ታላቅ ፍላጎት የተነሣ ወደ ኢየሩሳሌም ልከው በአይሁድ ዘንድ ስመጥር ከነበረው ከገማልያል ዘንድ እንዲማር አድርገውት ነበር::

በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ካህናተ አይሁድ የላኩለት መልእክት እንደደረሰው ለአይሁድ እምነትና ሥርዓት ቀናዒ ነበርና እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ክርስቲያኖችን ከኢየሩሳሌም ድርሻቸውን ሊያጠፉ ወደዚያ አቀና:: በኢየሩሳሌም የተቀጣጠለው የክርስትና እሳት ወደሌሎችም አጎራባች ሀገራት ገዛቱን አስፍቷል:: የኢየሱስን መሲህነት ያመኑ አይሁድ አንድ ልብ አንድ ሀሳብ ሆነው ሀብታቸውና ንብረታቸውን አስተባብረው የአንድነት ኑሮ መሥርተው ስለነበር ከመካከላቸው አንድ ስንኳ ችግረኛ አልነበረም:: ይህ በፍጹም ፍቅር ላይ የተመሠረተ የአንድነት ኑሮ ብዙዎች ወደ እነርሱ እንዲሳቡ ስላደረገ ማኅበረ ሐዋርያት እየሰፋ ሄደ:: በዚህ የተነሣ ማኅበሩን የሚያስተዳድሩ ሰባት አባላት ያሉት አንድ ኮሚቴ ሐዋርያት ሰየሙ:: እስጢፋኖስ የተባለው በጸጋ እግዚአብሔር የተሞላ ደቀመዝሙር የማኅበሩ አስተባባሪ ሆኖ ተሾመ::

የአሪት ትምህርት አበጋዝ የሆነው እስጢፋኖስ በቀሬና፣ በእስክንድርያ፣ በኪልቅያና በእስያ ካሉት ካህናተ አይሁድ ጋር በአፍም በመጽሐፍም እየተከራከረ መልስ በማሳጣት አፋቸውን ስላስያዛቸውና እንዲሁም እርሱን ከመቱ በእርሱ ሥር ያሉ ስምንት ሺ ማኅበረ እስጢፋኖስ ይበተናሉ:: በዚህም ክርስትናን እናዳክማለን ብለው «በሙሴና በእግዚአብሔር ላይ የስድብን ነገር ሲናገር ሰምተነዋል» የሚሉ የሐሰት ምስክር አዘጋጅተው ከከተማ አውጥተው በድንጋይ ደብድበው ገደሉት:: የጠርሴሱ ሳውል ለዚህ ዋና



www.ethiopianorthodox.org



አስተባባሪ ነበር[1] ከእስጢፋኖስ ሞት በኋላ ስምንት ሺ ማኅበረ እስጢፋኖስ በየአቅጣጫው እንደ አፈር ተበተኑ:: ክርስትናም ከመጥፋት ይልቅ ይበልጡኑ ተስፋፋ::

በሶርያ በምትገኘው ደማስቆ ውስጥ ብዙ አይሁድ ክርስትናን እንደተቀበሉ በተሰማ ጊዜ ራሱን የአይሁድ እምነት ጠበቃ አድርጎ የሚቆጥረው ሳውል ክርስቲያን የሆኑትን አይሁድ አስሮ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣ ዘንድ ከሊቀ ካህናቱ ዘንድ የማዘዣ ደብዳቤ ተቀብሎ መንገድ መሪዎችን አስከትሎ ወደ ደማስቆ ዘመተ:: ወደ ከተማዋ መግቢያ በተቃረበ ጊዜ ኃይለኛ መብረቅ ከሰማይ ባረቀ:: ሳውልም በምድር ላይ ወደቀ:: በዙሪያውም ድምፅ ተሰማ «ሳውል፣ ሳውል ስለምን ታሳድደኛለህ?» የሚል:: በፍርሀት የተዋጠው ሳውል «ጌታ ሆይ አንተ ማነህ?» አለው:: «አነተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ላንተ ይብስብሃል» አለው:: ሳውልም ከወደቀበት ተነሣ:: ዓይኖቹም ታውረው ነበር:: እጁንም ይዘው እየመሩ ወደ ደማስቆ አገቡት:: ሦስት ቀን ሙሉ እህል ውሃ ሳይቀምስ ቆየ::

በደማስቆ ይኖር የነበረ ሐናንያ የተባለ የጌታ ደቀመዝሙር ጌታ በራእይ በገለጸለት መሠረት በሳውል ላይ እጁን ጭኖ በጸለየለት ጊዜ ዓይኑ በራ:: በዚህ ወቅት የጳውሎስ ዓይነ ሥጋው ብቻ ሳይሆን ዓይነ ልቡናው ጭምር በርቶ ነበር:: አዲስ ስብዕናን ተላብሶ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሰው ጳውሎስ ሲያሳድዳቸው የነበሩት ክርስቲያኖችን መቀላቀሉ፣ እርሱ ከእነርሱ በላይ ሆኖ ስለ ክርስቶስ ሲመሰክር የሰሙ አይሁድ መገረም ብቻ ሳይሆን ድንጋጤም ፈጠረባቸው:: የቅዱስ ጳውሎስ የክርስቶስ ሐዋርያ መሆን አይሁድን እርቃናቸውን የሚያስቀር እንደሆነ አስቀድመው ስለገመቱ የግድያ መረባቸውን በቅዱስ ጳውሎስ ላይ ዘረጉ:: የከተማውን ዙሪያ ሌት ተቀን በጥብቅ ማስጠበቅ ጀመሩ:: ዳሩ ግን ይህን ያወቁ ክርስቲያኖች ቅዱስ ጳውሎስን በቅርጫት ውስጥ አድርገው በቅጥሩ ላይ አውርደው እንዲያመልጥ ስላደረጉ ከአይሁድ መረብ ሊያመልጥ ቻለ:: ዳሩ ግን ከኢየሩሳሌም ውስጥ በተለያዩ ሀገሮች መመስከሩን ቀጠለ::

---

[1] የሐዋ. ሥራ ፯÷፰

# ምዕራፍ ሁለት

## 2.1 የቤተ ክርስቲያን ጉዞ ወደ ምድረ ሮማ

*«ሑሩ ወመሐሩ አሕዛበ ምድር» ማቴ. ፳፰÷፲፱*

ሮሞሉስ የጥንትዋ ሮማ መሥራች እንደሆነ፣ አፈ ታሪክን መሠረት ያደረጉ የሮማ ታሪክ ጸሐፊዎች ይተርካሉ:: ዘመኑም ሰባት መቶ ሃምሣ ሦስት ዓመት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነው::[1] ስድሳ ሦስት ዓመት ከጌታ ልደት በፊት የሮማ ነገሥታት ምድረ ፍልስጤምን በቅኝ ግዛት ማስተዳደር ጀመሩ:: ከ14-37 ዓ.ም. ሮማን ያስተዳድር የነበረው ጢባርዮ ቄሣር ሲሆን ጌታ የተሰቀለው በእርሱ ዘመነ መንግሥት ነው:: ጢባርዮስ በምድረ ፍልስጤም እንደራሴው አድርጎ ከሾመው ከጲላጦስ ዘንድ ጌታን የተመለከተ ብዙ መረጃ ይደርሰው ነበር:: የቤተክርስቲያን አባቶች ትውፊታዊ መረጃን መሠረት አድርገው እንደሚተርኩት ጢባርዮስ ቄሣር እጅግ የሚወደው አንድ ልጅ ነበረው:: እርሱ በሞተበት ጊዜ በጣም አዝኖ ሬሳውን ሳያስቀብር ሰነበተ:: ከጥቂት ቀናት በኋላ ጌታ በኢየሩሳሌም ያደርገው የነበረውን ታምራት ያውቅ ነበርና «ከጢባ ርዮስ ቄሳር ምድራዊ ንጉሥ የተላከች መልእክት ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሠ ሰማይ ወምድር ትድረስ» ብሎ ልጁን እንዲያስነሳ ለት የምልጃ የልመና ጽሑፍ ጽፎ ይህችን መልእክትና የልጁን ሬሳ ወስደው ጐልጐታ /የጌታ መቃብር/ ላይ እንዲያኖሩለት ባለወ ጎቹን ላከ:: እነሱም ሔደው ደብዳቤይቱንና ሬሣውን በጌታ መቃ ብር ላይ ሲያኖሩት ሬሳው አፈፍ ብሎ ተነሥቷል:: ጢባርዮስም ከደስታው ብዛት የተነሣ የጌታን ውለታ ለመክፈል የዚህንስ ሰው እናቱን አምጡልኝ እኔ ቋሚ ለኋሚ ሚስቴ ገረድ ደነገጡር ሆነን እናገለግላታለን ብሎ እንደገና ሰው ቢልክ የእመቤታችን ክብር ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ ስላልሆነ ተሰውራባቸው አላገኟትም:: ዮሐንስ ወንጌላዊ ግን ሔዶ ስለክርስቶስ ከለደቱ እስከ ዕርገቱ ሰብኮለታል::[2]

1. The Colosseum P.4
2. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 115





ምንም እንኳን ከላይ በተገለጸው ታሪክ መሠረት ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ለጢባርዮስ ቄሳር ስለ ክርስቶስ ቢሰብክለትም ከእርሱ በኋላ የነገሡት የሮማ ነገሥታት የቤተክርስቲያን ጠላቶች እንደነበሩ በክርስቲያኖች ላይ ከፈጸሙት ኢሰብአዊ ድርጊት የምንረዳው ነው:: በወቅቱ የሮማ ግዛት በሰሜን ምሥራቅ በኩል ሰሜን አፍሪካን ግብጽንና መካከለኛውን ምሥራቅ ታናሽ እስያንና ግሪክን፣ በምዕራብ በኩል ፈረንሣይ እና እስከ ታላቋ ብሪታንያም ድረስ የተንሰራፋ ነበር::

ግሪኮችም ሆኑ ሮማውያን ባለብዙ አማልክት ቢሆኑም እነዚህ እንደሰው ለመሆን ምንም ያልቀራቸው አምላኮቻቸው የፈየዱላቸው አንዳችም ነገር ባለመኖሩ የውስጥ ስሜታቸውን ተረድቶ የልብ ፈቃዳቸውን የሚፈጽምላቸው፣ ሕይወታቸውን የሚታደጋት አምላክ ፍለጋ ነፍሳቸው ትቅበዘበዝ ነበር:: ሐመረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የፍቅር ዓርማዋን እያውለበለበች በሜዲትራንያን ባሕር ወደብ ላይ መልሕቅዋን ጥላ የሕይወት ጥሪ ደውሏን ባሰማች ጊዜ ማረፊያ አጥታ ትቅበዘበዝ የነበረች የአሕዛብ ነፍስ ቦታዋን አገኘች::

የድኅነት ፋና እያበሩ የትሕትናን ሸማ ተላበሰው በሮማ መንግሥት መናገሻ ከተማ እንደ እንጉዳይ በየቦታው ፍንድቅ ያሉት ክርስቲያኖች የአሕዛብን ልብ ማረኩ:: የመሪዋን ቃል መሠረት አድርጋ ወደ ምድረ አሕዛብ የተጓዘችው ቤተ ክርስቲያን በለስ ቀንቷት ብዙዎችን በማረከች ጊዜ የሮማ ባለሥልጣናት ዓይን በንዴት መቅላት ጀመረ::

በምድረ አሕዛብ በተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ላይ የመጀመሪያውን ስደት ያወጀው ኔሮን ቄሳር ነው /54-68 ዓ.ም./ በመሠረቱ ኔሮን ጭካኔ አብሮት ተወልዶ አብሮት ያደገ የሚባል ለት የሰው መግደል ሱስ የተጠናወተው የመጨረሻ ጨካኝ ሰው ነበር:: በሮማ መንበር ላይ በነገሠ በዓመቱ የአባቱን ልጅ /ወንድሙን/ አስገደለ:: ቆይቶ ደግሞ እናቱን በመርዝ ገደለ:: በዘመነ መንግሥቱ መገባደጃ ላይ ደግሞ ሚስቱን፣ እያስተማረ ያሳደገውን መምህሩን አስገድሏል::[1] በክርስቲያኖች ላይ ደግሞ ይህ ጭካኔው እጥፍ ድርብ ሆኖ ነበር:: ኔሮንም ሆነ ከእርሱ በኋላ የተነሡት የሮማ ነገሥታት

1. ተክለጻድቅ መኩሪያ የኢት. ታሪክ 2ኛ መጽሐፍ ገጽ 174



www.ethiopianorthodox.org

ቤተክርስቲያንን ጠምደው የያዙበት ምክንያት ምን ነበር? ብንል የሚከተሉት እንደምክንያት ሊጠቀሱ ይችላሉ::

1. የክርስትና ሃይማኖት ምንጭ የሮም ቅኝ ግዛት የሆነችው ምድረ ፍልስጤም መሆኗ በሮማ ባለሥልጣናት ዘንድ ጥርጣሬን በማሳደሩ አይሁድ የሮማን ግዛት ለማፍረስ የፈጠሩት ሃይማኖት ለበስ ፖለቲካ ስለመሰላቸው::
2. የሮማ ነገሥታት በግብዝነት የሚፈጽሙትን የመመለክ ጠባይ የክርስትና ትምህርት በይፋ ይቃወም ስለነበር እነርሱ እንዲመለኩ እንዲሰገድላቸው ሲፈልጉ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ይህን አጥብቃ ትቃወም ስለነበር::

ኔሮን ቄሣር ክርስቲያኖችን ለመፍጀት መነሻ ያደረገው የሮማን ከተማ መቃጠል ነው:: ለሮማ መቃጠል ዋናው ምክንያት ክርስቲያኖች እንደሆነ ተደርጎ መወራት ጀመረ:: የጣዖት ካህናት ለአማልክቶቻችን የማይተዘዙ ክርስቲያኖች በመኖራቸው አማልክት ተቆጥተው ከተማይቱን አቃጠሏት ሲሉ፤ ሌሎች ደግሞ ራሳቸውን ክርስቲያኖች ሆን ብለው በእሳት አቃጠሏት የሚለውን ወሬ ማስወራት ጀመሩ::

አሮጌዋ ከተማ በአዲስ ከተማ እንድትተካ ለእርሱም ሰፊና ያማረ ቤተ መንግሥት እንዲሠራለት በመፈለግ ኔሮን ቄሳር ራሱ ቃጠሎውን በስውር እንደፈጸመ በአንዳንድ የታሪክ ጸሐፍት ዘንድ ተዘግቧል:: ጻሩ ግን ቃጠሎው ያስከተለው የንብረትና የሕይወት ውድመት ከሕዝቡ በኩል አመፅ እንዳያስነሣ ቃጠሎውን ያስነሱት ክርስቲያኖች እንደሆኑ የሚወራውን ወሬ ይበልጥ አናፈሰው:: ሕዝቡንም በማሳመን በክርስቲያኖች ላይ ዘግናኝና አሰቃቂ እልቂት አወጀ:: ብዙ ክርስቲያኖች ሥጋቸው እንደ ሸንኩርት ተቀረደደ በፈላ ዘይት ተቀቀሉ፣ ሕዋሳታቸውን እየበጣጠሱ ለጣዖታቶቻቸው መስዋዕት አድርገው አቀረቡት:: ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ የሰይፍ ከረባት አስሮ በሮማ አደባባይ ላይ የተሞሸረው «በሸመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ ሌላውም ያስታጥቅሃል ወደማትወደውም ይወስድሃል»[1] የሚል ትንቢት አስቀድሞ በጌታ የተናገረለት ቅዱስ

[1] ዮሐ. ፳፩÷፲፰





ጴጥሮስ የቁልቁሊት ተሰቅሎ በሰማዕትነት ያለፉት በዚህ በኔሮን ቄሳር ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ አንገቱን በኔሮን ቄሳር ባለወጎች በተቀላ ጊዜ ከሰውነቱ የተለየችው ራሱ /ጭንቅላቱ/ ሦስት ጊዜ መሬት እየነካች በመዝለል ባገኘችው በረከት ደስታዋን መግለጽዋ ዛሬ አንገቱ በተቀላበት ቦታ የፈለቁት ሦስት የውሃ ምንጮች ሕያው ምስክር ናቸው:: የቅዱስ ጴጥሮስ አጽም ሰማዕትነትን በተቀበለበት በቫቲካን ውስጥ ተቀብሯል::

ከ66-70 ዓ.ም. ባለው ጊዜ እስራኤል አገራቸውን ከቅኝ ገዥዎች ነፃ ለማውጣት የጀመሩትን አመጽ ለማስቆም ወደ ኢየሩሳሌም ክተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብሎ የዘመተው ቬስፓስያን የእስራኤልን እንቅስቃሴ ደምስሶ ትልቁን የአይሁድ ቤተ መቅደስ በማቃጠሉና፣ ማንኛውንም የአይሁዶች ስብሰባና እንቅስቃሴ በሮማ ባለሥልጣናት ዘንድ በጥርጣሬ ይታይ ስለነበር ክርስቲያኖችም ሃይማኖታዊ ስብሰባቸውና ትጋታቸው በሮማ ነገሥታት ዘንድ በበጎ የማይታይ መሆኑን በመረዳታቸው መናኻሪያቸው የነበረችውን ኢየሩሳሌምን ለቀው ወደ ሮም፣ እስክንድርያ፣ አንጾኪያና ወደ ሌሎች አጎራባች አገሮች ተሰደዱ:: በምድረ ፍልስጤም የተወለደችው ቤተ ክርስቲያንም እድገትዋ በምድረ አሕዛብ ሆነ::

በኔሮን ቄሳር የተጀመረው የቤተ ክርስቲያን ስደት ከእርሱ በኋላ በተነሡት ቄሳሮችም ተጋግሞ ቀጥሏል:: የቬስፓስያን ልጅ የሆነው ዶሚቲያን /Domitian/ /81-96 ዓ.ም./ በክርስቲያኖች ላይ ከኔሮን ቄሳር ያልተናነሰ እልቂትን የፈጸመ ነው:: ገና በሕይወት ሳለ ምስሉን አሠርቶ ሰው ሁሉ ለምስሉ እንዲሰግድ አዝዞ ነበር:: በኤፌሶን የሐዋርያነት አገልግሎቱን በመፈጸም ላይ የነበረው ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ይህን ተቃውሞ በማስተማሩ የንጉሡን አዋጅ ተቃውሟል ተብሎ ፍጥሞ ወደተባለች ደሴት ተግዟል::

ከ98-117 ዓ.ም. የሮማን በትረ ሥልጣን የጨበጠው ትራጃን /Trajan/ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ነገሥታት ለየት ብሎ በኃይል ብቻ ሳይሆን በዘዴና በማስፈራራት ጭምር ክርስቲያኖችን ወደ ቤተ ጣዖት ለመመለስ ሙከራ ያደረገ ነው:: ሆኖም ሙከራው ሳይሳካለት በቀረ ጊዜ ያው የተለመደውን እልቂት በክርስቲያኖች ላይ ፈጽሟል:: ትራጃን ከእርሱ በፊት እንደነበሩት ነገሥታት ክርስቲያኖች ከአውሬ ጋር ሲታገሉና አውሬው ሲቦጫጭቃቸው



www.ethiopianorthodox.org

እያየ ይዝናና ነበር:: የሮማ ቄሳሮች ሰውን ከሰው፣ ሰውን ከአውሬ ጋር እያፋለሙ ያን በማየት የሚዝናኑበት ኮሎስየም /ፍላቪያን አምፊ ቴአትር/ የተባለ የቴአትር ማሳያ ቦታ ነበር:: ይህ የቴአትር ማሳያ ቦታ /ስታዲየም/ ከ75-80 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ተሠርቶ ያለቀ ሲሆን ሰባ ሦስት ሺ ተመልካች የመያዝ አቅም ነበረው::[1] ግላድያተርስ በሚል ስም የሚጠሩ ተፋላሚዎች የተለያየ የጦር መሣሪያ ይዘው እርስ በእርሳቸው ይፋለማሉ:: ያየለው ደካማውን በመግደል አሸናፊነቱን ያውጃል:: ክርስቲያኖችም በግላድያተርስ ስም ከአውሬ ጋር እንዲፋለሙ ተይዘው ወደ ኮሎስየም ይወሰዱ ነበር:: የወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ደቀመዝሙር የነበረው የአንጾኪያ ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ አግናጥዮስ በሮማውያን ወታደሮች ተይዞ ከሶርያ ወደ ሮም በመምጣት በዚህ ኮለሲየም ውስጥ ከአንበሳ ጋር እንዲታገል ተጥሎ በአንበሳ ስለተበላ «ለአንበሳ የተሰጠው» በሚል ቅጽል ይጠራል::

በዓይነትም ሆነ በብዛት ተመሳሳይና ተወዳዳሪ የሌለው እልቂትን ቤተ ክርስቲያን ያስተናገደችው በዘመነ ዲዮቅልጥያኖስ ነው /280-305 ዓ.ም./ ክርስቲያኖችን ለመደምሰስና ለማጥፋት እንደርሱ ያለ ኃይለኛ የቤተ ክርስቲያን ጠላት በሮም አልነገሠም የተባለለት ነው:: ዲዮቅልጥያኖስ በክርስቲያኖች ላይ ጥላቻ ያደረበት ስለሁለት ምክንያቶች ነበር::

አንደኛው:- የፋርስ መንግሥት የሮምን የግዛት ድንበር በመጣሱ በጦር አበጋዙ በጋሌሪዮስ አዝማችነት የሮምን ዳር ድንበር ለያስከብር የሔደው ጦሩ ድል ሆነ የጣዖታቱ ካህናት ሠራዊቱ ድል የሆነው በመካከሉ ክርስቲያኖች በመኖራቸው አማልክቶቻቸው በእነርሱ አዝነው መሆኑን ሊዲዮቅልጥያኖስ በማሳመናቸው::

ሁለተኛው:- እንደ ሌሎቹ የሮማ ነገሥታት ሁሉ ዲዮቅልጥያኖስም ምስሉን አሠርቶ በግዛቱ ያሉ ሁሉ ለምስሉ እንዲሰግዱለትና አምላካዊ ክብር እንዲያቀርቡለት አዝዞ ሳለ ክርስቲያኖች ግን ይህን ባለማድረጋቸው የአጵሎስ ካህናተ «እነዚህን ደፋሮችና ሰው ናፋቂዎች ከግዛትህ ማጥፋት ይገባሃል የነገሥታትን ክብር ይዳፈራሉ የአምላኮቻችንንም ሕልውና ይቃወማሉ:: እነሱ ካልጠፉ ለመንግሥታችንም ሆነ ለአምላኮቻችን ጤና አይሰጡም» ስላሉት::

1. The Colosseum P.3





ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በሮማ ግዛት ውስጥ የሚገኙ ክርስቲያኖች ሁሉ በያሉበት እንዲረሸኑ፣ አብያተ ክርስቲያናት እንዲደመሰሱ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲቃጠሉ፣ የቤተ ክርስቲያን ንብረት የሆነ ሁሉ እንዲወረስ አወጀ:: ይህም ሁሉ ሆኖ ዲዮቅልጥያኖስ ቤተ ክርስቲያንን ለመደምሰስ አልቻለም::

በአንድ ወቅት የሩሲያ ኮሚኒስት መሪ የነበረው ክሩሽኔቭ የሚከተለውን ርዕዮተ ዓለም መነሻ አድርጎ በሩሲያ በሚኖሩ ክርስቲያኖች ላይ እልቂት አውጀባቸው ነበር:: ብዙ ክርስቲያኖች እየታደኑ በባቡር ታጭቀው ሳይቤሪያ ወደተባለው በረዷማ ስፍራ እየተወሰዱ በአሰቃቂ ሁኔታ እንዲሞቱ ይደረግ ነበር:: ይህ ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት ግን ክርስቲያኖችን ይበልጡኑ አጠነከራቸው:: በዓላማቸውም እንዲጸኑ ይበልጥ አስተዋጽኦ ማድረጉን የተገነዘበው ክሩሽኔቭ «ክርስቲያንና ሚስማር አንድ ናቸው ሁለቱም ሲመቱዋቸው እየጠበቁ ይሄዳሉ» አለ ይባላል::

በዘመነ ዲዮቅልጥያኖስም የሆነው ይህ ነበር:: አሰቃቂ በሆነ መንገድ ክርስቲያኖች ቢጨፈጨፉም በሕይወት የቀሩት በቁማቸው ሕዋሳቶቻቸውን እየቆራረጠ የገደሉአቸው የወገኖቻቸው አሟሟት ሳያስቅቃቸው ሰማዕትነት አያምልጥህ እየተባባሉ ለሞት ይጠራሩ ነበር:: የዲዮቅልጥያኖስ ጭካኔያዊ ተግባርም የቤተ ክርስቲያንን ጉዞ አልገደበም:: ከገጸ ምድር፣ ወደ ካታኮምብ እንድትገባ በዚያም ትምህርትዋን እንድታስፋፋ አደረጋት እንጂ::

## 2.2 ካታኮምብ

*«በአንዲቱ ከተማም መከራ ቢያሳዩአችሁ ወደሌላይቱ ሽሹ»*
*ማቴ. ፲፥፳፫*

ከሁለተኛው መቶ እስከ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያለው ጊዜ የቤተ ክርስቲያን የስደት ዘመን እንደነበር ቀደም ብለን አይተናል:: የመከራው ጽናትም ቤተ ክርስቲያንን ካታኮምብ እንድ ትገባ አስገድዷታል:: በገጸ ምድር ላይ የመኖር መብታቸው የተገ ትገባ በዋሻ፣ ፈፈው ክርስቲያኖች ከሮማ ባለሥልጣናት ዕይታ ለመሰወር በዋሻ፣ ቀደም ለመቃብር በሠሩት ካታኮምብ እንዲሸሸጉ አድርጓቸዋል:: ቀደም ብለው ለሥጋቸው /አስከሬናቸው/ ማረፊያ ይሆኑ ዘንድ የሠሩዋቸው



www.ethiopianorthodox.org

የመቃብር ቦታዎች /Catacombs/ መኖሪያቸው ሆነው እንደነበር ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ የምንረዳው እውነታ ነው:: እነዚህ ከመሬት የላይኛው ክፍል ወደ ታች ብዙ ጠልቀው የተቆፈሩ ካታኮምቦች በወቅቱ በትረ ሥልጣኑን ጨበጠው ከነበሩት የሮማ ባለሥልጣኖች ዕውቅና ውጭ የነበሩ ምሥጢራዊ የክርስቲያኖች መኖሪያ እንደ ነበሩ ጥንታውያን የታሪክ መዛግብት የሚተባበሩበት ሲሆን ዘመና ውያኑ ተመራማሪዎች ደግሞ ወቅታዊ ግኝቶች ለዘመናት የዘለቀ ውን አስተሳሰብ ይሽራሉ በማለት ካታኮምቦች በወቅቱ ከነበሩት የሮማ ባለሥልጣናት ዕውቅና ውጭ እንዳልነበሩ እንደውም በአግባቡ የሚታወቁ እንደ ነበሩ፣ የጥንታውያን ክርስቲያኖችም መኖሪያ እንዳልነበሩ ዳሩ ግን ለጸሎትና ለስብሰባ ግን ይጠቀሙባቸው እን ደነበር ግኝቶቻቸውን መነሻ አድርገው ያስቀመጡ ቢሆንም የቀደ ሙት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዘጋቢዎች ያቆዩልን እውነታ ግን ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ሰማዕታት ካታኮምብ መግባትዋን ነው::

ከሁለት ሺ ዓመት በፊት ለነበሩት ሮማውያን «ካታኮምብ» የሚለው ስያሜ ሸለቆዋማ ከሆነ ቦታ ጋር የተያያዘ ነበር:: የኋላ ኋላ ግን ክርስቲያኖች ከመሬት ሥር ቆፍረው ለሠሩዋቸው የመቃ ብር ቦታዎች መጠሪያ ሆነ:: የጥንት ክርስቲያኖች ግን መካነ መቃብራቸውን «የእረፍት ቦታ» /place of rest-dormitory/ በሚለው መጥራትን ይመርጡ ነበር:: ትንሣኤ ሙታንን በማዘከር::

በጥንትዋ የሮማ ከተማና በአጎራባቾችዋ ያሉት ከስድሳ በላይ የሆኑ ካታኮምቦች በሁለተኛውና በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መካከል እንደተሠሩ ይታመናል:: በዚህ ሥራ ላይ በትጋት ተሰማ ርተው የነበሩ ክርስቲያኖች ፎስርስ /Fossores/ በሚል ስያሜ ይታወቁ ነበር:: የዛሬዎቹን መሐንዲሶች ስም ይጋራሉ:: በመጀመ ሪያው ምዕተ ዓመት የነበሩ ክርስቲያኖች ከአሕዛብ የተለየ የራሳ ቸው የሆነ የመቃብር ቦታ አልነበራቸውም:: እርግጥ ነው ቅዱስ ጴጥሮስ በዛሬዋ ቫቲካን፣ ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ በኦስቴንስ ጎዳና /Via ostiense/ አጠገብ መቀበራቸው ይነገራል:: ከሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ግን ክርስቲያኖች ተስፋ ትንሣኤ ያለው በድነ ሥጋቸው ከአሕዛብ በድን ተለይቶ ለብቻው የሚያርፍበት ቦታ ሊኖር እንደሚገባ በማመናቸው የራሳቸው የሆነ መካነ መቃብር ከመሬት ውስጥ ቆፍረው ማዘጋጀት ጀመሩ::





ዛሬ በጥንትዋ የሮማ ከተማ ላይ ሕያው ምስክር ሆነው የሚታዩት ካታኮምቦች የጥንት ክርስቲያኖችን የሃይማኖት ጽናት፣ መንፈሰ ጠንካራነትና ብርታት፣ ከማስገንዘብ በተጨማሪ ቤተ ክር ስቲያን ያሳለፈችውን የፈተና ዘመን ለትውልዱ ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩ መስታወቶች ናቸው::

በዚያን ዘመን ከነበረው ሥልጣኔ አንጻር ሲታይ የጥንት ክርስቲያኖች የሠሩዋቸው ካታኮምቦች የሚያስደንቁና ተአምር ነው የሚያሰኙ ናቸው:: ዶማና አካፋ ተጠቅመው፣ ጭል ጭል በሚል መብራት እየተመሩ ከሃያ ሜትር በላይ ጥልቀት፣ ሃያ ኪሎ ሜተር ርቀት ያለውና ወደ ተለያዩ ወለሎች በደረጃ የሚወረድበት የተለ ያዩ መቃብራት፣ የጸሎትና የመሰብሰቢያ አዳራሾች አካቶ የያዘ የመሬት ውስጥ መንደር መሥራት ችለዋል:: የተለያየ ቅርጽና አሠራር ካላቸው መቃብራት ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል::

<u>ሎኩሊ</u> /Loculi/:- ግድግዳው ተቦርቡሮ የአራት ማዕዘን /ሬክታንግል/ ቅርጽ ይዞ የተሠራ ለአንድ ሰው መቀበሪያ ብቻ የሚያገለግል ሲሆን ሟቹ በጨርቅ ተገንዞ ያለ አስከሬን ሣጥን የሚቀበርበት ነው:: አስከሬኑ ከተቀበረ በኋላ የመቃብሩ አፍ በሸክላ ወይም በእምነበረድ ይዘጋል:: ይህ ዓይነቱ መቃብር በብዛት በጨ ቅላ ዕድሜ ሳሉ ለሚሞቱ ሕጻናት የተዘጋጀ እንደነበር ከተቀበሩት ሕጻናት መረዳት ይቻላል:: በብዛትም ከሌሎቹ መቃብራት የላቀ ነው:: በወቅቱ የሕፃናት ሞት ከፍተኛ እንደነበር ከመቃብራቱ ብዛት መገንዘብ ይቻላል::

<u>አርኮሶሊየም</u> /Arcosolium/:- ውብና ለየት ያለ ቅርጽ እንዲ ኖረው ተደርጎ የተዘጋጀ የመቃብር ዓይነት ነው:: ከላይ የደጋን /arch/ ዓይነት ቅርጽ አለው:: ለአንድ ሰው ወይም ለመላ ቤተሰብ እንዲበቃ ተደርጎ የተሠራ ነው:: በሦስተኛውና በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተለመደ የመቃብር ዓይነት ነው::

<u>ሳርኮፋገስ</u> /Sarcophagus/:- ከድንጋይ ወይም ከእምነ በረድ የተሠሩ እንደ ሣጥን ያሉ መቃብራት ሲሆኑ ከዋጋቸው ውድነት የተነሣ የዚህ ዓይነት መቃብራት በካታኮምብ ብዙም አይታዩም::

ከእነዚህ መቃብራት በተጨማሪ ትናንሽ ክፍሎች /cubicula/ ሰፋ ያሉና ለጸሎት፣ ለመሰብሰቢያና ለተለያዩ መንፈሳዊ አገልግ ሎት ይጠቀሙባቸው የነበሩ በቅዱሳት ስዕላት፣ በሞዛይክ እና በሌ

www.ethiopianorthodox.org

ሎች አርክቴክቸራል ሥራዎች የተጌጡ ልዩ ክፍሎች /crypt/ ይገኛሉ::
በእነዚህ ክፍሎች በሰማዕትነት ያለፉ ቅዱሳን መቃብራት ይገኛሉ::
መሸሸ
በዘመነ ሰማዕታት ለነበሩ ክርስቲያኖች ካታኮምቦች
ጊያቸው ብቻ ሳይሆኑ እምነታቸውን ማጠንከሪያ ትምህርታቸውን
ማስፋፊያም ጭምር ነበሩ:: ለዚህም በተለያዩ ካታኮምቦች በአመድና
በከሰል ከእጽዋት ባዘጋጁት ቀለም የተሳሉ ቅዱሳን ስዕላት ዓይነተኛ
ምስክር ናቸው:: የጥንት ክርስቲያኖች ትምህርተ ሃይማኖትን በም
ሳሌ /symbols/ እንዴት ያስተምሩ እንደነበር ዛሬ ለታሪክ በቀሩልን
ካታኮምቦች የተገኙት ጥቂቶቹ ማስረጃዎች /ቅሪቶች/ ያስገነዝቡናል::
በግ
<u>መልካሙ እረኛ</u> /Good shepherd/:- እረኛው በትከሻው
ተሸክሞ የተሳለ ሲሆን በካታኮምብ መግቢያ በር ፊት ለፊት የሚ
ገኝ ነው:: እረኛው «ቸር ጠባቂ /እረኛ/ እኔ ነኝ» ያለው የጌታችንና
የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሲሆን፤ በጉ ደግሞ
በሰይጣን አሳችነት ከፈጣሪው አንድነት ከመንጋው ተለይቶ ባዝኖ
የነበረው የሰው ልጅ ምሳሌ ነው::[1]



1. ማቴ. ፲፰÷፲-፲፬
2. The Catacombs P.12





<u>ሁለት እጆቹን የዘረጋ ሰው ስዕል</u> /Orante/:- በዚህ ስዕል
አማካይነት በገነት ውስጥ በሰላምና በደስታ ያለች ነፍስን መስለው
ያስተምሩ ነበር::[1]



<u>ዓሣ /Ichthus/</u>:- ዓሣ በግሪክኛ ኢኽቲስ ይባላል:: የጥንት
ክርስቲያኖች ኢኽቲስ የሚለውን በምሕፃረ ቃልነት /acrostic/
ይጠቀሙበት ነበር::

ኢ = ኢየሱስ = ኢየሱስ
ኽ = ኽሪስቶስ = ክርስቶስ
ቴ = ቴው ኢዮስ = ወልደ እግዚአብሔር
ስ = ሶቴር = መድኅን

በተገናኝ ሲነበብ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር
መድኅን የሚል ትርጉም ይሰጣል::[2]

1. The catacombs P.9
2. The catacombs P.8



www.ethiopianorthodox.org

<u>መልሕቅ /Anchor/</u>:- በክርስቶስ በማመን የሚገኘውን ተስፋ ሕይወት የሚያመለክት ነው::[1]



<u>ፒኮክ /Peacock/</u>:- የለያየ ኅብረ ቀለማት ያላት ይህቺ ወፍ ከጌጥነት ባለፈ የማትሞትና የማትፈርስ የሕያዊት ነፍስ አምሳል ተደርጋ ተወስዳለች::

<u>ፎኒክስ /Phoenix/</u>:- በዚያን ዘመን በብዙዎች ዘንድ ይታመን የነበረው ፎኒክስ በመባል የምትታወቀው ወፍ መስህብነት ካለው ቀለሟ በተጨማሪ በየሺህ ዘመኑ እየታደሰች የምትኖር መሆንዋ ይነገርላታል:: ሺህ ዘመን ሲሞላት አካልዋን እሳት ውስጥ ትጨምረዋለች:: ከዚያም አመድ የሆነው አካልዋ ላይ ዝናብ ሲዘንብባት እንደገና ሕይወት ዘርታ በአዲስ አካል ትነሣለች:: ይህችን ወፍ ለትንሣኤ ሙታን መኖር ምሳሌ አድርገው ይጠቅሷት ነበር::

1. The catacombs P.9





ከምሳሌያዊ አገላለጽ /Allegorical figures/:- በተጨማሪ የቅዱሳት መጻሕፍትን ታሪኮችን በየጣሪያውና ግድግዳው ላይ ይስሉ ነበር:: ብሉይ ኪዳን ለሐዲስ ኪዳን እንደ ጥላ እንደመርገፍ መሆኑን በስዕላቱ ይገልጡ ነበር:: በምክረ ከይሲ ተታለው ትዕዛዙን እግዚአብሔርን የጣሱት አዳምና ሔዋን ከገነት ሲባረሩ፣ ኖኅና ቤተሰቡ በሠሩዋት መርከብ አማካይነት ከጥፋት ውኃ እንዴት እንደዳኑ፤ አብርሃም ልጁ ይስሐቅን ሊሰዋ ካራውን በልጁ አንገት ላይ እንደሰነዘረ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ የተያዘ በግ በዱር ውስጥ ታስሮ ሲያይና በልጁ ምትክ በጉን ሲሰዋ፤ ሊቀ ነብያት ሙሴ በበትሩ ዐለቱን መትቶ ለእስራኤል ውኃን ሲያፈልቅ፤ ረበናተ አይሁድ ሶስናን ሲከስዋት፤ ዳንኤል በአናብስት ጉድጓድ እንደተጣለ፤ ሠለስቱ ደቂቀ በእሳት ውስጥ እንደተጣሉ መልአከ እግዚአብሔር በመካከላቸው በትረ መስቀሉን ይዞ እንደቆመ ሌሎችም የብሉይ ኪዳን ታሪኮችን በስዕላት በካታኮምብ ይገልጹ ነበር::

የሐዲስ ኪዳንን ታሪክ በስዕላት ሲገልጹ ደግሞ ክርስቶስ በከብቶች ግርግም መወለዱን፤ ሰብዓ ሰገል እጅ መንሻቸውን ይዘው ሲሰግዱለት፤ እመቤታችን ልጅዋን አዝላ ወደ ምድረ ግብፅ ስትሰደድ፤ ጌታ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ሲጠመቅ ጌታ እውሩን በእጁ ዳሶ ሲያበራው፤ አሥራ ሁለት ዓመት ደም ሲፈሳት የነበረችው ሴት የጌታን የልብስ ዘርፍ ነክታ እንደተፈወሰች፤ የሞተው አልአዛር በጌታ ትዕዛዝ ከነመግነዙ ከመቃብር ሲወጣ፤ ጌታ ሰባት እንጀራና ጥቂት ዓሣን አበርክቶ ከአራት ሺ በላይ ርሁባንን እንዳጠገበ፤ ሰባት ቅርጫት ትርፍራፊም እንደተነሣ፤ ሌሎች ጌታ በዘመነ ሥጋዌው የፈጸማቸው ተአምራት በሥዕላት ይገልጹ ነበር::

በዘመነ ሐዋርያትና በሐዋርያነ አበው ጊዜ የተፈጸሙትን ድንቅ ተአምራት፣ ስለክርስቶስ አምላክነት ሲመሰክሩ በአላውያን ነገሥታት በአሰቃቂ ሁኔታ እንዴት እንደተገደሉ፤ በሰማዕትነት በማለፋቸውም የዘላለማዊ ሕይወት ባለቤት እንደሆኑ በእግዚአብሔር መንግሥት ያላቸውን ፍጹም ክብር ሁሉ በስዕላት አማካይነት ይገልጹ ነበር::

እንዲሁም በሞት የተለዩ ወገኖቻቸውን መልካም ተግባርና በሕይወተ ሥጋ በነበሩበት ጊዜ ያደረጉትን አስተዋጽኦ እጥር ምጥን ባለ አገላለጽ በሟቾቹ መቃብር ላይ በጽሑፍ ያሰፍሩ ነበር::

www.ethiopianorthodox.org

በልሳነ ላቲንና ግሪክ ተጽፈው አያሌ ዘመናትን ተሻግረው ለዛሬው
ትውልድ መልእክታቸውን ከሚያስተላልፉት ብዙ የካታኮምብ
ጽሑፎች ጥቂቶቹ ወደ ሌላ ቋንቋ ተተርጉመዋል:: ከእነዚህ ውስጥ
ጥቂቶቹን ለአብነት ያህል እንደሚከተለው እናቀርባለን::

«ፍላቪየስ ክሪስፒነስ:- በለጋነት ዕድሜዋ በ28 ዓመትዋ
ለተጠራችው አውረሊያ አኒያን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በትዳር
ስንኖር አንድ ቀንም አሳዝናኝ አታውቅም:: ፍጹም የፍቅር ሰው
ነበረች:: ቅድስት ነፍስሽ በክርስቶስ ሰላም እንደምታገኝ እምነቴ
ነው:: ደህና ሁኝልኝ ውዴ»

«ኘሮቢሊያነስ ለታማኝ ሚስቱ ፌሊሲቲ:- ደግነትዋ፣ ቀናነ
ትዋ ባጠቃላይ ጥሩ ስብዕናዋ በመላ ጎረቤቶቻችን የታወቀና የተ
መሰከረላት ነበረች:: ለስምንት ዓመታት ያህል ባለቤትዋ ከአጠ
ገብዋ ባልነበረ ጊዜ ለባልዋ ታማኝ ሆና የኖረች»

«የተወለድኩት በሮማ ነው:: ስሜን ከፈለጋችሁ ጁሊያ እባ
ላለሁ:: ከባሌ ፍሎሬንተስ ጋር በፍጹም ፍቅርና መተማመን ኖረ
ናል:: በሕይወተ ሥጋ ያሉና ህብተ ወልድና ስመ ክርስትና ያገኙ
ሦስት ልጆችን ትቼለት ወደ መካነ ሰላም ወደ ጌታ ሄጃለሁ»

«እጅግ የተወደደው ባለቤቴ አሌክስ ቤተ ክርስቲያንን በማ
ገልገል የተጠመደ ሰው ነበር:: ለአሥራ አምስት ዓመታት በትዳር
ስንኖር አንድም ቀን ክፉ ፊት አሳይቶኝ አያውቅም ነበር:: ሰላማዊ
ሕይወትን ከቅዱሳን ጋር ይኖር ዘንድ ወደ ተገባው ሥፍራ ሄዷል»

«ስቴፈንና ጄኔሮሳ እጅግ የወደዱ ጣፋጭ ወላጆች ነበሩ::
በትዳር ዘመናቸው ያለአንዳች ጭቅጭቅና ንዝንዝ በሰላምና በፍቅር
ኖረዋል:: እነዚህን ጣፋጭ ወላጆቹን በማጣቱ ደስታ የራቀው
ዱሩሰስ ይህን መቃብር አሠርቶላቸዋል»

«የአሥር ዓመቱ ጨቅላ ጁኒስ በዚህ ውስጥ ሰላማዊ እንቅ
ልፍን አንቀላፍቷል:: በኃጢአት ያላደፈው ጠቦት ንጹሕ ሰውነቱን
ለክርስቶስ ሊያቀርብ ወደ ሰማያዊው ንጉሥ ተጉዟል»

«ጣፋጭና ልዩ ክህሎት የነበረው ደልማቲያስ:- ያልታደለው
አባቱ ለሰባት ዓመታት እንኳን ከእርሱ ጋር ለመደሰት የአባትነት
ወግ አልደረሰውም:: ግሪክኛ እየተማረ ሳለ ላቲንኛን በግሉ ያጠና
ነበር:: በማርች 25 ተወለደ:: በፌብሩዋሪ 11 በሞት ተለየ:: ይህን
መቃብር አባቱ አሠራለት»



www.ethiopianorthodox.org



«ግልጽና ቀጥተኛ ጠባይ የነበራት ሲኮንዳ:- በጥሩ ስብዕናዋና
በፍጹም እምነትዋ የተወደደች ነበረች:: ራስዋን ለክርስቶስ በማጨት
እስከ ሞተችበት ቀን ድረስ በድንግልና ኖራለች:: ከአንደበትዋ
ነገረ ዘርቅ ወጥቶ የማያውቀው የዋኒት ርግብ በተወለደች በ20
ዓመትዋ ዘላለማዊ ሕይወትን ወደምታገኝበት ቦታ በጁላይ 15 ቀን
በሞት ተጉዛለች»

«እናንተ ኅዙናን፣ እንባችሁን አብሱ! እናንት ቅዱሳን የእግ
ዚአብሔር ሕዝቦች ስለዲየቆን ሬደምፐስ የጠየቃችሁ ከእግዚአብ
ሔር መንግሥት ድንገታዊ ጥሪ ደርሶት ሄዷል:: በምድራዊ ሕይ
ወቱ ትሕትናን የተላበሰ በአገልግሎቱ የተመሰገነ ወጣት ነበር::
በጠላት ዲያብሎስ ላይ ድልን ተጎናጽፎ ዛሬ የገነት ባለቤት ሆኗል»

«የደማስስ[1] እህት በዚህ አርፋለች:: ስሟን ለሚሻ አሪን
ይባላል:: ሕይወቷን ፍጹም ለእግዚአብሔር አሳልፋ የሰጠች ድንግ
ላዊት ነበረች:: በፍጹም መንፈሳዊ ትጋትዋም ያፈራችው ፍሬ
እነሆ በምድር ላይ ይታያል:: አ አንቺ ድንግል በአንቺ ሕይወት
የነበረው የጽድቅ ብርሃን በእኔም ሕይወት በርቶ ይኖር ዘንድ
በጸሎትሽ አስቢኝ»

በካታኮምብ ውስጥ የሚገኙት የመቃብር ላይ ጽሑፎች
በአጸደ ነፍስ ያሉት በአጸደ ሥጋ ላሉት ወገኖቻቸው እንዲያማል
ዱአቸው የሚያመለክቱም ናቸው:: ከብዙው በጥቂቱ የጠቀስናቸ
ውን የመቃብር ላይ ጽሑፎች በዚህ ጽሑፍ እናጠቃልላለን «የእግ
ዚአብሔር ባለሟልነትህን አሁን ያረጋገጥህ ነህና በፊቱ ለመቆም
ስለማይቻለኝ ስለእኔ ጸልይልኝ በአንተ ምልጃ ጌታ ኃጢአቴን
ይቅር ይለኛልና»

1. ፓፕ ቅዱስ ደማስስ

# 2.3 ቅዱስ ካሌክስተስ የሦስተኛው ምዕተ ዓመት ፖፖች የመቃብር ሥፍራ /ካታኮምብ/

*«ቡሩካኑን የምትሹ ከሆነ ሁሉም በአንድነት በዚህ ተኝተዋል» በካታኮምቡ በልሳነ ላቲን ተቀርጸው ከሚገኙት ጸሑፎች ውስጥ*

የጥንቱን የአፒያን መንገድ ይዛችሁ ስትጓዙ ዘመነ ሰማዕታ ትን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየውን በቅዱስ ካሌክስተስ /Saint Callixtus/ የተሰየመውን ታላቁን ካታኮምብ ታገኛላችሁ:: በካታኮ ምቡ የተካተቱት ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት መቃብራት በዘመነ ሰማዕታት በሰማዕትነት ያለፉ ክርስቲያን ወገኖቻችንን እንድናዘክር ግድ ይሉናል:: ዝናው ከሌሎች ካታኮምቦች ይልቅ የተናኘለት ይህ ካታኮምብ ውስጥ ለውስጥ ሃያ ኪሎ ሜትር ያህል ሲረዝም፣ ከላይኛው ገጸ ምድር ወደታች ብዙ ርቆ የተቆፈረና ባለ ሦስት ወለል ነው:: በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከአላውያን ነገሥታት ጋር የተጋደሉና በሰማዕትነት ያለፉ ፖፖች[1] ኤጲስ ቆጶሳት[2] መቃብራት /Crypts/ በዚህ ይገኛሉ::

ለሃያ ዓመታት ያህል ይህን ካታኮምብ ያስተዳደረውና በሰ ማዕትነት ያለፈው ፖፕ ቅዱስ ካሌክስተስ የቄሳሮች ዛቻ ሳይበግ ራቸው አንገታቸውን ለሰይፍ ሥጋቸውን ለእሳት መቃጠል አሳል ፈው የሰጡ ክርስቲያኖችን ሥጋ በዚህ ቦታ በክብር እንዲያርፍ ያደረገው ጥረትና ተጋድሎ በታሪክ ተከትቦ ሲዘከር ይኖራል:: ይህ ቅዱስ አባት በባርነት ሥር ከነበሩ ቤተሰቦች የተወለደ በመሆኑ በሳርዲኒያ የማዕድን ማውጫ ነፃነቱን እስካገኘበት ቀን ድረስ እጅግ አድካሚና አሰልቺ በሆነ የጉልበት ሥራ ተወጥሮ ይኖር ነበር:: ነፃነቱን ከተጎናጸፈ በኋላ ግን ዲቁና ተቀብሎ ፖፕ ቅዱስ ዜፋሪነስ /Pope St. Zephyrinus/ እስከሞተበት ቀን ድረስ የእርሱ ረዳት በመሆን አገልግሏል:: ኋላም ፖፕ እንዲሆን በመመረጡ የቀደሙት አባቶቹ ዕጣ ለእርሱም ደርሶት በሰማዕትነት እስካለፈባት ዕለት ድረስ ለአምስት ዓመታት /215-222 ዓ.ም./ በፖፕነት አገልግሏል::

1. Popes
2. Bishops



www.ethiopianorthodox.org



በዚህ ቅዱስ አባት ስም በተሰየመው ካታኮምብ የሚከተሉት ፖፖች መቃብራት ይገኛሉ::

<u>ቅዱስ ፓንቲአነስ</u> /St. Pontianus/ /ከ230 - 235 ዓ.ም/:- ሮማዊ ሲሆን በንጉሠ ነገሥት ማክሲሚነስ ተወንጅሎ በሳርዲያን የማዕድን ማውጫ እረፍት በሌለው የጉልበት ሥራ እንዲደክም ከተደረገ በኋላ በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድሏል:: ይህ ሰማዕት አባት በኃይል ከመንበሩ በተወሰደ ጊዜ አስቸጋሪ ሁኔታ በሮማ በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ላይ ደርሶ ነበር::

<u>ቅዱስ አንተርስ</u> /St. Antherus/ /ከ235 - 236 ዓ.ም/:-በትው ልድ ግሪካዊ ሲሆን የማይለወጥና የማይናወጸውን የእግዚአብሔር መንግሥት በአላውያን ፊት እየመሰከረ ለአርባ ሦስት ቀናት ያህል በእሥር ከቆየ በኋላ በሰማዕትነት ያለፈ ቅዱስ አባት ነው::

<u>ቅዱስ ፋብያን</u> /St. Fabian/ /236 - 250 ዓ.ም/:- ሮማዊ ሲሆን ዳክዮስ /Decius/ የተባለው ቄሳር በትረ ሥልጣኑን በጨበጠ ማግሥት ከባለሟሎቹ ጋር መክሮ በክርስቲያኖች ላይ እንዲህ የሚል አዋጅ አወጀ «በሮማ ግዛት በሮማዊ ዜግነት የሚኖሩ ክርስቲያኖች ሁሉ በሮማ ባሕል መሠረት የሮማ መንግሥት ሕጋዊ ነው ብሎ የተቀበለውንና ነገሥታቱም ሲያመልኳቸው የኖሩትን ጣዖታት በግዴታ እንዲያመልኩና መባዕ እንዲያቀርቡ» ይህን አዋጅ የሰሙት ክርስቲያኖች ከሃይማኖታዊ አቋማቸው ሳይናወጹ ለጣዖታት አንንበረከክም በማለታቸው የንጉሡን አዋጅ ባለማክበራ ቸው ከሊቅ እስከ ደቂቅ ባሉት ክርስቲያኖች ላይ አሠቃቂ የሞት ቅጣት ታዘዘባቸው:: ፖፕ ቅዱስ ፋብያን በዙሪያው ያሉትን ክርስ ቲያኖች በዓላማቸው እንዲጸኑ ሞትን ተሰቅቀው ወደ ኋላ እንዳያ ፈገፍጉ በቃለ እግዚአብሔር እያጽናና እርሱም የሰማዕትነትን ጽዋ ጨልጧል::

<u>ቅዱስ ሉኪስ ቀዳማዊ</u> /St. Lucius I/:- የትውልድ ቦታው በሮማ ሲሆን በፓፓነት የቆየው ለዘጠኝ ወራት ያህል ብቻ ነው /ከ253-254 ዓ.ም./ መላ የፓፓነት ዘመኑን በግዞት ነው ያሳለፈው::

<u>ቅዱስ እስጢፋኖስ ቀዳማዊ</u> /St. Stephen I/ /ከ254 - 257 ዓ.ም./:- በትውልድ ሮማዊ::

<u>ቅዱስ ሴክስተስ ዳግማዊ</u> /St. Sixtus II/ /ከ257 - 258 ዓ.ም/:- ይህ ቅዱስ አባት በትውልድ ግሪካዊ ሲሆን በቫለሪያን ዘመነ መንግሥት በክርስቲያኖች ላይ የእልቂት አዋጅ በታወጀ ጊዜ ከሌሎች አራት ዲያቆናት ጋር በነሐሴ 6 ቀን 258 ዓ.ም. አንገቱን በሰይፉ ተቀልቶ በሰማዕትነት ያለፈ ነው::

<u>ቅዱስ ዲዮናስዮስ</u> /St. Dionysius/ /ከ259 - 268 ዓ.ም./:- የዚህ ቅዱስ አባት የትውልድ ስፍራ በወል አይታወቅም:: በቫለሪያን የእልቂት አዋጅ ተዳክማ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን እንድትጠናከር ከፍተኛ ጥረት ያደረገ አባት መሆኑ ይነገርለታል::

<u>ቅዱስ ፊሊክስ ቀዳማዊ</u> /St. Felix I/ /ከ269 - 274 ዓ.ም./:- ከቅዱስ ዲዮናስዮስ በኋላ በሮማ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን በአባትነት የመራ ሲሆን፣ በትውልዱ ሮማዊ ነው::

<u>ቅዱስ ዩቲችያን</u> /St. Eutychian/ /ከ275 - 283 ዓ.ም/:- በቅዱስ ካሌክስተስ ካታኮምብ የተቀበረ የመጨረሻ ዘጠነኛው ፓፕ ነው:: ዲዮቅልጥያኖስ ከመመረጡ /284 ዓ.ም./:- ከአንድ ዓመት በፊት ነበር የሞተው::

ከላይ ከተጠቀሱት ዘጠኙ ፖፖች በተጨማሪ ሌሎችም ፖፖች በዚህ ካታኮምብ የተቀበሩ ሲሆን የሚከተሉት መቃብራት /Crypts/ ከዝነኞቹ መካከል ናቸው::

<u>የቅዱስ ጋዮስ</u> /St. Gaius/ መቃብር /Crypt/ /ከ283 - 296 ዓ.ም/:- የዚህ ቅዱስ አባት መሠረቱ /ምንጩ/ ከድልማጥያ የአሁንዋ ክሮሺያ ሲሆን በዘመነ ዲዮቅልጥያኖስ የሰማዕትነትን አክሊል የተቀዳጀ ቅዱስ አባት ነው::

<u>የሰማዕቱ የፖፕ ቅዱስ አውሳብዮስ</u> መቃብር /Crypt/ /309 ዓ.ም/:- ይህ ቅዱስ አባት በሲሲሊ በግዞት ላይ ሳለ እንደሞተ ይነገራል::





## 2.4 ታላቁ ቆስጠንጢኖስ /272 - 337 ዓ.ም/

### *«ዐቃቤ ሃይማኖት ወመፍቀሬ ካህናት»*

ቤተ ክርስቲያን በኃይለኛ የመከራ ማዕበል ተውጣ በምትንገላታበት በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማብቂያ ከምዕራቡ የሮማ ክፍል የሰላም ነፋስ መንፈስ ጀመረ:: በግበበ ምድር /ካታኮምብ/ ያለችው ቤተ ክርስቲያንም አንገትዋን ወደ ውጭ ማቅናት፣ የወንጌል ዝናርዋንም መታጠቅ ጀምራለች:: ወደ ገጸ ምድር ለመውጣት::

ዛሬ የይጎዝላቪያ ግዛት በሆነችው በጥንትዋ ናይሳን በ258 ዓ.ም. የተወለደው ቆስጠንጢኖስ ወልደ እሌኒ የሟች አባቱን ሥልጣን ወርሶ በሮም ምዕራብ ክፍል በገላትያ ነገሠ:: በዚህ ወቅት የሮማ ግዛት በአራት ተከፍሎ በአራት ነገሥታት ይተዳደር ነበር:: የምዕራቡ ግዛት በቆስጠንጢኖስና በማክሲንዳዮስ፤ የምሥራቁ ግዛት ደግሞ በለኒኪዮስና በማክሲማኖስዲያስ::

ቆስጠንጢኖስ አባቱ ኮንስታንዲዮስ ምንም እንኳን አረማዊ ቢሆንም እናቱ ዕሌኒ ግን ክርስቲያን ነበረች:: ንግሥት ዕሌኒ በልጅዋ ቆስጠንጢኖስ የልቡና ሰሌዳ ላይ የክርስትና ሃይማኖት ከልጅነቱ ጀምሮ እንዲሳል ማድረግዋ ከቆስጠንጢኖስ የኋላ ድርጊት የምንገነዘበው ነው::

ቆስጠንጢኖስ የቤተ ክርስቲያን ጠበቃነቱን ያሳየው ወደ መንበረ ሥልጣኑ ከወጣበት ማግሥት ጀምሮ ሲሆን በተለይ ደግሞ በባላንጣው ማክሲንዲዮስ ላይ በመስቀል አማካይነት ያገኘው ድል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል::

በ312 ዓ.ም ቆስጠንጢኖስና ማክሲንዲዮስ ለጦርነት ተፋላጉ:: ቆስጠንጢኖስ ወደ ጦር ሜዳ ለመዝመተ በጉዞ ላይ ሳለ «በዚህ ድል ታደርጋለህ» የሚል በመስቀለኛ ቅርጽ የተጻፈ ጽሑፍ በጠፈረ ሰማይ አየ:: በዚህ እየተመራ ሔዶ ከማክሲንድዮስ ጋር ጦርነት ገጠመ:: በጦርነቱም በለስ ቀንቶት ድል አደረገ:: ንጉሥ ማክሲንዲዮስ በጦርነቱ ላይ ስለሞተ ቆስጠንጢኖስ የማክሲንዲዮስ ግዛት የነበረውን ጠቅሎ በመያዝ አውግስጦስ ተባለ::[1]

1. አጼ እንደ ማለት ነው::

www.ethiopianorthodox.org

ምንም እንኳን ቆስጠንጢኖስ ክርስቲያን ከሆነችው እናቱ
ስለ ክርስትና የተማረና ያወቀ ቢሆንም ወደ ጦር ሜዳ ሲሄድ
በተአምር ያየው ትእምርተ መስቀልና ያስገኘለትም ድል ስለክርስ
ትና የበለጠ ጠልቆ እንዲያስብና ክርስቲያኖችንም እንዲወድ አድ
ርጎታል:: ሠራዊቱም በፈረሱ አንገት፣ በጋሻው እምብርት መስቀ
ላዊ ቅርጽ እንዲያደርግ አወጀ:: ከዚያን ጊዜ በኋላ የቆስጠንጢኖስ
ጦር ሠራዊት የሚለየው በመስቀሉ ነበር::

በ313 ዓ.ም ሊኪኒዮስ ባላንጣው ማክሲሚናስድያስን አባሮ
ምሥራቁን የሮም ግዛት ለብቻው ያዘ:: ወዲያውም የቆስጠንጢ
ኖስን እህት አገባና ዝምድናን መሠረተ:: ከዲዮቅልጥያኖስ ጀምሮ
ለአራት ተከፍላ ትገዛ የነበረችውን ሮም በሁለቱ ማለትም ምሥራቁ
በሊኪኒዮስ ምዕራቡ ደግሞ በቆስጠንጢኖስ ትገዛ ጀመር:: ቆስጠ
ንጢኖስም የክርስቲያኖችን ነፃነትና መብት የሚያስከብር ውል
ከሊኪኒዮስ ጋር በሚላኖ ቢፈጽምም ብዙም ሳይቆይ ሊኪኒዮስ
ውሉን በማፍረሱ የተነሣ ወደ ጦርነት አምርተው በውጊያው
ቆስጠንጢኖስ አሸንፎ የምሥራቁን ግዛት ጠቅሎ በመያዝ ለአርባ
ዓመት ያህል ከአራት ተከፍላ ትገዛ የነበረችው የሮም ግዛት በአንድ
በቆስጠንጢኖስ ሥልጣን ሥር ሆነች:: ቆስጠንጢኖስ የመንግሥቱን
ሥልጣን አንድ አድርጎ በያዘ ጊዜ በክርስቲያኖች ላይ ይፈጸም
የነበረው ግፍ በጣም ተቀነሰ:: ለቤተ ክርስቲያንም ሙሉ ያስተዳ
ደርና ትምህርቷን የማስፋፋት ነጻነት ተሰጣት::

ቆስጠንጢኖስ ለቤተ ክርስቲያን ከሰጣቸው መብቶች የሚከ
ተሉት ዋናዎቹ ናቸው::

1. ከግብር ነጻ እንድትሆን
2. ከመንግሥት ገቢ ሁሉ ድርሻ እንዲኖራት
3. ዕለተ እሑድ የክርስቲያኖች የበዓል ቀን እንድትሆንና በንጉሠ
   ነገሥቱ ግዛት ውስጥ ሁሉ ሥራ እንዳይሠራባት
4. ማንኛውም ክርስቲያን ንብረቱን ለቤተ ክርስቲያን ማውረስ
   እንደሚችል ቤተ ክርስቲያንም የመውረስ መብት እንዳላት
5. በክርስቲያናት መካከል ለሚፈጠሩ አንዳንድ አለመግባባት ወን
   ጀል ነክ ላልሆነ ጉዳይ ኤጲስ ቆጶሳት መዳኘት እንደሚችሉ::





ቆስጠንጢኖስ በእናቱ አማካይነት የክርስትናን ትምህርት
ቢቀበልም በይፋ ተጠምቆ ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና ያገኘው
ለሞት በቀረበበት ጊዜ ነው ያጠመቀውም የኒቆሚዲያ ኤጲስ
ቆጶስ አውሳብዮስ ነበር:: ለቤተ ክርስቲያን ብዙ ውለታ የዋለላት
ታላቁ ቆስጠንጢኖስ በተወለደ በ65 ዓመቱ በ337 ዓ.ም አርፏል::
ቆስጠንጢኖስ ጥምቀትን እስከ ዕለተ ሞቱ ያዘገየበት ለምንድር
ነው? ለሚለው ጥያቄ ለቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አስተያየታቸውን
ሲሰጡ በዚያን ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች ኃጢአት በጥምቀት
ከተሠረየ በኋላ ሁለተኛ ኃጢአት ቢሠሩ አይሠረይም የሚል
እምነትና ትምህርት ስለነበራቸው ከተጠመቁና ክርስቲያን ከተባሉ
በኋላ ኃጢአት እንዳይሠሩ ወደ ኃጢአት እንዳይመለሱ በመፍራት
ይጠመቁ የነበሩት ካረጁና ካፈጁ በኋላ እንዲያውም በሞት ጻእር
ላይ በሚገኙበት ቅጽበት ነበር:: ቆስጠንጢኖስም ጥምቀቱን
ያዘገየው በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ብለዋል::[1]

1. የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ 46::



www.ethiopianorthodox.org

በመሆንዋና አማካይ ቦታም በመሆኗ ነበር::

በ325 ዓ.ም. በኒቂያ በተካሔደው ጉባኤ ላይ የሃይማኖት ውሳኔ የሚሰጥበት ስለነበር እንደ ሐዋርያት ጉባኤ ኤጲስ ቆጶሳት ብቻ አልነበሩም የታደሙት የግሪክ ፈላስፎችና አርጌንሳውያን የአርዮስ ደጋፊዎችም እንዳያሙ በብዛት ተጠርተው መጥተው እን ደነበር ሶዞሜን የተባለው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ ጽፏል:: ጉባኤውን በሊቀ መንበርነት እንዲመሩ የተመረጡት ሦስት ሰዎች ሲሆኑ እነርሱም ሁለቱ ሊቃነ ጳጳሳት እለ እስክንድሮስና የአንጾኪ ያው ኤዎስጣቴዎስ ናቸው:: ሦስተኛው ደግሞ በመጀመሪያ የንጉሡ መልእክተኛ ሆኖ ወደ እስክንድርያ ሔዶ የነበረው የእስጳኝ ኤጲስ ቆጶስ አስዮስ ነው::

ጉባኤውን በንግግር የከፈተው ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ሲሆን ለጉባኤው ተሳታፊዎች የሚከተለውን መልእክት አስተላልፎ ነበር «ወዳጆቼ ዛሬ ከእናንተ ጋር መገኘቴ ከምመኛቸው ታላላቅ ምኞ ቶች አንዱ ነው:: በእናንተ በቅዱሳን አባቶች መካከል ለመገኘት ስላበቃኝ ከሁሉ በላይ የኾነውን ንጉሥ አመሰግነዋለሁ... አሁንም አባቶቼን አደራ የምለው በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ድል የተነሣው ረኩስ መንፈስ በአንዳንድ ምክንያት ደስታችንን እንዳያ ፈርሰውና ድፍረትን በተመላ ርካሽ አነጋገር አምላካዊውን ሕግ እንዳያፈርሰው ነው... አባቶቼ ከማንኛውም የውጭ ጦርነት ይልቅ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የሚደረገው የእርስ በእርስ ጦረነት የከፋ ነው:: በውጭ ከሚደረገው ጦርነት ይልቅ እጅግ የመረረ ነው:: አዲስ ችግር በመካከላችሁ መፈጠሩን ስለሰማሁ በነገሩ ብት ወያዩበት አይከፋም በማለት ያለምንም መዘግየት እንድትሰባሰቡ አደረግሁ የእግዚአብሔር አገልጋዮች አባቶቼ ሆይ መለያየትን ለማጥፋት ዛሬ ነገ አትበሉ:: ለዚህ አደራዬ ጥብቅ ነው»

ጉባኤው «ወልድ ፍጡር ነው» በማለት አርዮስ ያቀረባቸውን ጥቅሶች መረመረ:: ወልድ በባሕርዩ ፍጡር ከሆነ በመዳን ምሥጢ ር ላይ ስለሚያመጣው አደጋ፤ ወልድ ፍጡር ሳለ እንደ ሌሎቹ ፍጡራን በገደል በትሩፋት የአምላክነትን ክብር አገኘ ስለማለቱ ሁሉ ተገቢና አሳማኝ የሆነ መልስ ከመጽሐፍ ቅዱስ እየጠቀሰ ቅዱስ አትናቴዎስ ስለመለሰለት ጉባኤው በሐዋርያት አድሮ ያስተማረ መንፈስ ቅዱስ ዛሬም በአትናቴዎስ አድሮ እውነትን





መሰከረ በማለት አርዮስ ከክህደቱ ተመልሶ ወልድ የባሕርይ አምላክ መሆኑን አምኖ እንዲቀበል ጠየቀው:: እርሱ ግን አሻፈረኝ በማለቱ 318 ሊቃውንት እንደ አንድ ሰው ሆነው በአንድ ድምፅ አውገዘው ከቤተ ክርስቲያን ለዩት:: ቆስጠንጢኖስ ደግሞ ግዞት ፈረደበት:: ኋላም ሆድ ዕቃው ተዘርግፎ ሞተ:: አሟሟቱም የመ ቀሰፍት በመሆኑ አርቶዶክሳውያን በአርዮሳውያን ላይ የተጎናጸፉት ድል መሆኑ ይነገራል::

አርቶዶክስ የሚለው ስያሜ ለእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን መጠሪያ ሆኖ የተሰየመው በጉባኤ ኒቂያ ነው:: ቃሉ ግሪክኛ ሲሆን ትርጉሙም ቀጥተኛ /እውነተኛ/ ሃይማኖት ማለት ነው:: የአርዮስን ትምህርት የተከተሉ ደግሞ አርዮሳውያን ተባሉ::

## 3.3 ጉባኤ ቁስጥንጥንያ /381 ዓ.ም./

ቁስጥንጥንያ[1] የሮማ ኢምፓየር ሌላዋ መናገሻ ከተማ የሆነ ችው በቀዳማዊ ቆስጠንጢኖስ የመጨረሻዎቹ የሥልጣን ዘመናት ነው::[2] ቆስጠንጢኖስ ለቤተ ክርስቲያን በዋለው ውለታ መሠረት ለእርሱ ሲባል የኤፌሶን ወንበር ወደ ቁስጥንጥንያ በመዞሩ የሮማ ውና የቁስጥንጥንያው የመናገሻ ከተማዎች ሊቃነ ጳጳሳት እኔ እበ ልጥ እኔ እበልጥ እያሉ በሥልጣን ይሻኮቱ ነበር:: መንፈቀ አርዮሳ ውያን ደግሞ ቁስጥንጥንያን መናኸሪያቸው አድርገዋት ነበር:: አርዮሳውያን ገንነው ቁስጥንጥንያን ባጥለቀለቁበት ሰዓት ቁጥሩ ከመንፈቀ አርዮሳውያን የሆነው መቅዶንዮስ የቁስጥንጥንያን መን በር ይዞ ነበር:: ይህ መቅዶንዮስ ከሥላሴ አንዱ የሆነው መንፈሰ ቅዱስ ፍጡር ነው:: እያለ ያስተምር ነበር:: ሌላው መናፍቅ አቡሊ ናርዮስ የተባለው ደግሞ «ወልድ ሰው በሆነ ጊዜ ሥጋን እንጂ ነፍስን አልተዋሐደም ስለ ነፍስ በነፍስ ፈንታ መለኮት ለሥጋ ነፍስ ሆነው» የሚለውን ኑፋቄ ይነዛ ነበር:: «የእግዚአብሔር ልጅ የተዋሐደው የአዳምን ሥጋ አይደለም ሌላ በቅድምና የነበረ ሥጋ ነው» የሚሉ መናፍቃንም ቤተ ክርስቲያንን ያውኳት ነበር::

1. Constantinopie
2. The Colosseum P. 10



www.ethiopianorthodox.org

በመቅዶንዮስና በሌሎቹ መናፍቃን ትምህርት እየታወከች ያለችው ቤተ ክርስቲያን የተቃውሞ ደወሏን ባስተጋባች ጊዜ የወቅቱ የቁስጥንጥንያ ንጉሥ ቴዎዶስዮስ ቀዳማዊ ይህን የቤተ ክርስቲያን ችግር የሚፈታ ጉባኤ በቁስጥንጥንያ እንዲደረግ ለቤተ ክርስቲያን አባቶች መልእክት አስተላለፈ:: በ381 ዓ.ም. ከየቦታው የተሰባሰቡ አንድ መቶ ሃምሳ ኤጲስ ቆጶሳት በቁስጥንጥንያ ተሰበ ሰቡ:: የዚህ ጉባኤ ሊቃነ መናብርት የነበሩትም ጎርጎርዮስ ዘእንዚ ናዙና ጢሞቴዎስ ዘአልቦ ጥሪት[1] ናቸው::

ጉባኤው የመቅዶንዮስንና የአቡሊናርዮስን እንዲሁም የሌ ሎች መናፍቀንን ትምህርት ካዳመጠ በኋላ በሥላሴ ዘንድ መበላ ለጥ እንደሌለ መንፈስ ቅዱስ የባሕርይ አምላክ መሆኑን የቅዱሳት መጻሕፍትን ማስረጃ መሠረት በማድረግ የመቅዶንዮስን ትምህርት አውግዟል:: እግዚአብሔር ወልድ ከድንግል ማርያም ሥጋን ብቻ እንጂ ነፍስን አልነሳም ለሚለው የአቡሊናርዮስ ክህደት ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ሲመልስ «ሰው የሚባለው ነፍስና ሥጋ ነው:: መለኮት ሥጋ ሆኖ ሰውን አዳነ ማለትም ነፍስንም ሥጋንም ተዋሕዶ ነፍስ ንም ሥጋንም አዳነ ማለት ነው:: ሥጋ እንጂ ነፍስ አልነሳም /አልተዋሐደም/ ከተባለማ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ያልተዋሐደ ውን አላዳነውም የሰው ሥጋው እንጂ ነፍሱ አልዳነም ማለት ይሆናል» በማለት የአቡሊናርዮስን የክህደት መውጊያ ሰብሮ ጥሎ ታል:: በዚህ ጉባኤ አቡሊናርዮስም ተወግዟል:: ጉባኤው ጌታ የተ ዋሐደው የአዳምን ሥጋ አይደለም ሌላ በቅድምና የነበረ ሥጋ ነው የሚሉትን መናፍቀንንም አውግዟል:: ይህ ከግኖስቲኮች የተወረሰውን አስተሳሰብ አቡሊናርዮስ «ሥጋ በቅድምና ነበር ባሕርዩን አግዝፎ ታየ እንጂ» ብሎ ያስተምር እንደነበር ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ገልጾአል::

1. 22ኛው የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ



## 3.4 ጉባኤ ኤፌሶን /431 ዓ.ም./

ከተመሠረተች ጀምሮ የሃይማኖት ውዝግብ ያልተለያት ቁስጥንጥንያ፣ በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሊቀ ጳጳስዋ ንስጥሮስ ባፈለቀው የክህደት ትምህርት ታውካ ነበር:: ንስጥሮስ የአንጾኪያ ተወላጅ የሆነው የጠርሴሱ ኤጲስ ቆጶስ የዲያድርስ ተማሪ ሲሆን ከቤተ ክርስቲያን በውግዘት ያስለየውን ትምህርት ያገኘው ከመምህሩ ከዲያድርስ ነው:: በ427 ዓ.ም. የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ በተሾመ ጊዜ የክህደት ትምህርቱን የቤተ ክርስቲ ያን ትምህርት አስመስሎ ወደ ቤተ ክርስቲያን አሾልኮ ለማስገባት አመቺ ጊዜ ያገኘ መስሎት «ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ አለው:: ከማርያም የተወለደው ዕሩቅ ብእሲ ነው:: ቃል በጥምቀት በዮርዳኖስ እስኪያድርበት ድረስ ወልደ ማርያም የቃል ማደሪያ ለመኾን ተወለደ:: ወይም ውሃ በቦይ እንደሚያልፍ ቃል በማሕፀነ ማርያም አለፈ:: ስለዚህ ማርያም ወላዲተ ሰብእ ናት እንጂ ወላዲተ አምላክ አትባልም» እያለ በየደረሰበት ያስተምር ነበር::

ይህ የንስጥሮስ የኅድረት ትምህርት ከቁስጥንጥንያ አልፎ እስክንድርያ በመድረሱ የእስክንድርያ በተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ቅዱስ ቄርሎስ ኹል ጊዜ የበዐላትን መዋያ ቀናት የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ እንዲያውጅ የሠለስቱ ምእት ቀኖና በሚያዘው መሠረት የትንሣኤን በዓል መልእክት ሲያስተላልፍ የንስጥሮስ የክህደት ትምህርት በተባራሪ ደርሶት ስለነበር «ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ናት» የሚል ንባብ ያለበት መልእክት ጨምሮ አስተላለፈ:: ምንም እንኳን ቅዱስ ቄርሎስ የንስጥሮስን ስም ባያነሳም ንስጥሮስ ለእርሱ ትምህርት የተሰጠ የአጸፋ መልስ መሆኑ ስለገባው «ማር ያም ወላዲተ አምላክ አይደለችም» የሚል መልስ ወደ ቅዱስ ቄር ሎስ ላከ:: በዚህ ጊዜ ቅዱስ ቄርሎስ በሁኔታው አዝኖ የቀደሙት አባቶች ያላስተማሩትን እንግዳ ትምህርት ማስተማር የቤተ ክርስ ቲያን ሰላም የሚያናጋ መሆኑን ገልጾ ከስህተቱ እንዲታረም ጻፈለት::

ንስጥሮስ ግን የቅዱስ ቄርሎስን ምክር ከምንም ሳይቆጥር ይባስ ብሎ የሚያስተምረውን የኅድረት /የሁለት አካል ሁለት

www.ethiopianorthodox.org

ባሕርይ ትምህርቱን/ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለማስመሰል ለትምህርቴ ያግዙኛል ብሎ ከመጽሐፍ ቅዱስ ያሰባሰባቸውን ጥቅሶች ጽፎ ለቅዱስ ቄርሎስ ላከለት። ቅዱስ ቄርሎስም ለሁለተኛ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት ተቀብላ ይዛው የኖረችውን የምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት ጽፎ ይልክለታል። ንስጥሮስ ግን በክህደቱ ጸና። ቅዱስ ቄርሎስም ምክሩና ማባበሉ ውጤት እንዳላስገኘ ስላየ ለሦስተኛ ጊዜ 12 አንቀጽ ያለውን በተዋሕዶ ትምህርት ላይ ውሳጤን፣ ቱስሕትን፣ ኀድረተን ቡዓዴን የሚያስተምሩ መናፍቃንን የሚያወግዝ መልእክት ላከ። ይህ መልእክት ለንስጥሮስ ከመድረሱ ከ11 ቀን በፊት ንጉሡ ቴዎዶስዮስ የነገሩ መባባስ ስላሰጋው ጉባኤ ተሠርቶ በጉባኤ እንዲታይ አዋጅ ነግሮ ነበር።

ጉባኤው በኤፌሶን እንዲደረግ በተወሰነው መሠረት በጉባኤው ላይ ለመገኘት ንስጥሮስ 16 ግብረ አበሮቹን ኤጲስ ቆጶሳት ይዞ በቁስጥንጥንያ ቤተ መንግሥት ወታደሮች ታጅቦ ኤፌሶን ገባ። ቅዱስ ቄርሎስም ከእስክንድርያ ሊቀ ዲያቆኑን ዲዮስቆሮስንና ሌሎች ሃምሳ ኤጲስ ቆጶሳትን አስከትሎ ኤፌሶን ደረሰ። የአንጾኪያው ሊቀ ጳጳስ ዮሐንስ በሥሩ የሚገኙትን ኤጲስ ቆጶሳት ይዞ እንዲመጣ ተጠርቶ ነበር። ነገር ግን የንስጥሮስ ደጋፊ ስለነበር በሰዓቱ አልመጣም። እሱ እስኪመጣ ድረስ ሁለት ሳምንት ሙሉ ተጠበቀ ልዩ ልዩ ምክንያት እየፈጠረና መልእክተኛ እየላከ ብዙ ቀን ቢጠበቅም ሊመጣ አልቻለም።

ጉባኤው በ431 ዓ.ም. በኤፌሶን ሲደረግ በጉባኤው መጀመሪያ ቀን ንስጥሮስ ወደ ጉባኤው ቀርቦ ሐሳቡን ገልጦ እንዲናገር ቢጠየቅ ጉባኤው በሙሉ ካልተሰበሰበ አልቀርብም አለ። በጉባኤው ተጠብቆ ሳይመጣ የቀረው ጓደኛው ዮሐንስ ዘአንጾኪያ ብቻ ነበር። የዮሐንስ መቅረትም በምክር የተደረገ ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት አለ። ጉባኤው ንስጥሮስ ባይገኝም መጀመር እንዳለበት ተወሰነ። ቅዱስ ቄርሎስ የጉባኤው ሊቀ መንበር እንዲሆን ጉባኤው መርጠው በጉባኤው መጀመሪያ ቀን ንስጥሮስ የጻፋቸው የክህደት ትምህርቱን የያዙ ደብዳቤዎች ቀርበው ተነበቡ። ከዚያም ቅዱስ ቄርሎስ የንስጥሮስን ክህደት በማጋለጥ የጻፋቸው ደብዳቤዎች አሥራ ሁለት የውግዘት አንቀጾችን የያዘ መልእክት አንድ በአንድ ለጉባኤው ቀርበው ተነበቡ። የንስጥሮስ ትምህርት ከቤተ ክርስቲያን



www.ethiopianorthodox.org



ትምህርት የወጣ መሆኑ በጉባኤው ተረጋገጠ። የቅዱስ ቄርሎስ መልእክት ግን ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከቅዱሳን አበው ትምህርት ጋር አንድ ሆነው ስለተገኙ 200 ሊቃውንት ያሉበት የኤፌሶን ጉባኤ በአንድ ድምፅ ተቀበላቸው። የንስጥሮስን የሁለት ባሕርይ ትምህርትም በጽኑ አወገዘ። ከድንግል ማርያም የተወለደው ራሱ አምላክ መሆኑን በማረጋገጥ ድንግል ማርያም በአማን ወላዲተ አምላክ /ቴዎቶኮስ/ መሆንዋን በአንድ ድምፅ ወሰነ።

ከቤተ ክርስቲያን አንድነት ተለይቶ የተወገዘው ንስጥሮስ በ435 ዓ.ም. ወደ ግብፅ ሔዶ በአክሚም ይኖር ነበር። ከዚያም 16 ዓመት ቆይቶ በ451 ዓ.ም. ሞተ። ክህደቱ ግን አልሞተም።

## 3.5 ጉባኤ ኬልቄዶን

ምንም እንኳን ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የኑፋቄ ትምህርት አንግበው አያሌ መናፍቃን ቢነሱም ቀደምት የቤተክርስቲያን አበው ጉባኤ ዘርግተው መናፍቃንን በጉባኤ ተከራክረው በመርታት መናፍቃንን ከኑፋቄያቸው ጋር አንድ መንፈስ ሆነው በማውገዝ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ጠብቀው ኖረዋል። በ451 ዓ.ም. በጉባኤ ኬልቄዶን የተነጸባረቀው የኑፋቄ ነጸብራቅ ግን የቤተ ክርስቲያን አባላትን ለሁለት ጎራ ከፍሎ ያለፈ ነው። በምዕራብና በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የጸብ መጋረጃ የተጋረደው ከዚሁ ከጉባኤ ኬልቄዶን በኋላ ነው። እስከ ጉባኤ ኬልቄዶን ድረስ ቤተ ክርስቲያን በጉባኤ ኒቂያ ሠለስቱ ምዕት በወሰኑት ውሳኔ መሠረት በአራቱ መንበሮች ላይ በሚሰየሙት አባቶች ትመራ ነበር። እነዚህም፡

1ኛ. በቅዱስ ጴጥሮስ መንበር በሚቀመጠው የሮም ሊቀ ጳጳስ
2ኛ. በቅዱስ ማርቆስ መንበር በሚቀመጠው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ
3ኛ. በቅዱስ ጴጥሮስ መንበር በሚቀመጠው የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ
4ኛ. በቅዱስ ዮሐንስ መንበር በሚቀመጠው የኤፌሶን ሊቀ ጳጳስ ኋላ ላይ ለቆስጠንጢኖስ ሲባል የኤፌሶን መንበር ወደ ቁስጥንጥንያ ተዛውሯል።

ከጉባኤ ኬልቄዶን በፊት የተካሔዱት ዓለም አቀፍ የቤተ
ከጉባኤ ኬልቄዶን በፊት የተካሔዱት ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት ማለትም፡ ጉባኤ ኒቂያ /325 ዓ.ም/፣ ጉባኤ ቁስጥንጥንያ /381 ዓ.ም./ና ጉባኤ ኤፌሶን /431 ዓ.ም./ ከላይ በተ ገለጸው መሠረት ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናት /አባቶች/ በአካል ወይም በተወካይ የተሳተፉባቸውና እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንደአንድ ልብ መካሪ ሆነው ውሳኔ ያሳለፉባቸው ናቸው፡፡ በጉባኤ ኬልቄዶን ግን ተወጋግዘው የተለያዩበተ ነበር፡፡ የዚህም ምክንያት በጉባኤ ኤፌሶን /431 ዓ.ም/ በነበሩ አባቶች ተወግዞ ግብአተ መሬቱ የተፈጸመለት የንስጥሮስ ክህደት በሮሙ ፓፕ በልዮን አማካይነት ትንሣኤ አግኝቶ በኬልቄዶን ጉባኤ በመቆሙ የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን አባቶች በመቃወማቸውና የንስጥሮስ የሁለት ባሕርይ ትምህርት የሰፈረበትን የልዮን ጦማር ባለመቀበላቸው የተነሣ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ጉዞ መጥፎ ጠባሳ ጥሎ ያለፈው ይህ ታሪካዊ ክስተት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የሮማ ነገሥታት አረመኔ
ቅድመ ቆስጠንጢኖስ የነበሩ የሮማ ነገሥታት አረመኔ ከመሆናቸው የተነሣ ቤተ ክርስቲያንን ከገጸ ምድር ለማጥፋት ለዓይናቸው እንቅልፍ የነፈጉ ነበሩ፡፡ ድኅረ ቆስጠንጢኖስ የተነሱት ደግሞ ሁለት ዓይነት መልክ ነበራቸው ክርስቲያን ነን ሲሉ የአሕዛብነትም ጠባይ ይንፀባረቅባቸው ነበር፡፡ ውዳሴ ከንቱን በመሻት በቤተ ክርስቲያን የውስጥ አሠራር ጣልቃ እየገቡ፣ ሲላቸው ዶግማ ዋን በማፋለስ ከሐሳባቸው ጋር የሚስማማውን የቤተ ክርስቲያን አባት በመሾም ሐሳባቸውን የሚቃረነውን በማሰር፣ በማጋዝ ብሎም በመግደል ከዚያም ባለፈ ቀጥለን እንደምናየው ዓለም አቀፋዊ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ እንዲካሔድ በማስገደድ በቤተ ክርስቲያን ላይ በሚፈጽሙት የጀብዱ ሥራ የሚኩራሩ ዓይነት ነበሩ፡፡

እስከ ጉባኤ ኤፌሶን የነበሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ይህን የነገሥታቱን ጣልቃ ገብነት በቆራጥነት መንፈስ ተቋቁመው የቤተ ክርስቲያን ዶግማ ሳይፋለስ አንድነትዋም ሳይናጋ ያቆዩ ቢሆንም ከጉባኤ ኤፌሶን በኋላ በተለይ በሮም መንበር ላይ የተሰየመው ፓፓ ልዮን ቀዳማዊ የነገሥታቱ ፈቃድ ፈጻሚ በመሆን ለመለያየት ምክንያት ሆኗል፡፡

በጉባኤ ኤፌሶን ንስጥሮስ ተወግዞ ከቤተ ክርስቲያን አንድነት ከተለየ በኋላ በቁስጥንጥንያ የአንድ ገዳም አበምኔት የነበረው



www.ethiopianorthodox.org



ግሪካዊው አውጣኪ «ሥጋና መለኮት በተዋሐዱ ጊዜ መለኮት ሥጋን ውጦታል መጦታል» የሚል ክህደትን በማስተማሩ የቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ ፍላብያኖስ በሀገረ ስብከቱ ያሉትን ኤጲስ ቆጶሳት ብቻ ሰብስቦ በጉባኤ አድያም አውጣኪን አወገዘው፡፡ እንደ ቀደሙት መናፍቃን በመላው የአብያተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ፊት ቀርቦ ተጠይቆ በኑፋቄው ጸንቶ ከተገኘ መወገዝ ሲኖርበት ይህ ካለመሆኑ የተነሣ ማለትም ሌሎቹ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጉዳዩን ስላላወቁት አውጣኪ የቄርሎስን ሃይማኖት ስለመሰከርኩ በከንቱ ተወገዝኩ በማለት ለቤተ መንግሥት ይግባኝ አለ፡፡ እንደ ተለመደው በእስክንድርያ ፓትርያርክ በዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲ ያን ሲኖዶስ ጉዳዩ እንዲታይለት ንጉሡ ለእስክንድርያ ቤተ ክርስ ቲያንና ለሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት መልእክት ላከ፡፡

በ449 ዓ.ም. የአውጣኪን ጉዳይ ለማየት በኤፌሶን ጉባኤ ተደረገ፡፡ ጉባኤውን በሊቀ መንበርነት የመራው የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ነበር፡፡ የቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ ፍላብያኖስ እሱ ያወገዘው አውጣኪ ጉዳይ እንዲታይ በመወሰኑ ተናዶ በጉባኤው ላይ አልተገኘም፡፡ በጉባኤው ላይ አውጣኪ ስለ ሚያምነው እምነት ሲጠየቅ ክህደቱን በልቡ ይዞ ሃይማኖቱ እንደ ቅዱስ ቄርሎስ መሆኑን በመሐላ አረጋገጠ፡፡ በዚህ ጊዜ ጉባኤው አውጣኪን ከግዝቱ ፈትቶ በቤተ ክርስቲያን የነበረውን ሥልጣን መለሰለት፡፡

የሮሙ ፓፓ ልዮን ግን የጉባኤውን ውሳኔ እንደሰማ ጉባኤውን ነቀፈ፡፡ የጉባኤውንም ሊቀ መንበር ቅዱስ ዲዮስቆሮስን አወገዘ፡፡ ለፍላብያኖስም «ክርስቶስ ኹለት ባሕርይ ኹለት ሕላዌ አንድ አካል አለው ብለን እናምናለን» ማለትም መለኮት የመለኮትን ሥጋም የሥጋን ሥራ ይሠራል የሚል መልእክት ያዘለ ደብዳቤ ጽፎ ላከለት፡፡ ፍላብያኖስ ግን ለልዮን መልስ ሲመልስ ተጠንቅቆ የቅዱስ ቄርሎስን ትምህርት በማይቃወም ኹኔታ «ከሥጋዌ በኋላ በአንድ አካል በአንድ ከዊን ከኹለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ የኾነውን አንድ ክርስቶስን እናምናለን» በማለት መልሷል፡፡

ልዮን ለፍላብያኖስ የላከውን መልእክት ዲዮስቆሮስ በሰማ ጊዜ ንስጥሮሳዊ ነህ ብሎ ልዮንን አወገዘው፡፡ ይህን ተከትለው ላቲኖችና ግሪኮች በእስክንድርያ የቅዱስ ማርቆስ መንበር ላይ

እያሉ ሲጮሁ፤ አርቶዶክሳውያን አባቶች ማለትም ከግብጽ፣ ከሶ
ርያ፣ ከአርመንያ የመጡት በዚህ ንስጥሮሳዊ ትምህርት የማይስ
ማሙ መሆናቸውን እየገለጡ ጉባኤውን አቋርጠው ወጥተው ሔዱ።
የቤተ መንግሥቱ ባለሥልጣናት በልዮን ጦማር እንዲስማሙ ቢያ
ስፈራሯቸውም «ክርስቲያን ማንንም አይፈራም፣ ከእሳት ብትጥ
ሉንም ለምደነዋል ሰው ከተፈራ ሰማዕታት በቤተ ክርስቲያን
ባልነበሩ ነበር» በማለት በአቋማቸው ጸኑ።

የነገሥታትን ፈቃድ ለመፈጸም ታቅዶ በተዘጋጀው የኬል
ቄዶን ጉባኤ የልዮንን ጦማር አጽድቆ የቁስጥንጥንያን መንበር
ከሮም መንበር ጋር አስተካክሎ ተበተነ። ከጉባኤው በኋላ ንግሥት
ብርክልያ ቅዱስ ዲዮሰቆሮስን አስጠርታ ሐሳቡን እንዲለውጥ
በልዮን ጦማር እንዲስማማ መከረችው። እርሱ ግን ከቀናች ከእው
ነተኛ ሃይማኖቱ ፈቀቅ የማይል መሆኑን በመግለጹ ጽሕሙ እስኪ
ነጫጭና ጥርሶቹ እስኪወልቁ አስደበደበችው። እሱም መደብደቡን
በምስጋና ተቀብሎ የተነጨውን ጽሕሙንና የወለቁትን ጥርሶቹን
በአንድ ላይ ቋጥሮ «ይህ የሃይማኖት ፍሬ ነው» ብሎ በግብፅ
ለሚኖሩ ምእመናን ልኮላቸዋል። የፈቃዳቸው ተገዢ ባለመሆኑ
ብርክልያና የቁስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናት በቅዱስ
ዲዮስቆሮስ ላይ ገዞትን አወጁበት። እርሱም በተዋሕዶ ሃይማኖቱ
እንደጸና በእስር ላይ እንዳለ በ454 ዓ.ም. አረፈ። ከጉባኤ
ኬልቄዶን በኋላ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ከምዕራባውያን
ጋር ተቆራርጠው ቀሩ።

## 3.6 ከጉባኤ ኬልቄዶን ማግሥት

ክብርና ሥልጣን ከሃይማኖት በላይ የሆነባቸው የቁስጥንጥ
ንያ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናት ልዮን ንስጥሮሳዊ ትምህርቱን
እንዲያደላድል በኬልቄዶን ጉባኤ ላይ ለልዮን ጦማር ያሳዩት
አጋርነት የኋላ ኋላ ትዝብት ላይ ጥሏቸዋል። በጉባኤ ኒቂያ በስድ
ስተኛው አንቀጽ በተወሰነው መሠረት የአብያተ ክርስቲያናቱ መሪ
ዎች የማዕረግ ተራ የሮም፣ የእስክንድርያ፣ የአንጾኪያ፣ የኤፌሶን
የነበረው በግሪክ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና በቁስጥንጥንያ ነገሥ
ታት በነመርቅያን ተጽእኖ ተሽሮ የኬልቄዶን ጉባኤ ቁስጥንጥንያን



www.ethiopianorthodox.org



ሥርዋጽ በማስገባት ከሮም መንበር ጋር አስተካክሏታል። ዳሩ ግን
በተዋሕዶው አርበኛ በቅዱስ ዲዮስቆሮስ ላይ ውግዘት ለማስተላ
ለፍ፣ መከራ ለማድረስ እጅና ጓንት ሆነው የነበሩት የሮምና የቁስ
ጥንጥንያ አብያተ ክርስቲያናት ባለሥልጣኖች የክብርና የሥልጣን
ጉዳይ ስለሆነ በሃያ ስምንተኛው የኬልቄዶን ጉባኤ ውሳኔ /በኬልቄ
ዶን ጉባኤ ጸድቆ በወጣው በሃያ ስምንተኛው ሕግ ላይ መናገሻ
ከተማ ለሆነችው ለቁስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ
የአንደኝነቱን ማዕረግ በመስጠት ከሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን
ፓፓ ጋር አስተካክሎታል። የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሪ
በሽምግልና ብቻ ከመቅደሙ በስተቀር የሁለቱም አብያተ ክርስቲ
ያናት መሪዎች በማዕረግ /በክብር/ እኩል መሆናቸው ተወስኗል/
የሮሙ ፓፓ ራሱን የቤተ ክርስቲያን ራስ አድርጎ ስለሚቆጥር
መግባባት አልቻሉም። ውሳኔው በሮም ፓፓ ዘንድ ተቀባይነት
ባለማግኘቱ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ በሚል የሥልጣን ሽኩቻ
መሻኮት ቀጠሉ። የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በ1014
ዓ.ም. በፓፓ ቤኔዲክቶስ ስምንተኛ በቀኖና ሃይማኖት መንፈስ
ቅዱስን «ከአብም ከወልድም የሠረጸ ነው» /Filioque/ የሚለውን
ሥርዋጽ በማስገባትዋ ምንም እንኳን በወቅቱ የግሪክ ቤተ ክርስቲ
ያን የተቃውሞ ድምፅዋን ባታሰማም ቆይታ ቆይታ ግን በዚያ
መከረኛ የሥልጣን ሽኩቻ ከሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ጋር
እሰጥ አገባ ውስጥ ስትገባ ከአርባ ዓመት በፊት በዝምታ ያለፈ
ችውን ኑፋቄ ምክንያት በማድረግ ከሮም ቤተ ክርስቲያን ጋር
በ1054 ዓ.ም. በውግዘት ተለያይተዋል።

ከጉባኤ ኬልቄዶን በኋላ የቁስጥንጥንያ ነገሥታት የአብያተ
ክርስቲያናቱ መለያየት ሕዝቡን አንድ አድርጎ በሰላም ለመግዛት
የመሰናክል ድንጊያ ስለሆነባቸው አብያተ ክርስቲያናቱን እንደገና
ለማዋሐድ ጥረት አድርገው ነበር። ለምሳሌ ንጉሥ ዘይኑን /474 -
491 ዓ.ም./ የጉባኤ ኬልቄዶንን ውሳኔ ሽሮ ሁለቱንም ወገኖች
የሚያስማማ የማስታረቂያ ሰነድ እስከማስረቀቅ ደርሶ ነበር። ይህ
ረቂቅ የሁለት ባሕርይ እምነት ተከታይ በነበረው በቁስጥንጥንያ
ፓትርያርክ አብኪዮስና በተዋሕዶው የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን
ፓትርያርክ ጴጥሮስ ሞንጉስ አማካይነት የተረቀቀ ነበር። ረቂቁ
«ሄኖቲኮን» /አንድነት/ በመባል ይታወቃል። ረቂቁ በንጉሥ ዘይኑን

ቢጸድቅም የሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት ካህናትና ምእመናን አዎንታ /ይሁንታ/ ባለማገኘቱ ተግባራዊ ሳይሆን ቀርቷል:: በዚህ ሰነድ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ የሦስቱ ጉባኤ ውሳኔዎች የኒቂያ /325 ዓ.ም./፣ የቁስጥንጥንያ /381 ዓ.ም./፣ የኤፌሶን /431 ዓ.ም./ ተቀባይነት ተገልጸአል:: አርዮስ፣ ንስጥሮስና አውጣኪን ተወግዘ ዋል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ የባሕርይ ልጅ መሆኑ ተወ ስቷል:: ዳሩ ግን ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱ ቢወሳም በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ ወይም ሁለት ባሕርይ የሚለው ወሳኝ ጉዳይ አልተወሳም:: ለመለያየቱ ምክንያት የሆነችው የኬልቄዶን ጉባኤም አልተወገዘችም:: ሰነዱን በተመለከተ የግሪክ ካህናትና ምእመናን ባቀረቡት ቅሬታ የክርስትና እምነት በሦስቱ ጉባኤዎች ውሳኔ ብቻ መወሰኑ ለተዋሕዶዎች ያደላል ሲሉ:: ተዋሕዶዎች ደግሞ የኬልቄዶን ጉባኤ በይፋ ባለመወገዟ ለሁለት ባሕርይ እምነት አራማጆች ያደላ ነው በማለት በሁለቱም ፓትርያርኮች የተዘጋጀው ሰነድ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል:: በዚህ ዝግጅተ የተከፋው የሮም ፓፓ ፊሊክስ በ484 ዓ.ም. ሮም ውስጥ በጠራው ጉባኤ በኬልቄዶን ጉባኤ ለልዮን ጦማር መጽደቅ ተባባሪ የነበረችውን የቁስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የሆነውን አካኪያስን አወገዘው:: አካኪያስም በበኩሉ የሮሙን ፓፓ ስም ከሥርዓተ ቅዳሴው መዝገብ እንዲፋቅ አደረገ:: ከ30 ዓመት በኋላ እንደገና እርቅ ቢመሠርቱም በ1054 ዓ.ም. ከላይ በተገለጸው ሁኔታ በይፋ ተወጋግዘው ተለያይተዋል::

የአብያተ ክርስቲያናቱ ጎራ ለይቶ መናቆር የቁስጥንጥንያን ቤተ መንግሥት ያሳሰበው ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ከመቆርቆር የተነሣ ሳይሆን በተፈጠረው ክፍተት የውጭ ኃይሎች ገብተው የግዛቱን አንድነት አደጋ ላይ እንዳይጥሉት ከመሥጋት ነበር:: ስለዚህ ከዘይኑን ሞት በኋላ የቁስጥንጥንያን መንበረ መንግሥት የተቆናጠጠው ቀዳማዊ አናስታሲዮስ /491-518 ዓ.ም/ የአንድነቱ ሰነድ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ከፍተኛ ጥረት ቢያደርግም ሳይሳካ ቀርቷል:: ከእርሱም በኋላ የተነሱት ነገሥታት የበኩላቸውን ጥረት አድርገው ነበር:: ዳሩ ግን ሁለቱን ወገኖች የሚያስማማ ሁኔታ ባለመፈጠሩ ምኞት ሆኖ ቀርቷል:: እንደውም ኋላ ላይ ለሮማ ኢምፓየር መውደቅ አስተዋጽኦ አድርጓል::





መለካውያን /ሁለት ባሕርይ ባዮች/ የቁስጥንጥንያን ነገሥታት ዙፋን ተደግፈው በተዋሕዶዎች ላይ ያስፈነጥሩት የነበረው የመከራ ፍላጸ ተዋሕዶዎችን እጅግ ያስመረረና ጥላቻ ውስጥም የከተተ ስለነበረ «ሰይፌ ነበልባል ዘምድረ በዳ» በሚል የሚታወቀው የመሐመድ ሠራዊት /የዐረብ ጦር/ የቁስጥንጥንያን መንግሥት በየአቅጣጫው ከቦ በሚያስጨንቅበት ወቅት እግዚአብሔር እንባቸውን ሊያብስ በመለካውያን ላይ ያመጣው መአት መሆኑን አምነው እንደ ቀድሞው አጋርነታቸውን አላሳዩም:: እንደውም ዐረቦች ግብጽን ድል አድርገው ሲይዙ ድርጊቱን የተቀበሉት በታላቅ ደስታ ነበር::

## 3.7 የተዋሕዶ ክርስቲያኖች በእስልምና መወረር

መካ የእስልምና ብሔረ ሙላድ ናት:: ጥንተ መሠረቷን ከሚተርኩት የዐረብ ድርሳናት እንደምንገነዘበው የእምነት አባት የተባለው አብርሃም ከአጋር የወለደው እስማኤል የተባለ ልጅ ነበረው:: የአብርሃም ሚስት ሣራ እስማኤል የአብርሃም ወራሽ ይሆናል ብላ ስለሠጋች ባልዋ አብርሃምን እስማኤልን ከእናቱ ከአጋር ጋር እንዲያባርርላት ጠየቀችው:: እርሱም የሚስቱ የሣራን ቃል ተቀብሎ አጋርና ልጁ እስማኤልን ሸኛቸው:: አጋርም ልጅዋን በጀርባዋ አዝላ በበረሃ ስትጓዝ ሳለ እርሷም ልጅዋም በርሃብና በውኃ ጥም ሊሞቱ ስለደረሱ አንድ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብላ ስታለቅስ ትንሹ ልጅዋ እስማኤል በሁኔታው ተበሳጭቶ በታላቅ ቁጣ የቆመበትን አሸዋ ቢረግጠው ውሃ ፈለቀ:: አብርሃምም ለልጁ ለእስማኤል በበረሃ ውስጥ የተደረገውን ተአምር በሰማ ጊዜ ምንጩ ድረስ በመሔድ በአጠገቡ ቤተ መቅደስ ሠራ:: የቤተ መቅደሱም ስም ከአባ ተባለ:: በምሥራቅ በኩል ባለው በቤተ መቅደሱ ማዕዘን ጎን ከቀድሞ አባቶቹ የወረሰውን በምድር ላይ የመጀመሪያው ሰው አዳም ከገነት ይዞት የወጣው ነው የሚባለውን ጥቁር ደንጊያ አቆመ:: ከአባ በተባለው ቤተ መቅደስ አጠገብ ዘምዘም በሚባለው የእስማኤል ምንጭ አቅራቢያ አጋርና ልጅዋ ተቀመጡ:: እስማኤል በዚያ ቦታ አድጎ ትልቅ ቤተሰብ መሠረተ::



www.ethiopianorthodox.org

የእስማኤል ልጆች በቤተ መቅደስ አጠገብ መካ የተባለውን ከተማ
ሠሩ:: የዐረብ ሕዝቦችም ተባሉ::

የጥንት ዐረቦች የትም ቦታ ቢኖሩ ከአባና የእስማኤል
ምንጭ የሚገኝበት የመካ ከተማን ቅዱስ አድረገው ስለሚቆጥሩ
ምንም ያህል ቢርቁም ከያሉበት ቦታ ለመስገድ ወደ መካ ይመጡ
ነበር:: እንዲሁም መካ የዕጣን ምድር በመሆነዋ ብዙ ነጋዴዎች
ወደ እርሷ ይጎርፉ ነበር:: ይህን የተረዱ የመካ ነጋዴዎች በዐረቦች
ዘንድ ቅዱስ ነው ተብሎ የሚታመንበትን የእስማኤል ምንጭ
የግል ንብረታቸው አድርገው በመቁጠር ውኃውን መሸጥ ጀመሩ::
ለንግድ በዋለው ውኃ ቅድስና ላይ ዐረቦች መጠራጠር ስለጀመሩ
የቀደመ እምነታቸውን እየተዉ ወደ ቁማር ጨዋታና ሰካር
እንዲሁም ጥንቆላ ላይ አዘነበሉ::

በ570 ድኅረ ልደተ ክርስቶስ መሐመድ በመካ ሲወለድ
ባዕድ አምልኮ፣ ስካር፣ ቁማር ጨዋታና ጥንቆላ በዐረቦች ሕይወት
ላይ ነግሦ ነበር:: በዓመታቸው ባሉት ቀናት ልክ ያቆሟቸው
ሦስት መቶ ስድሳ ጣዖታትም ስሜተቸውን ማርከውት ነበር::[1] ገና
በእናቱ ማኅፀን ሳለ አባቱ የሞተበት መሐመድ የስድስት ዓመት
ልጅ ሳለ እናቱ በሞት ስለተነጠቀችበት ከስድስት ዓመቱ ጀምሮ
ያደገው በአያቱና በአጎቱ ቤት ነበር:: በአሕዛብ መካከል ያደገው
መሐመድ የ12 ዓመት ልጅ እያለ ከአጎቱ ከአቡ ታሊብ ጋር
ለንግድ ተግባር ወደ ሶርያ ሔዶ ሳለ ቡሐርያ ከተባለ ክርስቲያን
መነኩሴ ጋር እንደተዋወቀ ይተረካል:: ከእዚህ መነኩሴ በሰማው
የክርስትና ትምህርት ልቡ ሳይመሰጥ እንዳልቀረ ይነገራል:: እንዲ
ሁም ግመል ነጂ ሆኖ ከነጋዴዎች ጋር ወደ ግብፅ፣ ፋርስ፣ ሶርያ
በተጓዘባቸው ጊዜያት ሁሉ ከአይሁዶችና ከክርስቲያኖች ጋር ይገናኝ
ስለነበር የአይሁድና የክርስቲያን ሃይማኖት ትምህርት ግንዛቤ
ነበረው::

1. የዐረቦች አንዱ ዓመት 360 ቀናት ብቻ ነው ያሉት::





በመካ ሀብታም ነጋዴዎች ዘንድ «ታማኙ» በመባል ስሙ
ስለገነነ በ595 ዓ.ም. ከድጃ የተባለችው ሀብታም ሴት በወኪሎችዋ
አማካይነት ቀጥራው ስለነበር የታዘዘውን አጠናቆ ለከድጃ ሒሳቡን
ዘርዝሮ በፊትዋ ባቀረበ ጊዜ በግርማ ሞገሱና በንግግሩ የተማረከ
ችው የአርባ ዓመትዋና የስድስት ልጆች እናት የሆነችው ትዳሬ
ፈት ከድጃ ለባልነት ፈቀደችው:: የሃያ አምስት ዓመቱ ጉብል
መሐመድ የአርባ ዓመትዋን ከድጃን በፍጹም ፈቃደኝነት አገባ::
እሷን በማግባቱም ግመል ነጂ የነበረው መሐመድ መካ ላይ
ከነበሩት ሀብታሞች ይልቅ ሀብታም ሆነ::

መሐመድ ማንበብና መጻፍ አይችልም ነበር:: የሚስቱ
የአጎት ልጅ ዋርቃ የተባለ የአይሁድ እምነት ተከታይ /ኋላ ላይ
ክርስቲያን ሆኖ እንደሞተ ይነገራል:: የአይሁድንና የክርስቲያን
ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ዐረብኛ ተርጉሞ የነበረ/ ብዙ ጊዜ ብሉይ
ኪዳንን ያነብለት ነበር:: ሐዲስ ኪዳንንም ሲያነብለት በክርስቶስ
ታሪክ ልቡ ይመሰጥ እንደነበርና በባዕድ አምልኮና በመጥፎ ሥነ
ምግባር አረንቋ ተዘፍቀው የሚዳክሩ ወገኖቹን ከዚህ መጥፎ ሕይ
ወት መንጥቆ የሚያወጣ ነብይ ቢነሣ ምኞቱ እንደነበር ይተረካል::
በወገኖቹ ሕይወት ዘወትር የሚያዝነው መሐመድ ከከተማ ወጥቶ
ወደ ኮረብታ በመሔድ ስለወገኖቹ የወደፊት ዕጣ ይቆዝም ነበር::
አንድ ቀን በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እንደ
ተገለጸለትና ወርቅ የሚመስል ሰሌዳ አሳይቶት «አንብብ» እንዳለው
እርሱም ማንበብ እንደማይችል እንደገለጸለት ዳሩ ግን መልአኩ
እንደገና «አንብብ» ሲል እንዳዘዘውና ከዚያም በፊት ማንበብ የማ
ይችለው መሐመድ በሰሌዳው ላይ የተጻፈውን እንዳነበበ ለሚስቱ
ለከድጃ አጫወታት:: እርሷም ባልዋ ከመልአክ ጋር የተነጋገረ
መሆኑን አመነችና ደጋግሞ ወደ ኮረብታው ግርጌ እንዲሔድ
ከሰማይ የሚወርድለትን ራእይ እንዲጠባበቅ አጽናናችው:: መሐመ
ድም ምክሯን በመቀበል ደጋግሞ ወደ ኮረብቶች በመሔድ በየጊ
ዜው መልእክት ይቀበል እንደነበር ተከታዮቹ ይተርካሉ::

ባየው ራእይና በመጣለት መልእክት ተመርቶ «የአላህ
ነብይ» መሆኑን በቅድሚያ ለቤተሰቦቹና ለሥጋ ዘመዶቹ አወጀ::
ቀጥሎም ጣኦታትን ለማምለክ ለተሰበሰቡት ሰዎች «ሌላ አምላክ
ከአላህ በቀር የለም መሐመድም የአላህ ነብይ ነው» ሲል ስብከቱን



www.ethiopianorthodox.org

ቀጠለ:: ለጊዜው ግን ከሹፌትና በእርሱ ላይ ከመቀለድ ባለፈ
ትምህርቱን አሜን ብለው የተቀበሉ እምብዛም ነበሩ:: እርሱ ግን
ባለመሰልቸት ያለማቋረጥ በየቦታው ስብከቱን ቀጠለ:: በተለይ
የእስማኤልን የጉድጓድ ውኃና የከአባን መስጊድ መነገጃና የጥቅም
ማግኛ ያደረጉትን የመካ ሀብታም ነጋዴዎችና መሪዎች ላይ የሰላ
ሂስ በማቅረቡ ቀድሞ በቸልተኝነት ያለፉት የመካ ነጋዴዎች
በጥቅማቸው ላይ ስለመጣባቸው ማስጠንቀቂያ አዘል መልእክት
ወደ ቤተሰቡ ላኩ:: መሐመድ ግን ከተነሣበት ዓላማ ፍንክች
አላለም:: በዚህም በመካ ሀብታም ነጋዴዎች ጥርስ ውስጥ ገባ::

መሐመድ «ነብይነቱን» ለተቀበሉት ጥቂት ተከታዮቹ
እስላም የተባለውን እምነት አስተማራቸው ትርጓሜውም «ራስን
መስጠት ለአላህ ትዕዛዝ ራስን ማስገዛት» ማለት ነው:: ተከታዮቹ
ንም ሙስሊማን «እውነተኛ አማኞች» አላቸው:: መሐመድ ምንም
ያህል ቢጥርም በትውልድ አገሩ በመካ ውስጥ ትምህርቱ ብዙ
ተቀባይነት ሊያገኝ አልቻለም ነበር:: ይልቁን ብጽአት ለማድረስ
270 ማይል ርቆ ከሚገኘው ያትሪብ ከሚባለው ከተማ ወደ መካ
የመጡ ሁለት ሰዎች በመሐመድ ትምህርት በመሳባቸው በሁለተ
ኛው ዓመት ከያትሪብ 75 የሚሆኑ ሰዎች መጥተው የመሐመድ
ተከታይ ሆኑ:: ከእነዚህም መሀከል አሥራ ሁለት ደቀመዛሙርት
መርጦ በመሾም ወደያትሪብ ተመልሰው እስልምናን እንዲያስፋፉ
ላካቸው:: በያትሪብ ብዙ አይሁዶች ስለነበሩ የመሐመድ ትምህርት
ብዙ ተቀባዮችን ሊያገኝ ችሏል:: ምክንያቱም የአይሁዶች እምነት
በአንድ አምላክ ማመንና ጣዖትን መጥላት በመሆኑ የመሐመድ
ትምህርትም ከዚህ የወጣ ባለመሆኑ ነው::

የመካ ነጋዴዎችና ባለሥልጣናት መሐመድ በያትሪብ ብዙ
ተከታዮች እያገኘ መሆኑን ዐውቀው ትምህርቱን ከማስፋፋቱ በፊት
ሊገሉት ሲሹ መሐመድ አልካሷ በተባለች ተወዳጅ ግመሉ ተቀምጦ
ወደ ያትሪብ የሸሸባት ይህች ዕለት በእስላሞች ዘንድ ትከበራለች::
የእስላሞች የዘመን መጀመሪያ ዕለትም ሆና ተወስዳለች:: ዓመተ
ሂጅራ /ዓመተ ሽሽት/ በመባል ትታወቃለች::[1]

1. የእስላሞች የዘመን መጀመሪያ 622 ዓ.ም. ነው





የያትሪብ ሕዝብ መሐመድን እጁን ዘርግቶ በመቀበል
የከተማዋ ገዢ አደረገው:: የከተማዋ ስምም ከያትሪብ ወደ መዲና
ተለወጠ:: ትርጓሜውም የነቢይ ከተማ ማለት ነው:: በመዲና
እስልምና ያለከልካይ ተስፋፋ:: መሐመድ ከትውልድ ሀገሩ ከመካ
ሸሽቶ ወደ መዲና ከሔደ ከስምንት ዓመት በኋላ አሥር ሺ ሠራ
ዊት አሰልፎ ወደ መካ ዘመተ:: የመካ ሕዝቦችም የመሐመድን
ጦር ፈርተው ወደ የኮረብታው እግሬ አውጪኝ አሉ:: የመሐመድ
ሠራዊትም ሰው አልባ የሆነችውን ከተማ ተቆጣጠረ:: መሐመድም
አልካሷ በተባለችው ግመሉ ላይ ተቀምጦ ሠራዊቱን አስከትሎ
ወደ ከአባ አመራ:: እዚያም እንደደረሱም ለዘመናት ሲመለክባቸው
ወደነበሩት ጣኦታት እያመለከተ «እውነት መጥቶአል ሐሰት ግን
ኮብልሷል» ሲል ተከታዮቹ 360 የሚሆኑትን ጣኦታት በየተራ
አደቃቀው ጣሉአቸው:: ሸሽተው በየኮረብታው ለነበሩት የመካ
ሕዝቦችም «መሐመድ ከነሠራዊቱ ወደ መካ የገባው በተቀደሰው
መስጊድ ውስጥ ለመስገድ እንጂ ሰው ለመግደልና ለመዝረፍ አለ
መሆኑን» ስለገለጸላቸው ወደየኮረብታው ሸሽተው የነበሩት ሁሉ
ተመልሰው በመምጣት የእስልምናን ትምህርትና የመሐመድን
ነብይነትና መሪነት ተቀበሉ::

የእስልምና እምነት ግዛቱን ወደ ሌሎች ሀገራት ያሰፋው
ከመሐመድ ሞት በኋላ ነው:: ከመሐመድ ሞት በኋላ የመሐመድ
ታማኝ የነበረው አቡበከር የመሐመድን ትምህርት አንድ ላይ
አሰባስቦ መጽሐፍ እንዳደረገውና መጽሐፉንም ቁራን ብሎ ስም
እንዳወጣለት ይነገራል:: ትርጓሜውም ንባብ ማለት ነው:: ከመሐ
መድ ሞት በኋላ መሪነቱን ካሊፍ ተብሎ የተረከበውም ይኸው
አቡበከር ነው:: ካሊፍ ማለት የእግዚአብሔር ጥላ በምድር ላይ
ማለት ነው:: አቡበከርም ሆነ ከእርሱ በኋላ መሪነቱን የያዙት ሁሉ
ወታደሮች ወደ ፋርስና ወደ ሰሜን አፍሪካ እንዲሁም ወደሌሎች
ሀገራት በመላክ እስልምናን አስፋፍተዋል::

የሮማ አምፓየር ከቅኝ ግዛቱ ስፋት የተነሣ እያነገነገ ባለበት
በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን «እኔ የመጨረሻው ነቢይ የተላ
ኩት መልእክቴን በሰይፍ እንድፈጽም ነው:: ሰይፉም የሰማይና
የሲኦል ቁልፍ ነው:: ስለሃይማኖት ብሎ የሚመዘው ሁሉ ባለዋጋ
ነው» የሚለው የነቢያቸውን መመሪያ አንግበው ዓለምን በእስልምና



www.ethiopianorthodox.org

ለማጥለቅለቅ ታጥቀው የተነሱት እስላሞች ፋርስን፣ ሶርያን፣
ግብጽንና ሊቢያን በቁጥጥራቸው ስር በማድረጋቸው የባዛንታይን
መንግሥት ውጥረት ውስጥ ገባ:: በባዛንታይን መንግሥታት በሚ
ረዱት መላካውያን ግፍ የተፈጸመባቸው የግብጽና የሶርያ ክርስቲ
ያኖች የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው በሚለው መንፈስ አካባቢውን
እንደጉም ሊሸፍን ለደረሰው የዐረብ ጦር በራቸውን ወለል አድር
ገው ከፍተው በማስገባት ለቀደሙት ቅኝ ገዥዎቻቸው ያላቸውን
ጥላቻ አሳይተዋል:: ሆኖም ግን በእስላሞች ቁጥጥር ስር በሆኑት
በግብጽና በሶርያ የሚኖሩ ክርስቲያኖች «ትሻልን ሰድጄ ትብስን
አመጣሁ» እንዲሉ የባሰ እንጂ የተሻለ አልገጠማቸውም:: ይሻሉ
ይሆናል በሚል ግምት እጃቸውን ዘርግተው የተቀበሉአቸው የባሱ
ሆነው ተገኙ:: በተለያዩ ወቅቶች ግብጽን ያስተዳድሩ የነበሩት የሽ
ያትም ሆነ የሱኒ እስልምና እምነት ተከታይ የሆኑት ባለሥልጣኖች
በግብጽ አርቶዶክስ ምእመናን ላይና የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች
ላይ ከባድ የመከራ ቀንበር ጭነውባቸው እንደነበር የሚከተሉት
ድርጊቶች ምስክር ናቸው::

- በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ይሠሩ የነበሩት ክርስቲ
ያኖች ያለምንም ጥፋት ክርስቲያን በመሆናቸው ብቻ ይባረሩ
ነበር::
- ገደብ የለሽ ግብርና የነፍስ ወከፍ ታክስ እንዲከፍሉ ይገደዱ
ነበር::
- አንድ ፓትርያርክ ሞቶ ሌላ ለመተካት ከገዥዎች ፈቃድ ለመ
ጠየቀ ከፍተኛ ገንዘብ ይሰጥ ነበር::
- በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርኮች ላይ እስራትና
ሥቃይ ገዥዎቹ ያደርሱባቸው ነበር::
- በመስቀል ጦርነት ጊዜ እስላሞች በተዋሕዶዎችና በምዕራብ
መለካውያን መካከል የተፈጠረውን ስር የሰደደ ቅራኔ ግንዛቤ
ውስጥ ሳያስገቡ ክርስቲያን በመሆናቸው በቻ ተዋሕዶዎች
ለመስቀል ጦረኞች /ካቶሊኮች/ ያግዛሉ ብለው በመጠራጠር
በዓይነ መአት ይመለከቷቸው ነበር::
- አብያተ ክርስቲያናቱ ከነህብታቸው ያለ የሌለ ሀብታቸው
ተሟጦ የተወረሱበት ጊዜ ነበር::





- የሱኒ እስልምና እምነት ተከታይ የነበረው ሳላዲን የተባለው
የግብፅ ገዢ የአስተዳደር ሥራውን እንደጀመረ ክርስቲያኖችን
ከተለያዩ የሥራ ቦታዎች ከማባረሩ በተጨማሪ የውርደት ምል
ክት ከሆነው ከጥቁር ልብስ በስተቀር ነጭና በተለያዩ ኅብረ
ቀለማት ያጌጡ ልብሶችን እንዳይለብሱ፣ ፈረስ እንዳይጋልቡ፣
ከፍ ያለ መቀጫ ገንዘብ ለመንግሥት እንዲከፍሉ በማዘዙ ክር
ስቲያኖች በግፍ የተጣለባቸውን ገንዘብ ለመክፈል ያለ የሌለ
ሀብታቸውን ሸጠዋል፣ ርስታቸውንም ለእስላሞች እንዲሸጡ
በመገደዳቸው ርስት አልባ ሆነዋል:: የመከራውን /የግፉን/
ቀንበር መሸከም ያልቻሉ አንዳንድ ክርስቲያኖችም በነፃነት
ለመኖርና ባለመብት ለመሆን የእስልምናን እምነት መቀበል
የግድ በመሆኑ ሳይወዱ በግድ ሰልመዋል::

በቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ ዓቢዩን ሚና ሲጫወቱ
የነበሩት የእስክንድርያ /የግብፅ/ና የአንጾኪያ /ሶርያ/ አብያተ ክርስ
ቲያናት ቀደም ሲል በ451 ዓ.ም. በልዮን ጦማር ምክንያት በተፈጠ
ረው መለያየት ገዥዎቻቸው በነበሩትና የሁለት ባሕርይ እምነት
ደጋፊ በሆኑ ነገሥታት ኋላም ግብፅንና ሶርያን በተቆጣጠሩ እስላ
ሞች ባላባራ የመከራ ዝናብ በመደብደባቸው፣ የቀድሞ ቦታቸውን
አጥተው በምእመናንም ቁጥር ተመናምነው አሁን ያሉበት ደረጃ
ላይ ደርሰዋል:: እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ለዚህ ሁሉ ተጠያቂ
የሚያደርጉት በወቅቱ የነበሩትን የሮም ካቶሊክና የግሪክ ቤተ
ክርስቲያን መሪዎችን ነው::



www.ethiopianorthodox.org

## 3.8 በሮም ካቶሊክ፣ በምሥራቅ ኦርቶዶክስ[1] ና በኦርየንታል /ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ/[2] አብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለው የእምነትና የሥርዓት ልዩነት።

ሀ. የሮም ካቶሊክና የምሥራቅ ኦርቶዶክስ /መለካውያን/ ለኢየሱስ ክርስቶስ አንድ አካል ሁለት ባሕርያት አሉት ብለው ሲያምኑ የእኛ የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስ በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው ብላ ታምናለች።

ለ. የሮማ ካቶሊክ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ የሠረጸ ነው ብላ ስታምን የምሥራቅ ኦርቶዶክስና የኦርየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የጌታን ምስክርነት መሠረት አድርገው የመንፈስ ቅዱስ መሥረጽ ከአብ ብቻ መሆኑን ያምናሉ። ዮሐ. 15÷26።

ሐ. የሮማ ካቶሊክ ስለፐርጋቶሪ /መካነ ንስሐ/[3] የምታምነውና የምታ ስተምረው በሁለቱም ዘንድ ተቀባይነት የለውም።

መ. በኦርየንታልና በምሥራቅ ኦርቶዶክስ የምንቀበለውን ሥጋና ደም ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደው መሆኑ ሲታመን የሮማ ካቶሊክ ግን ነፍስ ያለው መለኮት የተዋሐደው ብላ ታምናለች።

ሠ. በካቶሊካውያን ዘንድ ከሥጋውም ከደሙም የሚቀበለው ቀዳሹ ብቻ ሲሆን ለምእመናን ግን ሥጋውን ብቻ ነው የሚያቀብሉአቸው።[4] በምሥራቅ ኦርቶዶክስና በኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ግን ሥጋውና ደሙ ለቀዳሹም ለምእመኑም እኩል ይሰጣል።

1. የምሥራቅ ኦርቶዶክስ /መለካውያን/ የሚባሉት የግሪክ፣ የሩማንያ፣ የሩሲያ፣ የቡልጋሪያ፣ የሰርቢያ የቆጵሮስና የመሳሰሉት አብያተ ክርስቲያናት ናቸው።
2. ኦርየንታል /ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ/ የሚባሉት የግብጽ፣ የሶርያ፣ የአርመንያና የሕንድና የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው።
3. በካቶሊካውያን እንደሚታመነው ሰዎች ስለሠሩት ኃጢአት በመጸጸት ንስሐ ገብተው ሳለ ንስሐቸውን ሳይፈጽሙ ድንገት ቢሞቱ በመንግሥተ ሰማይና በገሀነመ እሳት መካከል ልዩ የሆነ የንስሐ ቦታ ስላለ ነፍሶቻቸው ወደዚያ ሔደው ለኃጢአታቸው እስኪነጹ ድረስ መከራ እየተቀበሉ ቆይተው ኋላ ወደ መንግሥት ሰማይ ይገባሉ ብለው የሚያስተምሩት ትምህርት ነው።
4. በቫቲካን ሁለት ጉባኤ ደሙ ለምእመናንም እንዲሰጥ ተወስኖአል ይባላል።



www.ethiopianorthodox.org



ረ. የሮማ ካቶሊክ ቅድስት ድንግል ማርያምን አርያማዊት /ሰማያዊት/ ፍጥረት ናት ብላ ስታምን የምሥራቅ ኦርቶዶክስና የኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ግን አዳማዊት ፍጥረት መሆንዋን ያምናሉ።[1]

ሰ. በኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት የሜሮን አቀባብ ወዲያው ከጥምቀት አያይዞ ይፈጸማል። በምሥራቃውያን/መለካውያን/ ዘንድም ሥርዓቱ ያው ነው። በሮማ ካቶሊክ ግን ሕፃኑ ተጠምቆ አሥር ዓመታት ከቆየ በኋላ ነው ሜሮን የሚቀባው። የሚቀባውም ኤጲስ ቆጶሱ ብቻ ነው። እንደ ቤተክርስቲያናችን ሥርዓት በእነሱ ዘንድ ቄስ የመቀባት መብት የለውም።

ሸ. ቅዱስ ቁርባንና ሥርዓተ ቅዳሴን በተመለከተ

- ካቶሊካውያን ከቁርስ በኋላ አንድ ሰዓት ቆይተው ሲቆርቡ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን ለመቁረብ 18 ሰዓታት መጾም ይገባል።
- ካቶሊካውያን በአንድ ቀን በአንድ መንበር መላልሰው ሲቀድሱ በኦርየንታልና በምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ግን በአንድ መንበር አንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚቀደሰው።
- በካቶሊካውያን ዘንድ የቅዳሴ ሰዓት ሁልጊዜም ማለዳ ነው። በግሪክ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድም የቅዳሴ ሰዓት ሁልጊዜ ማለዳ ሲሆን በዓቢይ ጾም ግን ከእሑድ ቅዳሜ በቀር ቅዳሴ ክልክል ነው። እሑድ የቀደሱበትን በጽዋው አሰንብተው ዓርብና ረቡዕ በሌሎችም አመች በሆኑ ዕለታት ጸሎተ ሠርክ አድረሰው ያቆርቡታል። «ኰሮኢጊያዝሚኑ» አስቀድሞ የተቀደሰ ማለት ነው ይላሉ። እንዲሁም በጸሎተ ሐሙስ የቀደሱበትን እስከ ዓመት በመንበር ያስቀምጡታል አቁርቡኝ የሚል በድንገት ቢመጣ «ለመጠባበቂያ ነው» ይላሉ።[2]

1. ካቶሊካውያን በሐዋርያው ቶማስ የተጻፈ ነው ብለው የተቀበሉት መጽሐፍ እንዳለና በዚህም መጽሐፍ ውስጥ ኢያቄምና ሐና እርጅና ላይ ስለነበሩ ሐና በግብረ መንፈስ ቅዱስ «ያለወንድ ዘር» እመቤታችንን ጸንሳ መውለድዋ ተገልጾአል ይባላል። ዳሩ ግን በኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ አባባሉም ሆነ መጽሐፉ ተቀባይነት የለውም።
2. ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት ገጽ 53

በእኛ ቤተ ክርስቲያን የቅዳሴ ጊዜ እንደየሁኔታው የተለያየ ነው:: በጾም ወቅት ከሰዓት በኋላ ማለትም በዘጠኝ ሰዓት ሲሆን በበዓለ ሃምሳና ቅዳሜ በሠለስት፣ እሑድ በነግህ፣ በትንሣኤ በልደ ትና በጥምቀት ደግሞ በመንፈቀ ሌሊት ይቀደሳል::

- ♦ በካቶሊካውያን ዘንድ አንድ ቄስ ብቻውን መቀደስ ሲችል በእኛ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ግን አስገዳጅ ሁኔታ ካል ተፈጠረ በስተቀር ቅዳሴ ለማካሔድ አምስት ልዑካን ሊኖሩ ይገባል::
- ♦ በእኛ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በመለካውያን ሕፃናት ከተጠመቁና ሜሮን ከተቀቡ በኋላ ወዲያው ሲቆርቡ በካቶ ሊክ ዘንድ ግን ነፍስ ካወቁ በኋላ ነው የሚቆርቡት::

ቀ. በካቶሊካውያን ዘንድ ወደ ክህነት ለሚቀርቡ ሁሉ ማግባት ክልክል ነው:: በእኛ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የዲቁና ማዕረግ የተቀበለ አንዲት ሚስት አግብቶ የቅስና ማዕረግ መቀበል ሲችል ከዚያ በላይ ያለውን ማዕረግ ግን አያገኝም:: ዲቁናውን እንደተቀበለ ለመመንኮስ ቢፈልግ ግን ገዳም ገብቶ በረድእነት አገልግሎ ይመነኩሳል:: ከመነኮሰ በኋላ የቅስና ማዕረግ ይቀበ ላል:: ወደ ጵጵስና የሚወስደው መንገድም ይኸው ነው::

በመለካውያን ዘንድ ደግሞ አንድ ሰው የዲቁና ማዕረግ የሚቀ በለው ካገባ ወይም ከመነኮሰ በኋላ ነው:: የዲቁና ማዕረግ ከተቀበለ በኋላ ማግባት ክልክል ነው:: ሳይመነኩስ በድንግል ናው ብቻ ዲቁና ተቀብሎ ከዚያው ላይ ቅስና ይሰጡታል:: ይህም ላለማግባት መወሰኑን ካረጋገጡ በኋላ ነው:: እንዲሁም የካቶሊክ ካህናት ጽሕማቸውን ሲላጩ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ግን ያሳድጉታል::

በ. በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አብዛኛውን ጊዜ ከሥዕል በተ ጨማሪ ለጌታ ለእመቤታችን ለጻድቃንና ለሰማዕታት መታሰ ቢያ የድንጋይ ሐውልት ሲቀረጽላቸው በምሥራቅ ኦርቶዶክስና በኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ግን በሥዕል ይሳላሉ::





ተ. የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሥጋ ወደሙን በግልጽ በምእመኑ ፊት ፈትተው ሲያቀርቡ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን ለክብረ ሥጋወደሙ ሲባል ይጋረዳል፣ ይሸፈናል::

ቸ. የንስሐ አፈጻጸምን በተመለከተ በሮማ ካቶሊክ ተነሳሒው /ተና ዛዡ/ና ናዛዡ አይተያዩም:: እንዳይተያዩ የሚጋርዳቸው ነገር እንዲኖር ይደረጋል:: በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ግን ኑዛዜ የሚፈጸመው በግልጽ ነው:: ተናዛዡ ከናዛዡ ፊት ቀርቦ ኑዛዜውን ያቀርባል:: በቀኖና አሰጣጥ ላይም ልዩነት አለ:: የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ቄስ ተናዛዡ ሀብታም ከሆነ ቀኖናውን በገንዘብ ይዋጀዋል /ይለውጠዋል/:: ናዛዡ ገንዘቡን ተቀብሎ የሱን ፋንታ ይጸምለታል ይላሉ:: በእኛ ቤተ ክርስቲ ያን ግን ይህ ዓይነቱ የቀኖና አሰጣጥ ከሐዋርያት ትምህርት የወጣ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም::

ነ. የሮማ ካቶሊክ በጴጥሮስ መንበር ላይ የሚቀመጠው የሮም ፓፓ በመንበሩ ተሰይሞ በሚወስነው ሁሉ አይሳሳትም ስትል የምሥ ራቅ ኦርቶዶክስና የኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጉባኤ ተሰብስበው በተገኙበት በመ ንፈስ ቅዱስ መሪነት የተወሰነውና ለወደፊት የሚወሰነው ውሳኔ ነው የማይሳሳት በማለት የአንድን ሰው የፖፑን አለመሳሳት አይቀበሉም:: የሮሙ ፓፓ የሁሉ የበላይ ነው የሚለውንም ይቃወማሉ::



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አራት
# ፕሮቴስታንቲዝም

## 4.1 ጅማሮው

የምዕራቡን ዓለም ጠቅላ የያዘችው የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ፓፓ የሥልጣን ጡንቻውን እያፈረጠመ በመምጣቱ ምንም ያህል ሳይቀረው መላውን አውሮፓ እስከመቆጣጠር በመድ ረሱ ኃያልነቱ እያደገና እየበረታ ይሔድ ጀመር:: የፓፑን ትዕዛዝ መተላለፍም በሥጋም በነፍስም የሚያስቀጣ ኃጢአት ሆኖ ይቆጠር ነበር:: ፓፓው የክርስቶስ እንደራሴ መባልን ብቻ ሳይሆን በሕዝብና በመንግሥት ሁሉ ላይ የበላይ ገዥ ሆኖ እስከመታወቅ ደረሰ::

በሮማ ቤተ ክርስቲያን መንበር ላይ የሚሰየሙ ፓፓዎች ከተመረጡና በመንበሩ ላይ ከተሰየሙ በኋላ ወዲያው የፈቀዳቸውን ሕግ ያወጣሉ:: ለሚያወጡት ሕግ መታዘዝ ደግሞ የተከታዮች ሁሉ ግዴታ ነው:: በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ሕጎች በፓፓዎቹ ተደን ግገው ወጥተው ነበር:: ለቤተ ክርስቲያን የሚከፈለውን ታክስ ጨምሮ ሃይማኖት ነክ ከሆኑ መጻሕፍት ውስጥ ሊነበቡና ላይነበቡ፣ እንዲሁም በትምህርቱ ዘርፍ ሊጠኑና ላይጠኑ የሚገባቸውን እስከ መወሰንና ሕጉን ተላልፎ የተገኘውንም ሆነ በሮማ ካቶሊክ ውጭ ያሉትን ሁሉ በኃይል አስገድዶ ካቶሊካዊ ለማድረግ ጫና የማያሳ ድርና የሚቀጣ የምርመራ ክፍል /ኢንኩዚሽን/ በአሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተቋቁሞ ነበር::

ይህ የምርመራ ክፍል ፓፑ ላወጣው ሕግና ደንብ የማይገ ዙትን ሁሉ እስከ ሞት ድረስ ለመቅጣት የተቋቋመ ነበር:: የሮማ ካቶሊክ በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተግባራዊ አድርጋ የነበረው ይህ ኢንኩዚሽን በዘመነ ሰማዕታት የሮማ ቄሳሮች በክርስቲያኖች ላይ ያደርሱት የነበረውን ዐየነት ሥቃይና መከራ የሚያስታውስ ነው:: በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በአረመኔነት ጭካኔ ተሠቃይ ተው ለኅልፈት ተዳርገዋል:: በሚነድ እሳት የተጣሉ፣ በከባድ መዶመጫ የተዳመጡ፣ በመጋዝ የተተረተሩ በሌላም በሚያሠቃይ መሣሪያ እየተሰነጠቁና እየተቆራረጡ እንዲያልቁ የተደረጉ አያሌ ናቸው::



www.ethiopianorthodox.org



በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ውስጡን ሲጋጋም የነበረው ተቃውሞ ፈንድቶ ይፋ የወጣው በጀርመናዊው መነኩሴ በማርቲን ሉተር አማካይነት ነበር:: በጀርመን አገር የአይስሌበን ገበሬዎች ከነበሩት ሐንስና ማርጋሬት የተወለደው ማርቲን ሉተር ምንም እንኳን ወላጆቹ ድሆችና ከእርሱ ሌላ ስድስት ልጆች የነበሩአቸው ቢሆንም ማርቲን ሉተርን ፊደል አስቆጥረውት ነበርና ኮሌጅ ለመግባት የነበረውን ምኞት ለማሳካት የወላጆቹ አቅም ውሱን በመሆኑ ምግቡንና ሌላ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማሟላት ሲል በየመንገዱ ላይ እየዘፈነ በሚያገኘው ምግብ የሕግ ትምህርቱን ጀምሮ ነበር::[1]

የማርቲን ሉተር ሕይወት አቅጣጫ የሕግ ትምህርቱን ሊጨርስ ትንሽ ሲቀረው ተለወጠ:: የሚወደው ባልንጀራው ሞት ስላስደነገጠው የሕግ ትምህርቱን አቋርጦ ኤርፋርት ከነበረው አውግስቲንያን ገዳም ገባ::

ለሉተር ገዳም መግባት የተለያዩ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ:: አንዳንዶች በፍርድ ቀን እንዴት እሆናለሁ? በማለት የኃጢአተኝ ነት ስሜት አእምሮውን እያስጨነቀውና እየጸናበት ስለሔደ የነፍ ሱን ድኅነት ለማግኘት በማሰብ ወደምንኩስና እንደተመራ ሲገልጹ ሌሎች ደግሞ ከዕለታት በአንድ ቀን ማንስፊልት የነበሩ ወላጆቹን ጠይቆ ወደ ኤርፋርት ሲመለስ መንገድ ላይ አደገኛ አውሎ ነፋስ ሲያንገላታው በዚህ አውሎ ነፋስ ከመሞት ብታተርፊኝ ቀሪ ሕይ ወቴን አምላኬን በምንኩስና አገለግላለሁ ብሎ ለቅድስት ሀና ብጽአት ገብቶ ስለነበር ነው ይላሉ:: ያም ሆነ ይህ ሉተር በ1505 ዓ.ም. ኤርፋርት ከነበረው አውግስቲንያን ገዳም ገብቶ የአውግስ ቲንን ጽሑፎች አጣና::

1. በዚያን ጊዜ በጀርመን አገር የነበሩ ተማሪዎች ራሳቸውን የሚረዱት በዚህ ዓይነት ነበር:: እንደ እኛው ሀገር የቆሎ ተማሪ ማለት ነው:: ሕዝቡም ተማሪዎቹ ይህን በማድረጋቸው እንደ ለማኝ አይቆጥራቸውም:: ነገር ግን በየሰው ቤት እየዞሩ የዕለት ምግባቸውን የሚጠይቁ ተማሪዎች መሆናቸውን አውቆ ሴቶች ከየቤታቸው ብቅ እያሉ ወደቤታቸው እንዲገቡ በማድረግ ያበሉዋቸው ነበር::

የሉተር አመጽ በአብዛኛው የጀረመን ሕዝብ ዘንድ ድጋፍ ተችሮት ነበር:: ሕዝቡ በዚህ መንስኤ ለወደፊት የእምነቱን ነፃነት ብቻ ሳይሆን የሀገሩንም ነፃነት የሚጎናጸፍ እንደሚሆን ተስፋ በማድረጉ ከሉተር ኋላ በደጀንነት የተሰለፉ አያሌ ነበሩ:: ይህም ለሉተር የልብ ልብ ሰጥቶት በተቃዋሚነቱ እንዲገፋ አድርጎታል::

ሉተር መጽሐፍ ቅዱስን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ጀርመንኛ ቋንቋ የተረጎመ ሰው ሲሆን በዚህም ሥራው ለጀርመንኛ ቋንቋ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጉ ይወሳለታል:: እንዲሁም አያሌ የጸሎት መጻሕፍትንና መዝሙራትን በቀላል የጀርመንኛ ቋንቋ በማዘጋጀት ትምህርቱ በቀላሉ እንዲስፋፋ አድርጓል:: በሕይወት ዘመኑ አራት መቶ መጻሕፍትና መጽሔቶች መጻፉም ይወሳለታል::

ሉተር ከተራው ሕዝብ ይልቅ ለነገሥታት ያደላ እንደነበር ከአንዳንድ ድርጊቶቹ መገንዘብ ይቻላል በ1525 ዓ.ም. የጀርመን ገበሬዎች ገዥዎቻቸው የጫኑባቸው የበደል ቀንበር አንገፍግፏአቸው በመንግሥቱ ላይ አምጸው በተነሡበት ወቅት ሉተር ለተበደሉት ገበሬዎች ደጋፊ ሆኖ በመቆም ፈንታ ልዑላኑን በመደገፍ «ገበሬው የማያርፍ ከሆነ በሰይፍ ቆራርጡት» በሎ በይፋ በማስተማሩና እንዲፈጁ በመስማማቱ ከፍ ያለ ነቀፋ ደርሶበታል:: «የዚህ ዓለም ገዥዎች አማልክት ናቸው:: ተራው ሕዝብ ደግሞ ሰይጣን ነው» የሚል አባባልም ነበረው::

አና ባኘቲስት በመባል የሚጠሩትና የሕፃናት ጥምቀት አላስፈላጊ መሆኑን በማስተማር ዳግም ያጠምቁ የነበሩ የኘሮቴስታንት ክፍሎች ንቅናቄያቸው ከጊዜ ጊዜ እየጨመረ አባላታቸውም እየበረከተ መሔዱ ያሰጋው ሉተር የየሀገሩ ገዥዎች ንቅናቄያቸውን በሰይፍ እንዲያቆሙት በማስተማሩ በሺህ የሚቆጠሩ አና ባኘቲስቶች በጭካኔ ተገድለዋል:: በዚህም የሮማ ካቶሊክ በተቃዋሚዎችዋ ላይ ታደርሰው የነበረውን ጭካኔያዊ ቅጣት ይቃወም የነበረው ሉተር ያንኑ ጭካኔያዊ ተግባር ራሱ በመድገሙ ከፍተኛ ትዝብት ላይ ወድቋል::

በአይሁድ ላይ ከነበረው የመረረ ጥላቻ የተነሣ «ለክርስቲያን ከአይሁድ የሚከፋ አደገኛ ጠላት የለውም» እያለ ይሰብክ ነበር:: በዚህ ጸረሴማዊ አቋሙም በአንዳንድ ጸሐፍት ዘንድ «የሒትለር የመንፈስ አባት» እስከመባል ደርሷል:: የአእምሮ ዘገምተኞችን



www.ethiopianorthodox.org



በተመለከተ የነበረው አቋምም እጅግ አሳዛኛና ከአንድ የእምነት መሪ ቀርቶ ከአንድ ተራ ሰው እንኳን የማይጠበቅ ነበር «የአእምሮ ዘገምተኞችን ከማስወገድ ውጭ ሌላ ምንም መፍትሔ የለም» ይል ነበር::

## 4.2 ኘሮቴስታንቲዝም ድኅረ ሉተር

ከሉተር በፊት ለተሐድሶ መንገድ ጠራጊዎች እንደነበሩ ከሚነገርላቸው ውስጥ ፒተር ዋልዶና ጆን ዊክሊፍ በዋነኛነት ይጠቀሳሉ:: በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በደቡብ ፈረንሳይ ተነስቶ ለነበረው «ዋልዴንስ» ለተባለው ንቅናቄ መሥራችና ፊት አውራሪ የነበረው ዋልዶ ሀብታም ነጋዴ እንደነበርና «ፍጹም ልትሆን ብትወድ ሑድና ያለህን ሽጠህ ለድሆች ስጥ» በሚለው የጌታ ትምህርት ተመርቶ ሀብቱን ሁሉ ሽጠ ለድሆች በመስጠት ንቅናቄውን መጀመሩ ይነገርለታል::

ዋልዶ በሮማ ፓፓ ላይ የሰላ ሂስ የሰነዘር እንደነበርና «ፓፓውና ተከታዮቹ ኢየሱስ ባስተማረው ትምህርት ውስጥ የሌሉ በመሆናቸው ልንከተላቸው አይገባም» ይል ነበር:: ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍትንም አይቀበልም ነበር:: ጸሎተ ቅዳሴና ለሙታን የሚደረገው ጸሎተ ፍትሐትም አያስፈልግም ባይ ነበር:: የዋልዶ ተከታዮች ዋልዴንሰ /ዋልዴኖች/ ተብለው ሲጠሩ ሰው መልካም ክርስቲያን ከሆነ በምቾትና በተድላ እንደዚሁም በኃጢአት ሥራ ለመኖር አይችልም የሚል አስተምህሮ ነበራቸው::

በአሥራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሣው የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ መምህርና የካቶሊክ ካህን የነበረው ጆን ዊክሊፍ «ፓፓዎች ፈጽሞ ኃጢአት አይሠሩም» የሚባለውን ነገር እንደማይቀበልና እንደውም ብዙ የሚነቀፉበት ተግባር እንዳላቸው፣ እንዲሁም ከላቲን ቋንቋ ይልቅ ለእንግሊዝ ሕዝብ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ሊጸለይና ሊቀደስ እንደሚገባና ብቸኛው የድኅነት መገኛም መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ እንደሆነ አጥብቆ ያስተምር ነበር::

ዝዊንግልና ጆን ካልቪን በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሱ የተሐድሶ አራማጆች የነበሩ ሲሆን ከሉተር ትምህርት

የተለየ አቋም ይዘው በመገኘታቸው የኘሮቴስታንት እንቅስቃሴ ገና ከማለዳው ነበር መከፋፈል የገጠመው::

ሉተርና ዝዊንግል በአንድ አጋጣሚ በሆነ ጉዳይ ላይ ሲከራከሩ ቆይተው በኋላ ሁለቱም ተማረው እስከ ጥል ደረሱ:: በመጨረሻም ሉተር በዝዊንግል ሐሳብ መንፈሱ እጅግ ስለታወከ ከተቃዋሚው ጋር እጅ ለእጅ ለመጨባበጥ እምቢተኝነትን አሳይቷል::

እ.ኤ.አ. በ1509 ዓ.ም. ከፓሪስ ሰባ ማይል ርቃ በምትገኘው ኖዮን በተባለችው ትንሽ ከተማ ውስጥ የተወለደው ጆን ካልቪን ከእርሱ በፊት የነበረውን የዝዊንግልን ተስፋ ከፍጻሜ ያደረሰ ሲሆን በአስተምህሮው ከሉተር የተለየ ነበር:: ዝዊንግልም ሆነ ካልቪን ስለ ቅዱስ ቁርባን የነበራቸው አመለካከት ከሉተር ፍጹም የተለየ ነበር:: በተጨማሪም ሉተር በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት የጌታ መስቀል፣ ሻማ ማብራት፣ በቅዳሴ ጊዜ የካህናት አልባሳት የመሳሰሉት እንዲሠሪባቸው በማድረጉ ከዝዊንግልና ከካልቪን ወቀሳና ውግዘት ደርሶበታል::

ካልቪን ትምህርቱን በማይቀበሉት ላይ ውግዘትና ቅጣት የሚያስከትል ሕግ አውጥቶ ነበር:: በ1553 ዓ.ም. ሚካኤል ሴር ቤቱስ የተባለ የእስጳኝ ተወላጅ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት በመካዱ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተይዞ በእሳት እንዲቃጠል ስለፈረደችበት ከእስር ቤት አምልጦ ጄኔቫ ገብቶ ነበር:: ተቃዋሚዎቼን በመቀስቀስ ረብሻ ያስነሳብኛል ብሎ የሰጋው ካልቪን ክህደቱን ምክንያት አድርጎ ከከተማው ሹማምንት ጋር በመስማማት ተይዞ በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት አስደርጓል::

ካልቪን የአንድ ሰው ድኅነትም ሆነ ጥፋት አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተወሰነ ስለሆነ ሰው በራሱ ለያመጣው የሚችለው ለውጥ የለም የሚል አስተምህሮ ነበረው:: እንዲሁም እርሱ የሚመራት ቤተ ክርስቲያን ራሷን ችላ በመተዳደር ከህገሩ መንግሥት ጋር ተባብራ እንድትሠራ አስተምሯል:: ሉተር ግን የእርሱ ቤተ ክርስቲያን በልዑላን ሥር እንድትተዳደር ነው ያደረገው::

ከላይ የተጠቀሰው ልዩነታቸው እንዳለ ሆኖ ሉተርና ካልቪን የሚከተሉትን በጋራ ተቀብለው ያስተምሩ ነበር:: ለጌታ ሁለት ባሕርያት እንዳሉት /ይህም የኬልቄዶን ጉባኤ ያሳለፈው ውሳኔና





ቤተ ክርስቲያንን ለሁለት የከፈለ መሆኑን ከዚህ በፊት አይተናል::/ በመጽሐፍ ቅዱስ የታዘዙትን ትዕዛዛትና የወጡትን ሕግጋት በመጠበቅ ሳይሆን በእምነት ብቻ ነው የሚዳነው የሚለው ትምህርት የሁለቱም ነበር:: የእመቤታችንንና የሌሎች ቅዱሳንን አማላጅነትና ክብር ሁለቱም አይቀበሉም:: ቅዱሳት መካናትን መሳለም፣ ለቅዱሳን ስዕላት የሚገባውን ክብር መስጠትና ገዳማዊ ሕይወትን አላስፈላጊ እንደሆኑ ሁለቱም ያምናሉ::

የሉተር ተከታዮች ሉተራውያን ሲባሉ የካልቪን ተከታዮች ደግሞ ካልቪኒስቶች ይባላሉ:: በካልቪን የተመሠረተው የእምነት ድርጅት «የኘሬስባይቴሪያን ቤተክርስቲያን» በመባል ይጠራል:: በሉተር የተጀመረው የኘሮቴስታንት እንቅስቃሴ ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው ሁሉ ሪሱ ሉተር በሕይወተ ሥጋ እያለ በተለያየ ጎራ ተከፋፍሎ ነበር:: ከሉተር ሞት በኋላም ክፍፍሉ እየጨመረ ሔዶ በዚህ በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የክፍልፋዮቹን ቁጥር ለመገመት እስኪያዳግት እንደ ሰማይ ከዋክብት በዝተው ይገኛሉ:: እንደ ባሕር አሸዋ ጉልቆ መሣፍርት ከሌላቸው የኘሮቴስታንት ክፍልፋዮች የጥቂቶቹ አመሠራረትና እምነት እነሆ:-

## 4.3 የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን

አንዳንድ የአውሮፓ ነገሥታት የሉተር እንቅስቃሴ በገንዘብና በሞራል ሲደግፉ የእንግሊዝ ንጉሥ የነበረው ሔንሪ ስምንተኛ ግን ፈር የለቀቀውን የሉተር ትምህርት በማውገዝ በሰባቱ ምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ጸጋ የሚሰጥ መሆኑን አብራርቶ በመጻፍ ለሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ያለውን ታማኝነትና ጠበቃነት በማሳየቱ ፓፓ ልዮን ዐሥረኛ «የእምነት ጠባቂ» ሲሉ አሞካሽተውት ነበር::

የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጠበቃ ተብሎ በፓፓ ልዮን የተሞገሰው ንጉሥ ሔንሪ መንግሥቱን የሚወርስ ወንድ ልጅ ልትወልድለት ያልቻለችውን ሚስቱን ካቴሪኒ ዘአራጐንን ፈትቶ አን ቦሌይን የተባለችውን ሴት ለማግባት በመፈለጉ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ይህን ፍላጐቱን ከግቡ እንዲያደርስ ከአሁኑዋ ሚስቱ ጋር ያለውን ፍቺውን እንድታጸድቅለት እንዲሁም ያሰበውን

www.ethiopianorthodox.org

ሁለተኛውን ጋብቻም እንድትባርክለት በኢንግላንድ የፓፑ እንደ ራሴና የንጉሡም ዋና ባለሟል በነበረው በእንግሊዛዊው በካርዲናል ቶማስ ዌልሴይ አማካይነት ለፖፑ ቢልክ ፖፑ ሐሳቡን ሳይቀበለው ቀረ::

ይህ ሳይሳካ በመቅረቱ ሐሳቡን በሌላ መንገድ ተፈጻሚ ለማድረግ የንጉሡ አሽርጋጆች ካቴሪኒ ዘአራጐንን ተፋትታ በምን ኩስና ተወስና ገዳም ገብታ እንድትኖር ቢወተውቷትም እርሷ ግን ፈቃደኛ ሆና ባለመገኘቷ ሰላማዊ የሆነ ሌላ አማራጭ በመጥፋቱ በንጉሡ ግፊት በተመሩት የፓርላማው አባላት ውሳኔ መሠረት በ1532 ዓ.ም. የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ከሮሙ ፓፓ ከቀሌምን ጦስ ሰባተኛ አስተዳደረ ነጻ የወጣች መሆንዋን አወጀች:: ካርዲናል ዌልሴይም ፍችውን በተግባር ላይ ለማዋል ፈቃደኛ ስላልሆነ በን ጉሡ ትዕዛዝ ከሥልጣን ተወገደ:: የሮሙ ፓፓም ይህንን ድርጊት እንደሰማ ንጉሡንና ተባባሪዎቹን አወገዘ:: ዳሩ ግን ውግዘቱ ተቀባ ይነትን አላገኘም ነበር:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለፓፑ የሚላከው ገጸ በረከትና አሥራት ተቋረጠ::[1]

ንጉሥ ሔንሪ በእርሱ ኃላፊነት ቤተ ክርስቲያንዋን እንዲ መራ የካንተርቤሪ ሊቀ ጳጳስ አድርጎ በሾመው በክራንሜር ትዕዛዝ ከካቴሪኒ ጋር የነበረው ጋብቻ ተሠርዞ አን ቦሌይንን አገባ:: ቆየት ብሎም የንግሥት ኤልሳቤጥን እናት አን ቦሌይንን አመነዘረች በሚል ሰበብ ከፈታት በኋላ በ1537 ዓ.ም. ኤድዋርድ የተባለውን ወንድ ልጅ የወለደችለትን ጃን ሴይሙርን አግብቶ ነበር::

የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ከላይ በተገለጸው ሃይማኖታዊ ባልሆነና የንጉሡን ፈቃድ መሠረት ባደረገ ምክንያት ከሮማ ካቶ ሊክ ቤተ ክርስቲያን ተገንጥላ ራስዋን ብትችልም ቅሉ በአብዛኛው እምነትዋና ሥርዓትዋ የሮማ ካቶሊክን የመሰለ ነው:: በአንዳንድ መልኩ የኘሮቴስታንት ተጽእኖም ይንጸባረቅባታል::

የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዘመን ከክርስትና አስተ ምህሮ በወጣና የሰዎችን ፍላጐት ባገናዘበ መልኩ የምትወስናቸው ውሳኔዎች ክርስቲያኖችን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም እያስገረመ ያለ

[1] የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሉሌ መላኩ ገጽ 288





ጉዳይ ነው:: ወግ አጥባቂ በሆኑትና ለዘበተኛ አቋም ባላቸው መሪ ዎችዋ ለረዥም ጊዜ አከራካሪ የነበረው የሴቶች ቅስና መቀበል ጉዳይ በለዘበተኞቹ ድል አድራጊነት ከተደመደመ በኋላ ሴቶችን ወደ ጵጵስና ማዕረግ የማድረሱ ጉዳይም በመንገድ ላይ ነው:: በዚህ ፈር የለቀቀ ተግባርዋ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ለሌሎች የኘሮቴስታንት ክፍሎች ፋና ወጊ ሆናለች:: የእርሷን አሰረ ፍኖት በመከተል አብዛኞዎቹ የኘሮቴስታንት ክፍልፋዮች ግብረ ሰዶማዊ ያንን ሳይቀር በአገልጋይነት አሠማርተዋል::

በአሜሪካ ካሉት የኘሮቴስታንት ድርጅቶች በአንጻራዊነት ወግ አጥባቂ መሆንዋ የማነገርላትና 2.5 ሚሊዮን ተከታይ ያላት የኘሬስባይቴሪያን «ቤተ ክርስቲያን» እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ2001 ዓ.ም. ባብስ ሚለር የተባለች የእምነቱ ተከታይና በነገረ መለኮት ትምህርት የማስተርስ ዲግሪ ያላት ግብረ ሰዶማ ዊት ባቀረበችው የመብት ጥያቄ ላይ ለመወያየት የተሰበሰበው አጠቃላይ ጉባኤ 60 በመቶ የሚሆነው ተሰብሳቢ ግብረ ሰዶማውያን /gays and lesbians/ ለቅስና ማዕረግ ሊበቁ እንደሚገባ መስማማቱን ኦስተን አሜሪካን ስቴትስ ማን /Austin American States man/ የተሰኘው ዕለታዊ ጋዜጣ በጁን 21 2001 ዘገባው ላይ ዘግቦ ነበር::

የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ከክርስትና መስመር የወጣ አስደንጋጭና አሳፋሪ ውሳኔዎችን በመወሰን ተግባራዊ የምታደርገው የሴቶች መብት ተሟጋቾችም ሆኑ የሰዎች መብት ተሟጋቾች የመጽሐፍ ቅዱስን አስተምህሮ መሠረት አድርገው ለሚያሰሙት ትችትና ቅሬታ ፈጥና መልስ ለመስጠትና አባላትን ለማብዛት የምታደርገው ሩጫ ነው በማለት የሚተቹ አሉ::

ከመስመር የወጡ ውሳኔዎችን ፈጥና በመወሰንዋ ተግባራዊ በማድረግ የምትታወቀው «የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን» የግብረ ሰዶማውያን ቅስና መቀበልና በአገልግሎት ላይ መሠማራት አጀብ አሰኝቶ እያነታረከ ባለበት ወቅት ይባስ ይግረማችሁ ብላ በቅርቡ አንድ ግብረ ሰዶማዊ ቄስን ለጵጵስና ማብቃትዋን ለዓለም ይፋ አድርጋለች:: ይህንንም መገናኛ ብዙኃን በመቀባበል አስተጋብተውታል::

www.ethiopianorthodox.org

# 4.4 ሞርሞኒዝም

## «የኋለኞቹ ቅዱሳን የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን»

በአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት መባቻ ላይ ምዕራቡ የኒ ውዮርክ ግዛት የሉተርንና የካልቪንን እምነትና ሀሳብ በሚደግፉ የተለያዩ ድርጅቶች /denominations/ የተጥለቀለቀበት ወቅት ነበር:: የሞርሞኒዝም እምነት መሥራች ጆሴፍ ስሚዝ ምንም እንኳን ቤተሰቡ በሰሜን አሜሪካ በስፋት የተስፋፋው የፕሬስባይቴሪያን እምነት ተከታይ ቢሆንም እርሱ ግን እውነት በአንዳቸውም ውስጥ የለም በሚለው አቋሙ በወቅቱ እንደ አሸን ፈልተው በነበሩት የእምነት ድርጅቶች በአንዳቸውም ላይ እምነት አልነበረውም:: በርከት ላሉ ጊዜያት በአእምሮው ለተፈጠሩት ጥያቄዎች አጥጋቢና አሳማኝ መልስ ለማግኘት የብዙዎቹን ደጅ መርገጡንና ዳሩ ግን መንፈሱን የሚያረካ መልስ ከአንዳቸውም ባለማግኘቱ በግሉ መጽ ሐፍ ቅዱስን ሲያነብ «ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጎድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን ለእርሱ ይሰጠዋል» የሚለው የሐዋርያው የያዕቆብ መልእክት ለዘመናት የማይፈታ እንቆቅልሽ ሆኖበት ለነበረው ጥያቄ መልስ እንደሰጠ ውና በቃሉም መሠረት ወደ እግዚአብሔር አውትሮ በመለመኑ አብና ወልድ ተገልጸው ወደ እውነት እንደመሩት በእርሱም አማ ካይነት ከብዙ ዘመናት በኋላ እውነተኛዋ የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ለዓለም ይፋ እንደሆነች መለፈፍ ጀመረ::

የእምነቱ መሠረት ስለሆነው ስለመጽሐፈ ሞርሞን አመጣጥ ሲናገርም «በ1823 ዓ.ም. ምሽት ላይ በትሕትና ወደ ኤልሻዳይ መጸለይ ጀመርኩ እግዚአብሔርንም በመጥራት ላይ ባለሁበት ጊዜ ያለሁበት ክፍል በብርሃን ተጥለቀለቀ ብርሃኑም ከቀትር ፀሐይ እስኪበልጥ ድረስ ወዲያውም ከአልጋዬ አጠገብ በጣም ያሸበረቀ ነጭ ካባ የለበሰ መላ አካሉ ብርሃን የለበሰ ሰው ከመሬት ከፍ ብሎ በአየር ላይ ተንሳፎ ታየኝ በስሜ በመጥራትም ወደ እኔ የተላከ መልእክተኛ መሆኑን ስሙም ሞሮኒ እንደሚባል እግዚአብ ሔርም ለእኔ የምሠራው ሥራ እንደነበረው እናም ስሜም በሁሉም



www.ethiopianorthodox.org



ሀገሮች፣ ነገዶች፣ ቋንቋዎችና ሕዝቦች መካከል በጥሩና በመጥፎ እንደሚነሳ ነገረኝ::

ቀደም ያሉትን የዚህ አህጉር ነዋሪዎች ታሪክ እና የመጡበ ትን ምንጭ ከየት እንደሆነ የሚናገር በወርቅ ሰሌዳዎች ላይ ተጽፎ የተቀበረ መጽሐፍ እንዳለ ለጥንት ነዋሪዎች በአዳኙ የተሰጠውን የዘለዓለማዊውን ወንጌል ሙሉነትም በውስጡ እንደያዘ እንዲሁም ሁለት ድንጋዮች የብር ቅስት ውስጥ በደረት ኪስ ታስረው መቀበ ራቸውን የተሠሩትም ኡሪምና ቱሚም ከሚባለው እንደሆነ የእነዚህ ድንጋዮች ባለቤትና ተጠቃሚ የነበሩትም የጥንት ባለራእዮች መሆናቸውንና እግዚአብሔርም መጽሐፉን ለመተርጎም ዓላማ እነሱን እንዳዘጋጃቸው ነገረኝ:: ጊዜው ሳይደርስና ከእርሱም መልእ ክት ሳላገኝ ሰሌዳዎቹን ለማንም እንዳላሳይ አስጠነቀቀኝ ከዚያም ከእኔ ተሰወረ::»

ከዚህ በኋላ በኒውዮርክ በማንችስተር ኦንታሪዮ መንደር አጠገብ ካለው ኩሞራ ከተባለ ኮረብታ ከአንድ ቋጥኝ ስር ተደብቆ ማግኘቱን ጆሴፍ ስሚዝ ለሚቀርባቸው ሰዎች መናገር ጀመረ:: ከዚያም በ1830 ዓ.ም. መዝገቡን ወደ እንግሊዘኛ ቋንቋ «መጽሐፈ ሞርሞን» የሚል ርዕስ ሰጥቶ ተረጎመው:: እንደ ሞርሞኖች አነጋገር መዝገቡ በአንድ ሞርሞን በተባለ ታሪካዊ ነቢይ የተጠቀሱና ያጠሩ ሲሆን ጽሑፉን ካጠናቀቀ በኋላ መዝገቡን ለወንድ ልጁ ለሞሮኒ ሰጠው:: እርሱም ከራሱ ትንሽ ቃላት በመጨመር በኩሞራ ኮረብታ ውስጥ ሰሌዳዎቹን ደበቀ:: እ.ኤ.አ መስከረም 21 ቀን 1823 ዓ.ም. ይኸው ሞሮኒ ከሞተ የተነሣው ሰው ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ታየው:: እናም ስለጥንታዊው መዝገብና ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ስለመተር ጎሙ አስተማረው::

እንደ ሞርሞኖች አገላለጽ «መጽሐፈ ሞርሞን» በጥንታዊት አሜሪካ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች «ቅዱስ ታሪክ ነው»:: በጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት የተተረጎመው «መጽሐፈ ሞርሞን» ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ስድስት መቶ ዓመት ገደማ ሌሂ የተባለ ከነገደ ዮሴፍ የሆነ እስራኤላዊ በትንቢተ ነቢያትና ለእርሱ ለራሱ በታየው ራእይ ተመርቶ ኢየሩሳሌም ከመጥፋትዋ በፊት ራሱንና ቤተሰቡን ከጥፋት ለማዳን መላ ቤተሰቡን ይዞ ከኢየሩሳሌም ወደ ምድረ በዳ መሸሹን ከልጆቹ ታናሹና በእርሱ መንፈስ የተጓዘው

ባለራእዩ ኔፊ በመዘገበው ታሪክ ተነስቶ የአንድ ሺ ዘመናት ታሪክን በመቀባበል በሚተርኩት ኔፋውያን «ነቢያት» ታጅቦ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድኅረ ልደተ ክርስቶስ ላይ በመጨረሻው ዘጋቢ «ሞሮኒ» በተባለው መዝገብ ይቋጫል::

እንደ መጽሐፉ አገላለጽ ከክርስቶስ ልደት በፊት ስድስት መቶ ዓመት ገደማ ከኢየሩሳሌም የወጡት የሌሂ ዘሮች በምድረ በዳ ለ30 ዓመታት ያህል ተንከራተው በመጨረሻ «የቃል ኪዳንዋን ምድር»፣ «ከምድር ሁሉ በላይ የተመረጠችውን ምድር» ማለትም ምድረ አሜሪካን ይረግጣሉ:: ይኸውም በ570 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ማለት ነው::

«የቃል ኪዳንዋ ምድር» /ምድረ አሜሪካ/ ከእግዚአብሔር የተሰጠቻቸው የሌሂ ዘሮች እርስ በእርሳቸው ባለመስማማታቸው የተነሣ በየጊዜው ይጣሉ ነበር:: የሌሂ ታላቅ ልጅ የሆነው የላማን ዘሮች እንደ አባታቸው በክፉ መንፈስ የሚመሩ በመሆናቸው ብዙውን ጊዜ በእግዚአብሔር መንፈስ በሚጓዙት የኔፊ ዘሮች ላይ በጠላትነት ይነሱባቸው ነበር:: በኋላም ኔፋውያንና ላማናውያን ተብለው ወደ ሁለት ሀገሮች ይከፈላሉ:: የኋላ ኋላ ግን ላማናውያን ኔፋውያንን ጨርሰው ከምድሪቱ ያጠፋአቸዋል:: የምድሪቱ ብቸኛ ወራሽም ይሆናሉ:: እንደ ሞርሞኖች እምነት ላማናውያን የዋናዎቹ የአሜሪካ ሕንዶች አባቶች ናቸው::

«መጽሐፈ ሞርሞን» ለሞርሞናውያን በምድር ካሉ መጻሕፍት ሁሉ የበለጠ ትክክልና የእምነታቸውም የማዕዘን ድንጋይ ነው:: በመጽሐፉ የተካተቱት ኔፋውያን በተባሉት «ባለራእዮች» የታዩ ናቸው የተባሉት ራእዮች በአብዛኛው በመጽሐፍ ቅድስ በነቢያት የተነገረው ትንቢትና የታየው ራእይ በሌሎች ስም የቀረበ እስኪ መስል ድረስ እጅግ ተመሳሳይነት አለው::

ቀዳማዊ ኔፊ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በራእይ ማየቱን እንዲህ ሲል ገልጾአል «ታላቂቱን የኢየሩሳሌም ከተማ እናም ሌሎች ከተሞችን አየሁ:: እናም የናዝሬትን ከተማ ተመለከትኩ:: በናዝሬት ከተማም አንዲት ድንግል ተመለከትኩ:: እርሷም እጅግ ውብና ያማረች ነበረች:: አንድ መልአክም ከሰማይ ወርዶ በፊቴ ቆመ እናም ኔፊ ምን ትመለከታለህ አለኝ? አንዲት ከድንግሎች ሁሉ በላይ መልካም በጣም ቆንጆ ድንግል በማለት





ተናገርኩት:: እርሱም እነሆ የተመለከትካት ድንግል በሥጋ የእግዚአብሔር ልጅ እናት ናት አለኝ»[1] ይህ ራእይ የታየበት ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት ስድስት መቶ ዘመን ቀደም ብሎ መሆኑ በመጽሐፉ ተገልጾአል::

ኔፊ የጌታን በቤተልሔም መወለድ፣ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ መጠመቅ፣ በአይሁድ ቅንአት እንደሚሰቀል፣ እንደሚሞት፣ ከሙታን ተለይቶ እንደሚነሣ፣ ከዚያም ማረጉን ሁሉ አስቀድሞ በትንቢት መስታወትነት አይቶ እንደነበር በመጽሐፉ ተገልጾአል::

መጽሐፈ ሞርሞን እንግዳና አስገራሚ ትረካዎችም ተካተው በታል:: ለምሳሌ የሚከተለውን ለአብነት ያህል ብንጠቅስ ክርስቶስ ባረገበት በ34 ዓ.ም. ኔፋውያን ለጋስ ምድር ብለው በሚጠሯት ምድረ አሜሪካ አስቀድመው በሠሩት ቤተ መቅደስ ተሰብስበው ሳለ ከሰማይ ድምፅ ይመጣል:: «እነሆ በእርሱ ደስ የሚለኝ ስሜንም የማከብርበት የምወደው ልጄ ይህ ነው:: እርሱን ስሙት» በማለት አብ ከሰማይ ሲናገር ነጭ ልብስ የለበሰ አንድ ሰው ከሰማይ ወርዶ በመካከላቸው ቆመ «እነሆ ነቢያት ወደ ዓለም ይመጣል ብለው የመሰከሩልኝ እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ» ባለ ጊዜ በዙሪያው የነበሩት ሁሉ በመሬት ላይ ወደቁ «እርሱም ተነሱ ወደ እኔ ኑ ብሎ የችንካሩን ምልክት የተቸነከረ እጆቹንና እግሮቹን ለሕዝቡ አንድ በአንድ እየጠራ አስዳሰሳቸው:: ኔፊንም ከሕዝቡ መካከል ጠርቶ በድጋሚ ወደ ሰማይ በምወጣበት ጊዜ ይህን ሕዝብ እንድታጠምቅ ሥልጣንን እሰጥሃለሁ» አለው:: ሌሎችንም ጠርቶ እንዲያጠምቁ ሥልጣንን ሰጣቸው የተጠሩትና ለማጥመቅ ኃይልና ሥልጣን የተቀበሉት አሥራ ሁለት ነበሩ::[2]

ከተመረጡት አሥራ ሁለቱ ውስጥ ዘጠኙ በጥያቄአቸው መሠረት ሲሞቱ መንግሥተ ሰማያትን እንደሚወርሱ ማረጋገጫ ሲሰጣቸው ቀሪዎቹ ሦስቱ ግን ፍላጐታቸው ለዘላለም ሕያው ሆነው በምድር ላይ እንዲኖሩ ስለነበር የልባቸውን ሐሳብ ጌታ አውቆ

1. 1ኔፊ. 11÷13-18
2. 3ኔፊ. 11 ና 12



www.ethiopianorthodox.org

ምርጫቸው አመስግኑአቸው እስከ መጨረሻው ሞትን ሳይቀምሱ በምድር ላይ ስለ እርሱ እየመሰከሩ እንደሚኖሩ አረጋግጠላቸው ተለይቷቸው ማረጉንና በቃሉ መሠረትም ዘጠኙ ኋላ ላይ ሲሞቱ ሦስቱ ግን እስከ ዛሬ በምድር ላይ እንዳሉ ተጽፏል::[1]

የዋናዎቹ የአሜሪካ ሕንዶች አባቶች ናቸው የተባሉት ላማናውያን ነጭና ቆንጆ ነበሩ ከተባሉት ወንድሞቻቸው ኔፋውያን ተለይተው መጥቆራቸው በክፋታቸው ምክንያት በደረሰባቸው መርገም መሆኑን ዳግማዊ ኔፊ የተባለው እንዲህ በማለት ገልጾታል «እነሆም በእርሱ ላይ ልባቸውን አጠጠሩ እንደ ድንጋይም ሆኑ ስለዚህ እነርሱ ነጭ እና ቆንጆ እንዲሁም ያማሩ በመሆናቸው ለሕዝቤ የሚስቡ እንዳይሆኑ ጌታ እግዚአብሔር ቆዳቸውን አጠቆረው»[2]

አሜሪካ በቀል ከሆኑት የእምነት ድርጅቶች አንዱና ቀደምት የሆነው ሞርሞኒዝም ምንም እንኳን ክርስትናን መነሻ አድርጎ የተቋቋመ ቢሆንም የእምነቱ መሠረትና መመሪያ የሆነው «መጽሐፈ ሞርሞን» በመሆኑ በክርስትና ስም ከተቋቋሙት ሁሉ ልዩ ያደርገዋል::

ሞርሞኖች በብዛት ሠፍረው የሚገኙት በሰሜን አሜሪካ ዩታ ተብሎ በሚጠራው ከተማ ሲሆን ሚዩዝሪ እስቴትም ሌላኛዋ መናኸሪያቸው ነች:: እንደውም ሞርሞኖች እንደሚያምኑት ሚዩዝሪ እስቴት በመጨረሻው ዘመን የክርስቶስ መንግሥት የሚመሠረትባት ከተማ ናት:: «በመጨረሻው ዘመን የእግዚአብሔር ቤት ተራራ በተራሮች ራስ ላይ ጸንቶ ይቆማል:: ከኮረብቶችም በላይ ከፍ ከፍ ይላል:: አሕዛብም ወደ እርሱ ይጎርፋሉ»[3] ተብሎ በነቢዩ ሚኪያስ እንዲሁም «በዘመኑ ፍጻሜ የእግዚአብሔር ቤት ተራራ በተራሮች ራስ ላይ ጸንቶ ይቆማል:: ከኮረብቶችም በላይ ከፍ ከፍ ይላል:: አሕዛብም ወደ እርሱ ይሰበሰባሉ» ተብሎ በነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢት የተነገረው «በቃል ኪዳንዋ ምድር» በአሜሪካ ለምትገኘው

1. 3ኔፊ. 28÷1-40
2. 2ኔፊ. 5÷21
3. ሚኪ. ፬÷፩





ሚዩዝሪ እስቴት መሆኑን ይናገራሉ:: ሐዋርያው ዮሐንስ በራእዩ ያያትና «ቅድስቲቱ ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም»[1] በማለት የገለጻትን ኤተር የተባለው የሞርሞኖች ነቢይ በመጽሐፈ ሞርሞን ላይ እንዲህ በማለት ገልጾአታል «ለዮሴፍ ቅሪቶችም ምሳሌ ትሆን ዘንድ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም በዚህች ምድር/በአሜሪካ/ ትገነባለች::»[2]

ኔፊ የተባለው የሞርሞኖች ሌላው ነብይም «ከአባታችሁ ከያዕቆብ ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳን እፈፅም ዘንድ ይህን ሕዝብ በዚህች ምድር /አሜሪካ/ እመሠርታለሁ:: እርሷም አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ትሆናለች:: እናም የሰማይ ሥልጣናትም በዚህ ሕዝብ መካከል ይሆናሉ::»[3] በማለት ተናግሯል:: ምንም እንኳን መጽሐፈ ሞርሞን «አዲሲቱ ኢየሩሳሌም» በምድረ አሜሪካ እንደምትመሠረት ቢገልጽም እስከ 1831 ዓ.ም. /እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር/ ትክክለኛው ቦታ ተለይቶ አይታወቅም ነበር:: በዚሁ ዘመን ግን በጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት ሚዩዝሪ እስቴት የኋለኞቹ ዘመናት ቅዱሳን መሰብሰቢያ የሆነችው «አዲሲቱ ኢየሩሳሌም» /ጽዮን/ የሚገነባባት ከተማ መሆንዋ በመገለጹ ሞርሞኖች በሚዩዝሪ እስቴት ቦታ እየገዙ መሰባሰብ ጀመሩ:: ብዙ ሞርሞኖች ንብረታቸውን በሚዩዝሪ እስቴት እንደሚያከማቹ ይነገራል:: ምክንያቱም ባለማለፍ ጸንታ የምትኖር ዘላለማዊ ርስታቸው /የኋለኛዋ ዘመን ጽዮን/ መሆንዋን ነብያቸውና የእምነቱ መሥራች አረጋግጠላቸዋልና::

## የሞርሞኖች ዶክትሪን

- በሥላሴ እናምናለን ይሉና አካላዊነታቸውን ሲገልጹ አብና ወልድ እንደ ሰው የሚጨበጥ የሚዳሰስ ውሱን የሆነ አካል እንዳላቸው መንፈስ ቅዱስ ግን ዝርው መንፈስ መሆኑን ያምናሉ::[4]

1. ራእይ ፳፩÷፪
2. ኤተር 13÷6
3. 3ኔፊ. 20÷22
4. Articles of Faith P.38



www.ethiopianorthodox.org

- ማንኛውም ሰው የሚቀጣው ራሱ በሠራው ኃጢአት እንጂ በአዳም ኃጢአት የሚቀጣ ማንም የለም:: ሕፃናት ያለ ጥምቀት መዳን ይችላሉ:: እንዲሁም ሕፃናትን ማጥመቅ በእግዚአብሔር ፊት ከባድ ፌዝ ነው::[1]
- የመጀመሪያው የወንጌል ሕግ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን፣ ሁለተኛው ንስሐ ሦስተኛው ስርየተ ኃጢአት የሚገኝበት ጥምቀትና አራተኛው በአንብሮተ እድ የሚገኘው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ መሆኑን ያምናሉ::[2]
- ልሳን በመናገር እንዲሁም በመተርጎም፣ በራእይ፣ በፈውስ በመሳሰሉት ያምናሉ::
- መጽሐፍ ቅዱስ በአግባቡ ከተተረጎመ የእምነታቸው መመሪያ እንደሚሆን ሲናገሩ መጽሐፈ ሞርሞን ግን የእምነታቸው የማዕዘን ራስ ነው[3]
- በእስራኤል እንደገና መሰብሰብና በአሥሩ ነገድ እንደገና መመሥረት ያምናሉ:: እንዲሁም አዲሲቱ ኢየሩሳሌም /ጽዮን/ በምድረ አሜሪካ በሚዩዝሪ እስቴት እንደምትገነባ ኢየሱስ ክርስቶስም በአካል መጥቶ መንበረ መንግሥቱን በሚዩዝሪ እስቴት ላይ አድርጎ እንደሚገዛ የኋለኞቹ ቅዱሳን ለእርሱ ባለሟል እንደሚሆኑ ያምናሉ[4]

እንደ ሞርሞኖች አስተምህሮ በዚህች ዓለም ላይ ሁለት ዓይነት አብያተ ክርስቲያናት አሉ:: እነርሱም የሰይጣንና የኢየሱስ እያንዳንዱ ሞርሞን የእርሱ «ቤተ ክርስቲያን» በዓለም ላይ ካሉት ሁሉ ብቸኛዋ «የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን» መሆንዋን ሲያምን ሌሎቹን ግን የዲያብሎስ ተቋም እንደሆኑ ያለማመንታት ይናገራል::

1. Articles of Faith P.47, ሞሮኒ 8÷9-13
2. Articles of Faith P.87-105
3. Articles of Faith P.214, 247
4. Articles of Faith P.297, 320





# 4.5 አድቬንቲስት

ምጽአተ ክርስቶስ በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጸ፣ በክርስቲያኖች ዘንድም የታመነ የማይቀርና የሚሆን ክስተት ነው:: ዳሩ ግን መቼ እንደሚሆን ከፍጡር ኅሊና የተሰወረና ፈጽሞ የማይታወቅ ለመሆኑ ጌታ ራሱ «ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ የሰው ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም»[1] በማለት አረጋግጦልናል::

አሜሪካዊው ገበሬ ዊልያም ሚለር ግን የምጽአት ቀን ከፍጡራን እውቀት ውጭ መሆንዋ በማይታበል የጌታ ቃል ተረጋግጦ ሳለ እርሱ ግን ይህቺ ቀን በእርሱ ዘንድ መታወቅዋን መስበክ ጀመረ:: በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ ስምንት ቁጥር አሥራ አራት ላይ የሠፈረውን[2] መነሻ አድራጎ በእርግጠኝነት ምጽአተ ክርስቶስ እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ1844 ዓ.ም. እንደሚሆን ያለምንም እፍረት አወጀ::

በመላው አሜሪካ የተናኘው ይህ የዊሊያም ሚለር ትንቢት የወቅቱ ዐቢይ የመነጋገሪያ ርዕስ ሆነ:: የባፕቲስት ድርጅት ለሚለር የሰባኪነት ፈቃድ ሰጠ:: ጋዜጦች፣ መጽሔቶች የሚለርን የምጽአት ስብከት ማራገብ ጀመሩ:: ሚለር የጎሰመው የምጽአት ቀን ነጋሪት የብዙዎችን ልብ ያሸበረ ስለነበር ብዙዎች የሚለር ትምህርት ሰለባ ሆኑ::

«አድቬንት» የሚለውና የክርስቶስን ዳግም ምጽአት የሚገለጸውን የእንግሊዝኛ ቃል በመጠቀም የምጽአት ቀን ናፋቂዎቹ የሚለር ተከታዮች «አድቬንቲስት» የሚል መጠሪያ ያዙ:: የአጋጣሚ ነገር ሆኖ በወቅቱ በዓለም ላይ የተከሰቱ አንዳንድ እንግዳ ክስተቶች ለሚለር «ገበሬ አስደንግጥ» ስብከት ተደማጭነት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አድርገው ነበር::

እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በኖቬምበር 13፣ 1833 ዓ.ም. የተከሰተው የከዋክብት ወደ ምድር ከባቢ መዝለቅ

1. ማቴ. ፳፬፥፴፮



www.ethiopianorthodox.org

/meteoric shower/ ከዚህ በፊት ፈጽሞ ያልታየና ያልተመዘገበ እጅግ አስገራሚ አስደንጋጭም ክስተትን በዓለም ላይ ፈጥሮ ያለፈ መሆኑ በዘርፉ ላይ በተሰማሩት ምሁራን የተሰጠው አስተያየት የምጽአት ዋዜማ ላይ ለመሆናችን አመልካች ነው በማለት ሚለራ ውያን ለስብከታቸው ማጣፈጫ ጨው አድርገው ተጠቅመውበታል። «ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ። ፀሐይም እንደ ማቅ ጠጉር ጥቁር ሆነ ጨረቃም በሞላው እንደ ደም ሆነ። በለስም በብርቱ ነፋስ ተናውጣ ቃሪያዋን ፍሬ እንደምትጥል የሰማይ ከዋክብት ወደ ምድር ወደቁ ሰማይም እንደ መጽሐፍ ተጠቅልሎ አለፈ። ተራራ ዎችና ደሴቶችም ሁሉ ከስፍራቸው ተወሰዱ»[1] የሚለው የዮሐንስ ራእይ ከወቅታዊው ክስተት ጋር እየተነጻጸረ በሚለራውያን ይመሰጠር፣ ይተነተን ነበር።

«ሚድናይት ክራይ» በሚል ርዕስ በራሱ በሚለር ይዘጋጅ የነበረው ጽሑፍም ሚለር ተከታዮቹን ለ1844 ዓ.ም. የምጽአት ቀን እንዲዘጋጁ የሚቀሰቅስበት ነበር። በሚለር ደጋፊዎችም ሆነ ተቃዋሚዎች ዘንድ በጉጉት ትጠበቅ የነበረችው ቀን እየተቃረበች በመጣች ጊዜ የሰውን አእምሮ የወጠሩና በጭንቀት ማጥ የከተቱ የተለያዩ መልእክቶች ይተላለፉ ነበር። ሰማይ በመብረቅ እንደሚ ታረስ፣ ሰማይና ምድር እንደ ጨርቅ ተጠቅልለው እንደሚያልፉ፣ የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ እንደሚሉ፣ ሁሉም ወደ ሰማይ እንደሚነጠቅ...

በ1844 ዓ.ም. በዓለም ላይ የተለየ ነገር አልተከሰተም። ለሚለራውያን ግን ይህቺ ዕለት ከዋክብት ነፋስ አማቶ እንደሚያረ ግፈው የዛፍ ቅጠል ከሰማይ የሚረግፉበት፣ ፀሐይ ማቅ የምትለብ ስበት፣ ሰማይና ምድር ከመሠረታቸው የሚናወጡባትና ክርስቶስ በእልፍ አእላፋት መላእክት ታጅቦ የሚገለጽባት ቀን ነበረች።

1844 ዓ.ም. እንደ ዋዛ ካለፈ በኋላ የሚለር ተቃዋሚዎች የስላ የሂስ ብዕራቸውን አሹለው ተነሡ። ሚለራውያንም የማስተ ባበል ሥራቸውን ገፉበት። የኋላ ኋላም «አድቬንቲስት» በሚለው መጠሪያ የተደራጁት የሚለር ተከታዮች ለሦስት ተከፈሉ።

1. ራእይ ፮፥፲፫ና፲፬





የመጀመሪያዎቹ «ዘሰቨንዝ ዴይ ,አድቬንቲስት» በሚል ስም ሲጠሩ ሰንበት ቅዳሚት መሆንዋን የሚያምኑና የእሑድን ሰንበትነት የማይቀበሉ እንዲሁም የሰው ሁሉ ነፍስ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ በመቃብር ውስጥ እንደምትኖር አድርገው የሚያስ ተምሩ ሲሆኑ ሁለተኛዎቹ ደግሞ «ዘ አድቬንት ክርስቲያን ቸርች» በሚል ስም ሲጠሩ የእሑድን ሰንበትነት አምነው የተቀበሉ ናቸው። ሦስተኛዎቹ «ዘቸርች ኦፍ ጐድ ኦፍ ዘአብርሃሚክ ፌዝ» የሚባሉት ሲሆኑ ሰንበትን በተመለከተ ከሁለተኛዎቹ ጋር አንድ ናቸው።

## 4.6 ባሃኡላህ

በአሜሪካ ሚለራውያን፣ በአውሮፓ ደግሞ ቴምኘላሮች የነ ገረ ምጽአት ነጋሪትን በሚጎስሙበት ወቅት መካከለኛው ምሥራ ቅም ቁርአንና የእስልምና አዋልድ መጻሕፍትን መሠረት ባደረጉ የምጽአት ቀን ተንባዮች ተጥለቅልቆ ነበር። ፍጻሜ ዓለም መቃረ ቡን ከሚያቀነቅኑት መካከል በኢራን ሀገር ከምትገኘው ከሺራዝ ከተማ የተነሣውና በታሪክ ባብ /ሲወለድ የወጣለት ስሙ ሰይድ ዓሊ መሐመድ ነው/ በመባል በታወቀው ወጣት ነጋዴ የተጠነሰሰው ንቅናቄ አንዱና ዋነኛው ነበር።

ከ1844-1853 ዓ.ም. ባሉት ጊዜያት በሁሉም ደረጃ ላይ የነበሩ የኢራን ተወላጆች የእግዚአብሔርን ቀን መድረሱንና ባብም ራሱ በእስልምና ሃይማኖት ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚመጣ ትን ቢት የተነገረለት መሆኑን በሚገልጸው በእርሱ አዋጅ በተቀሰቀ ሰው የተስፋ ማዕበል ተጥለቅልቀው ነበር።

የባቢዎች እምነትና አዋጅ የመለኮታዊ ግልጸት ሂደት ከመ ሐመድ መምጣት ጋር ማክተሙንና ይህን የሚቃረን ነገር መናገ ርም በሞት የሚያስቀጣ ክህደት መሆኑን ከሚያምኑትና ከሚያስተ ምሩት የእስልምና እምነት መሪዎች ከፍተኛ ተቃውሞ አስነሳ። ባብና ተከታዮቹም ተወገዙ። የኢራን መንግሥትም በሺህ የሚቆጠ ሩ የአዲሱ እምነት አራማጆችን አስወገደ። ባብም ሐምሌ 9 ቀን 1850 ዓ.ም. በሕዝብ ፊት እንዲረሸን ተደረገ።[1]

1. ባሃኡላህ ገጽ 4

www.ethiopianorthodox.org

በባብ እምነት ተስበውና ተማርከው እንቅስቃሴውን ከተቀላ ቀሉት ታዋቂ ሰዎች ውስጥ ባሃኡላህ አንዱና የታወቀ ስለነበር ተይዞና በሰንሰለት ታስሮ በባዶ እግሩ ወደ ቴህራን ተወሰደ። ባሃኡላህ የቃሉ ትርጉም የእግዚአብሔር ክብር ማለት ሲሆን ሲወለድ የተሰጠው ስም ሁሴን ዓሊ የሚል ነበር። በአንድ በኩል በጣም በታወቀው የግል ዝናውና ቤተሰቡ በኢራን ሕዝብ ዘንድ በነበረው ደረጃ በሌላ በኩል ደግሞ የባቢዎች መፈጀት በምዕራባውያን ኤምባሲዎች ዘንድ በቀሰቀሰው ተቃውሞ በመደገፉ ባሃኡላህ የሞት ፍርድ ሳይፈረድበት ቀረ። ዳሩ ግን እጅግ በከፋና በከረፋ በተባይ በተወረረ ከመሬት ወለል በታች በሚገኝ «የጨለማው ጉድጓድ» በመባል በታወቀው «ሲያህቻል» እስር ቤት ውስጥ መታ ሰሩንና ተልእኮውንም በዚህ እስር ቤት ውስጥ በ1852 ዓ.ም. መጀ መሩን የእምነቱ ተከታዮች ይገልጻሉ።[1]

ከእስር ቤት ከወጣ በኋላ በግዞት ወደ ኢራቅ በመጓዝ በዚያ ያሉትን የእምነቱን ተከታዮች በማሰባሰብ እምነቱን ማደራጀቱን ቀጥሏል። ቀስ በቀስ በጽሑፎቹ አማካይነት አመለካከቱ ወደ ሌላው ዓለም ተዛምቷል። የባሃኡላህ እምነትና ተልእኮ ሁሉንም የእምነት ክፍሎች በአንድነት የሚያስተሳስር እንደሆነ ተከታዮቹ ይናገራሉ። በእነርሱ ዘንድ ቡድሀ፣ ክርስቶስ፣ መሐመድ እና ሌሎችም እኩል ቦታ አላቸው። ከሁሉም እምነት መልካም መልካሙን መርጦ በሕይወት መተግበር የእምነታቸው መመሪያ ነው። ከዚህ አልፎ ይህ ነው የሚባል የሃይማኖት አቋም የላቸውም። ምዕራባውያን «ዲሞክራሲያዊ ሃይማኖት» በማለት ያሞካሹታል። በ1988 ዓ.ም. እንደ ወጣው ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ ዓመታዊ መጽሐፍ አገላለጽ በዓለም ላይ የበሃኢ እምነት ተከተዮች ቁጥር አምስት ሚሊዮን እንደሆነና በ155 ሀገራት የባሃኢ ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባኤያት እንደሚገኙ ተገልጾአል። በእስራኤል ሀገር በሃይፋ የሚገ ኘው ጽ/ቤታቸው እጅግ ማራኪና በብዙ ቱሪስቶች የሚጎበኝ ነው።

1. ባሃኡላህ ገጽ 3





## 4.7 የይሖዋ ምስክሮች /Jehovah Witnesses/

*«ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶቹ ሆነው ይመላለሳሉና ብዙ ጊዜ ስለ እነርሱ አልኋችሁ አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላለሁ መጨረሻቸው ጥፋት ነው። ሆዳቸው አምላካቸው ነው፣ ክብራቸው በነውራቸው ነው አሳባቸው ምድራዊ ነው»*

*ፊልጵ. ፫÷፲፰ና፲፱*

መናፈሻ ውስጥ ተቀምጠው ወይም አውቶቡስ ማቆሚያ ስፍራ ላይ ቆመው ወይም እየሔዱ ሳለ ከረባት ያሠሩና ቦርሳ የያዙ ሰዎች መጥተው ድንገት ሰላምታ በመስጠት «የመጠበቂያ ግንብ» የምትል መጽሔት ወይንም ደግሞ ጠንካራ ሽፋን ያላት አነስተኛ መጽሐፍ ሰጥተው መጠነኛ ክፍያ የሚጠይቁና በዚያው አያይዘው ስብከታቸውን የሚቀጥሉ ሰዎች አጋጥመዎት አያውቁም? ካጋጠመዎት እነርሱ ሌሎች አይምሰልዎት ያለምንም ጥርጥር «የይሖዋ ምስክሮች» ናቸው።

በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማብቂያ ላይ እንደተነሱት ኩኤከር እንደሚባሉት የፕሮቴስታንት ክፍልፋዮች ሁሉ እነዚህም ቄስና ቤተ ክርስቲያን የሌላቸው ናቸው። ኩኤከሮች የውስጥ ብርሃን የሚሉት እውነተኛው ሃይማኖት በእያንዳንዱ ውስጥ ስለሚገኝ እውነተኛ አማኞች የሚገናኙበት ቦታ ሁሉ የተቀደሰ ነው ብለው ያምናሉ። በግል ቤቶች ውስጥ ይሰበሰባሉ። የሣር ድርቆሽና እህል በሚከማችበት ቤት ውስጥ ይገኛሉ። በየትም ግልጽ ቦታና በገበያ ስፍራ አንድነት ስብሰባ ያደርጋሉ።

የይሖዋ ምስክሮችም እንደ ኩኤከሮች በመናፈሻ ቦታ ይገኛሉ፣ በአውቶቡስ ማቆሚያ ይቆማሉ፣ በመንገድ ዳር ቆመው ኃላፊ አግዳሚውን ወጪ ወራጁን እጅ እየነሱ በማስቆም ያለፍላጎቱ የእምነታቸው ተሳታፊ እንዲሆን ይወተውቱታል። ይህ የድርጅታቸው መርሆ በመሆኑ ነው አማኞቹ በዚህ ተግባር ላይ ተጠምደው የሚውሉት።

የዚህ ድርጅት ጥንተ መሠረቱ ብሔረ ሙላዱ ምድረ አሜሪካ ናት። የት መጣው እንዴት ነው? ቢሉ በ325 ዓ.ም. በኒቂያ በተደረገው ጉባኤ «ወልድ ፍጡር» ያለው አርዮስ ተወግዞ ከቤተ

www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያን አንድነት ተለየ:: በ381 ዓ.ም. ደግሞ መቅዶንዮስ
«መንፈስ ቅዱስ ሕፁፅ» በማለቱ በጉባኤ ቁስጥንጥንያ ተወገዘ::
የእነዚህ መናፍቃን የኑፋቄ ትምህርት በእነ ቅዱስ አትናቴዎስና
በእነቅዱስ ጎርጎርዮስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ግብአተ መሬቱ
ተፈጽሞ ሳለ በአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማብቂያ ላይ
ቻርልስ ቴዚ ሩስል የተባለው አሜሪካዊ መፍቀሬ አርዮስ ወመቅዶ
ንዮስ ሆኖ ኑፋቄያቸውን ከመቃብር ምሶ አውጥቶ ዳግም የክርስትና
ትምህርት እንደሆነ ለማሳመን በክርስትናው ዓለም መድረክ ላይ
አቆመው:: ምንም እንኳን አርዮሳውያንና መቅዶኖሳውያን ጨርሰው
ከገጸ ምድር ያልጠፉ ቢሆንም ቅሉ ክህደቱ ጎልቶ የተሰበከው
በቻርልስ ሩስልና በተከታዮቹ ነው::

የአሁንዋ የፒተስበርግ ክፍል በምትሆነው በፔንሲልቫንያ
እ.ኤ.አ በ1852 ዓ.ም. የተወለደው ቻርልስ ቴዚ ሩስል በዘመኑ
ከነበሩት «አብያተ ክርስቲያናት» የተለየ አቋምና አመለካከት ስለ
ነበረው የራሱን ድርጅት ለማቋቋም ዓላማ ነበረው:: በተለይም
«ሁሉም ነገር አስቀድሞ በእግዚአብሔር የታወቀና የተወሰነ ነው::
ስለዚህ ሰው በገዛ ኃይሉ ሊለውጠው የሚችለው አንዳችም ነገር
የለም» የሚለውና «ዘላለማዊ ቅጣት አለ» የሚለው የብዙዎቹ አብ
ያተ ክርስቲያናት አስተምህሮ ስለሆነ ይህን በመቃወም «የመጽሐፍ
ቅዱስ ጥናት» በሚል ሰበብ በአካባቢው የሚገኙትን ወጣቶች እያሰ
ባሰበ በራሱ እምነትና አመለካከት መቅረጽ ጀመረ:: ቀስ በቀስ
ሩስል እርሱን በዓላማና በአመለካከት የሚመስሉ ብዙ ሰዎችን
አፈራ:: ኑፋቄውንም በመጽሐፍት እያሳተመ ማሠራጨት ጀመረ::

እ.ኤ.አ በ1881 ዓ.ም. «ጽዮን ዎችታዎር ትራክት ሶሳይቲ»
የሚለውን ድርጅት ከመሰሎቹ ጋር ሆኖ አቋቋመ:: በዚህ ተቋም
አማካይነትም የተለያዩ የይሖዋ ምስክሮችን የእምነት አቋም የሚገ
ልጹ ትራክቶች፣ መጽሔቶችና መጻሕፍቶች እየታተሙ ለመላው
ዓለም ይሠራጫሉ:: የዚህ ድርጅት መስራችና የመጀመሪያው ኘሬ
ዝዳንት የሆነው ሩስል የቅሌት ማኅደር እንደነበር የታሪክ መዛግ
ብት ያስረዳሉ:: በ1879 ዓ.ም. ማርያ ፍራንሲስ ከተባለችው ሴት
ጋር ትዳር የመሠረተ ቢሆንም በነዝናዛነቱና በዋልጌነቱ ምክንያት
ትዳሩ ፈርሰዋል:: ለትዳራቸው መፍረስ ዋናው መንስኤ የሩስል
እኩይ ምግባርና ጠባይ መሆኑን ባለቤቱ ስትገልጥ «ሩስል ራሱን





ወዳድ ተመጻዳቂ፣ ከሁሉ በላይ ነኝ ባይ እንዲሁም ደግሞ ከሌሎች
የእምነቱ ተከታዮች ከሆኑ ሴቶች ጋር የሚማግጥ ነው» ብላለች::[1]

ሌላው የሩስል ቅሌት «ታምረኛ ስንዴ» በማለት ገቢውን
ለማዳበር በማሰብ ገበሬዎችን በማታለል ለስንዴ አምራቾች በውድ
ዋጋ የሸጠውና ብዙ ብር ያጋበሰበት ስንዴ ጉዳይ ነው:: «ተአምረኛ
ስንዴ» ተብሎ በሩስል የተሞካሸው ስንዴ ከዚህ በፊት ካለው
የስንዴ ዘር ተለይቶ አምስት እጥፍ ምርት እንደሚያስገኝ በመገናኛ
ብዙኃን ሳይቀር እንዲለፈፍ አደረገ:: ከፍተኛ ምርት ለማግኘት
ጉጉት ያደረባቸው አምራቾች «ታምረኛውን ስንዴ» በውድ ዋጋ
ገዙ:: ዳሩ ግን «ተአምረኛው ስንዴ» ተአምር የሚያሰኝ ምርት
ሊሰጥ ቀርቶ ከተራው የስንዴ ዘር ያነሰ ምርት ነበር የሰጠው::[2]

የሩስል ቅሌት መች በዚህ ብቻ ቆመ:: ራሱን ከነብያት
ጎራ አሰልፎ ሀብተ ትንቢት እንደተሰጠው ሁሉ የክርስቶስን ዳግም
ምጽአት ተነበየ:: «የክርስቶስ መንግሥት ከ1874 ዓ.ም. ጀምሮ
መግዛት ትጀምራለች ማለትም ክርስቶስ ይገለጣል:: የዓለም ፍጻሜ
ደግሞ በ1914 ዓ.ም. ይሆናል»[3] ብሎ ነበር::

እ.ኤ.አ. በ1916 ዓ.ም. ሩስል ሲሞት የድርጅቱን መሪነት
ሩዘርፎርድ የተባለው ሰው ተረከበ:: ሁለተኛው የዎችታወር ሶሳይቲ
ኘሬዝዳንት የሆነው ሩዘርፎርድ «ክርስቶስ ከነሥጋው አላረገም
ሥጋውን በሁለተኛው ሰማይ ላይ አስቀምጦታል ለወደፊት ክርስቶስ
መጥቶ ሺህ ዘመን በሚገዛበት ጊዜ ለወገኖቹ እንደ ዐውደ ርእይ
ያሳያቸዋል» የሚል የኑፋቄ ትምህርት አስተምሯል::

## የይሖዋ ምስክሮች እምነትና አስተምህሮ

- በእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት አያምኑም:: ወልድ ፍጡር ነው ሲሉ መንፈስ ቅዱስን ደግሞ ዝርው ኃይል /impersonal power/ ነው ብለው ያምናሉ::
- ሁሉን ቻይ አምላክ/ይሖዋ/ ብለው የሚያምኑት አብን ብቻ ነው::
- ክርስቶስ የተሰቀለው በተመሳቀለ እንጨት ላይ ማለትም በመ ስቀል ላይ ሳይሆን ቀጥ ባለ እንጨት በግንድ ላይ ነው ይላሉ::

---

1. Jehovah's Witnesses P. 13
2. The oxford Dictionary of the Christian Church P. 1189
3. The oxford dictionary of the Christian church



www.ethiopianorthodox.org

- በእነርሱ እምነት ክርስቶስ ማለት ሚካኤል፣ ሚካኤል ማለት ክርስቶስ ነው::
- ገነትና ሲኦል የሚባሉ አጸደ ነፍሳት የሉም:: ገነት ማለት የአትክልት ስፍራ ሲኦል ማለት መቃብር ነው ይላሉ::
- የመላእክትና የቅዱሳንን አማላጅነት አይቀበሉም::
- የነፍስን ሕያውነት አይቀበሉም:: ሞትም በእነርሱ አስተምህሮ የሥጋና የነፍስ መለያየት ሳይሆን የሰው ደም መፍሰስ ወይም የደም ዝውውር መቆም ነው:: በእነርሱ እምነት በሰውና በእንስሳ መካከል ልዩነት የለም::
- የሰማይና የምድርን ማለፍ አይቀበሉም ምድር ለዘላለም ናት ይላሉ:: ስለዚህ በምድር ላይ ለዘላለም እንደሚኖሩ ያምናሉ::
- የደም ማስተላለፍን /blood transfusion/ ይቃወማሉ::
- በዓላትን ማክበር፣ የልደት ቀንን ማሰብ የመሳሰሉትን አጥብቀው ይኮንናሉ:: ትንሣኤንና ገናን ሌሎችንም ሃይማኖታዊ በዓላትን ማክበር ከአሕዛብ የተወረሰ ልምድ እንደሆነ ይናገራሉ:: ለዚህም በጥንት ዘመን ለሳተርን ይደረግ የነበረውን ፌስቲቫል የምዕራቡ ዓለም ክርስቲያናዊ በዓል አድርጎ ማክበሩን በምሳሌነት ይጠቅሳሉ::[1]

1. በእርግጥ በምዕራባውያን ዘንድ ከጌታ ልደት ጋር ተያይዞ የሚደረገው የገና ዛፍ /Christmas Tree/ የት መጣውን ስንመረምር ጥንት ምዕራባውያን ሳተርን ለተባለው ጣኦት ያደርጉት የነበረ ነው:: በምዕራፍ አንድ ላይ ጠቆም አድርገን እንዳለፍነው የጥንት ምዕራባውያን በሆራስተርን የሁለት አማልክት እምነት ያምኑ ነበር:: በዓለም ላይ ያሉ ተቃራኒ ክንውኖች ሁሉ በደጉና በክፉው አምላክ ፉክክር የተፈጸሙና የሚፈጸሙ አድርገውም ያምኑ ነበር:: ሳተርንን ደጉ አምላክ እንደሆነ ያምኑ ነበር:: እንደሚታወቀው ሁሉ በምዕራቡ ዓለም ክረምቱ እጅግ አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሣ በታላቅ ችግር ላይ ሆነው ነበር የሚያሳልፉት:: ዛሬ በቴክኖሎጂ ችግሩን ቢቋቋሙትም ዛፎች ሁሉ ቅጠላቸው ረግፎ መለመላቸውን ሲቀሩ ጽድ የተባለው ዛፍ ግን ከሌሎቹ ሁሉ የክረምቱን በረዶና ቅዝቃዜ ሁሉ ተቋቁሞ በልምላሜው «መልካሙ ዘመን» ብለው እስከሚጠሩት ወቅት ድረስ ይዘልቅ ነበር:: ይህም የሆነው ጽድ ደጉ አምላክ ሳተርን ከክፉው አምላክ ራሱን ሸሽጎ የሚያቆይበት መደበቂያው በመሆኑ ነው ብለው ያምኑ ነበር:: በዚህ የተነሣ የደጉ አምላክ ዘመን ሲመጣ ደጉ አምላክ ክፉውን ጊዜ ተሸሽጎ ያሳለፈበትን ጽድ በማስጌጥ የሳተርን ቀንን በታላቅ ድምቀት ያከብሩ ነበር:: ክርስትና በመላው የሮም ግዛት ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆን በታላቁ ቆስጠንጢኖስ ከታወጀ ጊዜ ጀምሮ ግን ብዙ ጣኦታዊ በዓላት ክርስቲያናዊ ሆነው እንዲከበሩ ተደርገዋል::



www.ethiopianorthodox.org



ዳሩ ግን ትንሣኤ፣ የጌታ ልደት ቀንና ሌሎችም ክርስቲያናዊ በዓላት የት መጣቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንጂ ጣኦታዊ አምልኮት አለመሆናቸው ሊታወቅ ይገባል:: አይሁድ የሚያከብሩአቸው ሃይማኖታዊ በዓላት እንደነበሩ እዚህ ላይ ልብ ይሏል::

ሩስል የአምላክ መንግሥት በ1914 ዓ.ም. በምድር ላይ መግዛት ትጀምራለች ብሎ የተናገረው ትንቢት ሳይፈጸም ቢቀር ተከታዮቹ ካፈርኩ አይመልሰኝ ብለው ይመስላል የሩስል ትንቢት እርሱ ባለው ጊዜ እንደተፈጸመ ለማሳመን የአምላክ መንግሥት በሰማይ ላይ መግዛት የጀመረችበት ጊዜ በርግጥ 1914 ዓ.ም. ነው በማለት ግዛቱ በሰማይ እንደተቋቋመ ያለ ማፈር ይናገራሉ::

በዚሁ ዘመን የተፈጸመውን የአንደኛ ዓለም ጦርነትንም እንደ ዋቢ አድርገው ይጠቅሳሉ:: ጌታ የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክት ምንድር ነው? ብለው ደቀ መዛሙርቱ በጠየቁት ጊዜ ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ ግድ ነው ብሎ የተናገረውን ወስደው በዚያን ዘመን የነበረው የ1ኛ ዓለም ጦርነት ለትንቢቱ ተፈጻሚነት ዓይነተኛ ምስክር እንደሆነ ለማሳመን ይጣጣራሉ::

«ከክርስቶስ ጋር በሰማይ ላይ ሆነው ለወደፊት በምድር ላይ የምትመሠረተውን የአምላክ መንግሥት በገዥነት የሚመሩ 144 ሺ ከምድር ላይ እንደሚዋጁ ማለትም ከሙታን ተለይተው በመነሳት ወደ ሰማይ እንደሚነጠቁ» የይሖዋ ምስክሮች ያስተምራሉ:: «ታናሽ መንጋ» /anointed class/ በሚል ስያሜ የሚጠሩዋቸው እነዚህ ከክርስቶስ ጋር በገዥነት የሚሰየሙት እጅግ ብዙ ከሆኑት ምድራዊ ተገዥዎቻቸው ከሆኑት በእነርሱ አጠራር «ታላቁ መንጋ» /Great Crowd/ ከተባሉት ተለይተው የሚመረጡት በአገልግሎታቸው ብቃትና ጥራት መሆኑን ይገልጻሉ:: «ትንሹ» ና «ትልቁ» መንጋ የተባሉት ሁሉም የይሖዋ ምስክሮች ብቻ መሆናቸውን እዚህ ላይ ያጤኗል::[1]

የክርስቶስ ዳግም ወደዚህች ምድር መምጣት በይሖዋ ምስክሮች ዘንድ አይታመንም:: የክርስቶስ ዳግም ምጽአት እንደ ኦርቶዶክሳውያን እምነት በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው የተወጋ ጎኑን እያሳየ በገሃድ በአካል የሚመጣ ሳይሆን ንጉሣዊ ግዛቱን ወደ

ምድር የሚያዘነብልበትና «ታናሹን መንጋ» ከሞት የሚያስነሳበት እንደሆነ ነው የሚገልጹት::[2]

በይሖዋ ምስክሮች ዘንድ ሰው ማለት ሥጋዊ ፍጥረት ብቻ ነው:: የማትሞትና የማትፈርስ ዘላለማዊ ሕይወት ያላት ነፍስ የለችውም:: በዚህች ምድር በሕይወት የሚንቀሳቀሰውም በደም ሲሆን ደሙ ሲፈስ ወይም ዝውውሩን ሲያቆም ይሞታል:: በዚህ እምነታቸው «ሰው ከእንስሳት የተለየ አይደለም:: የሰውና የእንስሳት ሞት አንድ ነው ሁሉም ወደ አፈርነት ይመለሳሉ» ሲሉ ያስተምራሉ::

የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ግን ሰው በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረ ሲሆን ከአራቱ ባሕርያትና ከደማዊት ነፍስ በመፈጠሩ በማናቸውም ነገር ከእንስሳት ጋር ተመሳሳይነት ሲኖረው ነገር ግን ከእንስሳት የሚበልጥበት እግዚአብሔርን የሚመስልባት እንደ መላእክት ፍጹም የማትሞት የማትፈርስ የማትበሰብስ የምታስብና የምትናገር ዘወትር ሕያው ሆና የምትኖር ነባቢት ነፍስ ስላለችው ከእንስሳት ይለያል «ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ» እንደተባለ::[3] ሰው ሕያው የሆነች ነፍስ እንዳለችው መጽሐፍ ቅዱስ በሚከተሉት ቦታዎች ያስገነዝባል::[4]

1. ወደ ዘላለማዊ ሕይወት የሚመራ እውነት ገጽ 75-83
2. ወደ ዘላለማዊ ሕይወት ገጽ 81
3. ዘፍ. ፪÷፯
4. መዝ. ፴/፴፩/÷፭፣ መክ. ፲፪÷፯፣ ማቴ. ፲÷፳፰፣ የሐዋ. ፯÷፶፱፣ ራእይ ፮÷፱





## 4.8 «ኢየሱስ ብቻ» /Only Jesus/

በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው ሊቢያዊው ሰባልዮስ እንዱ እግዚአብሔር አንድ ገጽ ብቻ እንዳለው ያስተምር ነበር:: አንዱ ገጽ በተለያዩ ዘመናት ቅርጹን ለዋውጦ ታየ:: ብሉይ ኪዳንን ስለሠራ አብ ተባለ:: በዘመነ ሐዲስ ደግሞ ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ ስለታየና ሐዲስ ኪዳንን ስለሠራ ወልድ ተባለ:: ኋላም በበዐለ ጰራቅሊጦስ በእሳት አምሳል ወርዶ ለሐዋርያት ምሥጢር በመግለጡ መንፈስ ቅዱስ ተባለ በማለት የእግዚአብሔርን ልዩ ሦስትነት ክዶ አንዱ ገጽ ወይም አንዱ አካል በተለያዩ ዘመናት ቅርጹን ለዋውጦ እንደመጣ በአጽንኦት ያስተምር ነበር:: ይህ የሰባልዮስ ትምህርት «ሞዶሊስቲክ ሞናርኪያኒዝም» ይባላል:: የዘመናችን ሰባልዮሳውያን «ክርስቲያን ሞኖተይዝም» በማለት «ኢየሱስ ብቻ» ባዮች ደግሞ የሰባልዮስን ክህደት አዲስ ሰሌዳ ለጥፈውለት እያንቀሳቀሱት ይገኛሉ::

ድርጅታቸውን «የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» በማለት የሚጠሩት የዘመናችን ሰባልዮሳውያን በካሪዝማቲካዊ እንቅስቃሴያቸው ፔንቴኮሳታል ከሚባሉት ሌሎች የኘሮቴስታንት ቡድኖች ጋር አንድ ሲሆኑ የጥንታዊቱን ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮም አይቀበሉም:: ባለአንድ አምላክ /Monotheistic/ ነን የሚሉት እነዚህ ክፍሎች ሌሎች የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት የሚያምኑት አብያተ ክርስቲያናትን ባለ ብዙ አማልክት /Polytheistic/ አድርገው ይፈርጃሉ:: በብዙ አስተምህሮዋቸው ከሌሎች የኘሮቴስታንት ቡድኖች ጋር የሚመሳሰሉት እነዚህ ቡድኖች በሚከተለው አስተምህሯቸው ከብዙዎቹ ይለያሉ:: መጠሪያ ስማቸው እንደሚያስገነዝበው አብ፣ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የሚባለው አንዱ ኢየሱስ ነው ባዮች ናቸው:: «መለኮት ከዘላለም በአካል በባሕርይ በስም በግብር አንድ እንጂ ሁለት ወይም ሦስት አልነበረም:: በሦስት መንገድ ግን ራሱን ለሕዝቡ ገልጾአል:: በሦስት መንገድ የተገለጸበትም ምሥጢር በአብነት በሥጋ ዓይን ሳይታይ በወልድነት በሥጋ እየታየ በመንፈስ ቅዱስነት እስትንፋሱን በሕዝቡ ልብ ውስጥ በማሳደር ተገልጦአል»[1]

1. ኢየሱስን ማን ይሉታል ገጽ 12



www.ethiopianorthodox.org

ይህ የ«ኢየሱስ ብቻ» አማኞች ትምህርት ከሰባልዮስ ትምህርት ጋር ፍጹም ተመሳሳይ መሆኑን ያጤኗል:: መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስ ገነዝበን ግን አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በአካል፣ በስም በግብር ፍጹም ሦስት መሆናቸውን ነው::[1]

አብ በሥጋ ተገለጠ ብለው የሚያምኑት እነዚህ ክፍሎች ቃል ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነ ፍስዋ ነፍስ ነስቶ ሰው መሆኑን ፍጹም ይክዳሉ:: ከዚህ ይልቅ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ሥጋነት ተለወጠ ሲሉ ያምናሉ:: «የአብ ርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም»[2] ለሚለው የሐዋርያው ትምህርት ጆሮዋቸውን የደፈኑ ናቸው:: ጌታም ስለራሱ ሲናገር «የሰው ልጅ» እያለ መናገሩ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ ሰው በመሆኑ እንደሆነ ልባቸው አያስተውልም:: መሠረታዊውን የድኅነት ትምህ ርት የማይቀበሉት እነዚህ ክፍሎች በፍጹም ከህደታቸው አላዋቂዎ ችን እያታለሉ ወደ ጥፋት ገደል እየወረወሩ ይገኛሉ::

## 4.9 ኘሮቴስታንት በታላቅ ቀውስ

የኘሮቴስታንቱ ኅራ ማርቲን ሉተር በይፋ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተገንጥሎ መወጣቱን ካወጀበት ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ባላቋረጠ መከፋፈል ላይ መሆኑ የአደባባይ ምሥጢር ነው:: ከክፍፍሉ መብዛት የተነሣም ይህን ያህል ደርሷል ብሎ ለመናገር የማይቻልበት ደረጃ ላይ እንዳለ እናስተውላለን:: ከክፍፍሉ ይልቅ ከፍቶ የሚታየው ደግሞ ከፋፋዮቹ ይዘውት የሚነሱት «ኑፋቄ» ጆሮን ጭው የሚያደርግ መሆኑ ነው::

«ቁሳዊው የኢየሱስ ደም በተረገመው እንጨት ላይ በፈሰሰበት ወቅት በደም ሥሮቹ ውስጥ ይፈስ ከነበረበት ጊዜ የላቀ ዋጋ አልነበረውም» የክርስቲያን ሳይንስ ዶክትሪን

«ኢየሱስ በሲኦል ዳግም ተወልዶ ተነሣ» ኬኔት ኮኘላንድ ባሳተሙት መጽሐፍ ላይ የተገለጸ::

1. ማቴ. ፫፥፲፮-፲፯፣ ማቴ. ፳፰፥፲፱፣ ዮሐ. ፲፬፥፲፮-፲፯፣ ዮሐ. ፲፭፥፳፮
2. ዕብ. ፪፥፲፮





«ክርስቶስ ኃጢአት ወይም ሰይጣን ሆኖ ነበር»

«ኢየሱስ በሥጋም በመንፈስም ሞቷል» የእምነት እንቅስቃሴ

«ክርስቶስ መከራውን ሁሉ ስለተቀበለልን የእኛ ድርሻ መዘነጥ ነው» ዘንጥ ለኢየሱስ

«ክርስቶስ ራስ ነው እኛ አካል ነን የክርስቶስ አካል ክርስቶስ ነው እኛ ክርስቶስ ነን» ሬማ

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ የኑፋቄ ትምህርቶች የኘሮቴስ ታንቱን ዓለም ከድጡ ወደ ማጡ እየከተቱ መሆኑን እንገነዘባለን::

## ብልጽግናን ማዕከል ያደረገው የእምነት እንቅስቃሴ

«ሃሌ ሉያ» በማለት ለምስክርነት መቆሙን አበሰረ:: የጉባ ኤው ታዳሚዎችም «ሃሌ ሉያ» በሚለው ጩኸት ለመስማት ፈቃ ደኝነታቸውን ገለጹለት:: መስካሪው የሀገር ቤቱ አርቲስት በጀር መን በስደት ለሚኖሩት የእምነቱ አጋሮች ገለጻውን ቀጠለ:-

«ይገርማችኋል ጌታን ሳልቀበል በፊት /በኦርቶዶክስ እምነት በነበረበት ጊዜ ማለቱ ነው/ የረባ የቤት ቁሳቁስ አልነበረኝም በቤት ኪራይም እንከራተት ነበር:: ዛሬ ግን ጌታን በመቀበሌ የሁለት ፎቅ ቤቶች ባለቤት ሆኛለሁ:: ሃሌ ሉያ» ሰሚዎቹም የእርሱን ቃል ተቀብለው አስተጋቡ::[1]

ይህ አርቲስትና የማስታወቂያ ድርጅት ባለቤት የሆነው ሰው የየትኛው ዲኖምኔሽን አባል እንደሆነ ባላውቅም የሰጠው ምስክርነት ግን ብልጽግናን ማዕከል አድርጎ የሚንቀሳቀሰው ክፍል የሚያስተጋባው ትምህርት ለመሆኑ የሚከተለውን መረጃ መጥቀስ ይቻላል::

«በፊት በእግሬ እሔድ ነበር:: አሁን ግን ኮንትራት ታክሲ እጠቀማለሁ» ፓስተር ግርማ አሰፋ የዊነርስ ቻኘል ፓስተር የሰጠ ው ምስክርነት[2]

1. ከቪዲዮ ካሴት የወሰድኩት ነው
2. ብልጽግና ገጽ 10

www.ethiopianorthodox.org

ይህ የፓስተሩ ምስክርነት ደግሞ «ኢየሱስን ወደ ሕይወትህ ባስገባህ ቅጽበት ከድህነት ከበሽታና ከመንፈሳዊ ሞት ትድናለህ» የሚለው የእምነት እንቅስቃሴ አስተምህሮ ነው[1] የእምነቱም መሥራች ኬነት ሀገን የተባሉ ሰው እንደሆነ ይነገራል::

ኬነት ሀገን በኦክላሆማ ቱልሳ ያቋቋሙት ሬማ የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከል ከ1974 - 1988 ዓ.ም. ብዙ የዓላማው አራማጅ የሆኑ ተማሪዎችን አስመርቆ በዓለም ላይ ያሠራጨ ሲሆን በመዲናችን በአዲስ አበባም «ሬማ የእምነት አገልግሎት» የሚል ስያሜ ያነገተ ተቋም ከሙሉ ወንጌል ተገንጥሎ በመውጣት ውክቢያ በመፍጠር ላይ ነው::[2]

«ለ45 ዓመታት ሙሉ በኢየሱስ ስም ጠይቄ ያላገኘሁት ነገር የለም:: ለጥያቄውም የሚሰጠው ምላሽ ሁልጊዜም አዎን የሚል ነው::» በማለት ኬነት ሀገን የተናገሩትን በመያዝ የእምነቱ ተከታዮች የፈለጉትን ሁሉ በኢየሱስ ስም ጠይቀው እንደሚያገኙ ያምናሉ:: እዚህ እኛው ሀገር በአንድ የብልጽግና ወንጌል ሰባኪ የተደረገውን አንድ የኘሮቴስታንት መጽሔት ሲገልጽ «የተቆጣጠረውን ምስባክ የሚነጥቅበት ያለ ይመስል በጥርጣሬ በር በሩን አጮልቆ የሚያየው የብልጽግና ሰባኪ አዎንታዊ ቃል በመናገርና በኢየሱስ ስም በማዘዝ አድማጮቹ የሚፈልጉትን ሁሉ ሊያገኙ እንደሚችሉ ይናገራል:: በኃይል ስለሚጮህ ምን እንደሚል መስማቱ ራሱ አስቸጋሪ ነበር:: ባለፈው ሳምንት ሁሉም የሚፈልጉትን ነገር በኢየሱስ ስም ጠይቀው እንዳገኙና አንዳንድ የብልጽግና ሰባኪዎችም ባጭር ጊዜ ውስጥ የመርሴዲስ ባለቤቶች ለመሆን እንደበቁ በመግለጽ የአድማጮቹን ሞራል ቀሰቀሰ:: ወዲያውም የተመኙትን መርሴዲስ ከእጃቸው የሚያስገቡ የመሰላቸው ተሰብሳቢዎች የኢየሱስን ስም እየጠሩ በኢየሱስ ስም መርሴዲስ ለእኔ/ በኢየሱስ ስም ይሉ ገባ:: ከብዙ ሥርዓት የለሽ ጫጫታ በኋላ ሰባኪው እንደገና መናገሩን ቀጠለ:: መርሴዲሱን በእምነት ስለተቀበላችሁ በሉ አሁን እንንዳ:: ፒ... ፒ... ሬጽ... ሬጽ... ስፍራው በአንዴ ባቡር መንገድ ሆኖ አረፈ»[3]

1. ብልጽግና ገጽ 10
2. ብልጽግና ገጽ 16
3. ብልጽግና ገጽ 77





የእምነት እንቅስቃሴ ሌላው መርሆ ኢየሱስን በተቀበሉ ቅጽበት ከበሽታ ፈጥኖ መፈወስ እንዳለና በሽታም በዚያ አማኝ ላይ እንደማይሰለጥንበት የሚገልጸው ነው:: በመሠረቱ በሽታ ወይም ሕመም ሁሉ የኃጢአት ውጤት አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስም በሽታ የኃጢአት ውጤት ብቻ መሆኑን አያስተምርም:: እንደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ዋጋ የሚያስጥ ደዌ አለ የኢዮብና የቅዱስ ጳውሎስ ዓይነት:: የመቅሰፍት ደዌም አለ እንደሄሮድስ ያለ:: የእምነት እንቅስቃሴ አራማጆች ግን «በሽታ በሥጋዊ አካል ላይ የሚታይ መንፈሳዊ ሁኔታ ነው የሚመጣው ከሰይጣን መንፈሳዊ ዓለም ነው::» ብለው ያስተምራሉ:: ስለዚህ በእምነት የመገለጥ እውቀት እንደሚፈወሱ ያምናሉ:: የሕመም ሥቃይም ሆነ የበሽታ ምልክት አለመፈወሳቸውን በመግለጽ ሊያሳምናቸው አይችልም:: ይህ እንቅስቃሴ ያስከተለውን ጦስ «ልጃችን ሲሞት ዝም ብለን አየን» በሚል ርዕስ አንድ አባት የልጃቸውን አሟሟት የተረኩበት መጽሐፍ እንዲህ ገልጾታል::

የዚህ እምነት ወንጌላዊ የሆኑት ዌስሊ ፓከር ለተባለው ልጃቸው የፈውስ ጸሎት ካደረጉለት በኋላ ወላጆቹ በስኳር በሽታ ለሚሠቃየው ልጃቸው መድኃኒት ላለመስጠት ወሰኑ:: በልጁ ላይ በሽታው እየጸና መጥቶ በጣዕረ ሞት ሲያጣጥር ወላጆቹ በተማሩት መሠረት ሰይጣን ውሸተኛ የሞት ምልክት በማሳየት የሚፈትናቸው መሰላቸው:: በመሆኑም በአገስት 23፣ 1973 ዓ.ም. ልጃቸውን በሞት እስኪነጠቁ ድረስ አዎንታዊ የፈውስ ቃል መናገራቸውን ቀጠሉ::

ልጃቸው ከሞተም በኋላ የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ሊካሔድ አልቻለም:: ዌስሊ ከሞት ይነሣል በሚል እምነት አባቱ «የትንሣኤ ኘሮግራም» አዘጋጁ:: ልጃቸው ከሞት አልነሣ ሲል የልጅ አባት እምነት የሌላቸውን ሰዎች ሁሉ ከኘሮግራሙ ስፍራ አባረሩ:: ከዚያም የልጃቸውን ትንሣኤ ለአንድ ዓመት ያህል በእምነት ሲጠባበቁ ቆዩ:: በዚህ መሐል ለልጃቸው ሞት ምክንያት በመሆናቸው ፍርድ ቤት ተከሰሱ::[1]

1. ብልጽግና ገጽ 17



www.ethiopianorthodox.org

እዚህ አዲስ አበባም አንዲት አንድ እግሯ አጭር የሆነ
ሴት አንድ ቀን መድረክ ላይ ወጥታ በአንድ እግሯ ፈንጠር ፈንጠ
ሴት አንድ ቀን መድረክ ላይ ወጥታ በአንድ እግሯ ፈንጠር ፈንጠ
ር እያለች ተፈውሻለሁ ማለቷና ግራ የተጋቡ ሰዎችም ከመድረኩ
ስትወርድ ለመሆኑ ምኑ ላይ ነው የተፈወስሽው ቢሏት «ድሮ
እንደዚህ አልነበረም ስትል እንደሞገተቻቸው ተናግረዋል»[1]

## የካሪዝማቲክ እንቅስቃሴ

የኘሮቴስታንትን ጎራ እየናጠው ያለው ሌላው ማዕበል
የካሪዝማቲኮች እንቅስቃሴ ነው:: በመንፈስ ተሞላን በማለት እንደ
ባለዛሮች የሚያጓሩና ሰውነታቸው እስክስታ የሚመታ፣ የሚርገፈ
ገፉ፣ እንደ እንስሳት የሚጮሁ፣ በሳቅ የሚንከተከቱ፣ በዚህም
ድርጊታቸው የብዙ ሰዎችን ስሜት የሳቡ የፔንቴኮስታል አራማጆች
በሀገራችን መብዛታቸው የማይካድ ነው::

እንዲህ ዓይነቱ የፔንቴኮስታል እንቅስቃሴ ወደ ሀገራችን
ከገባ ረዥም ጊዜ ባያስቆጥርም በዓለም ደረጃ ግን በ1901 ዓ.ም.
በቶፕካም ካንሳስ እንደተጀመረ ይነገራል:: የእንቅስቃሴው መሪ
ሲኤፍ ፔርሃም የተባለ የሜቶዲስት አገልጋይ የሆነ ሰው በመንፈስ
ቅዱስ ተጠምቆ በልሳን መናገር መጀመሩን ገለጸ:: ይህ ዓይነቱ
እንቅስቃሴ ወደ ሌሎቹ የኘሮቴስታንት ክፍሎችም ተዛመተ:: እየ
ዋለ ሲያድር እንቅስቃሴው ሌሎች ልምምዶችን አካተተ በመንፈስ
መታረድ፣ ከመሬት ጋር መጣበቅ፣ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ሳቅ
መሳቅ፣ መንቀጥቀጥና አሁን አሁን ደግሞ ዳንስ::

አንዲት በጀርመን አገር በስደት የምትኖር እህት «ይህን
ጉድ እስቲ እየው» ብላ አንድ የኘሮቴስታንቶች የስብከት ካሴት
ሰጠችኝ:: የምዕራባውያኑ የካሪዝማቲክ እንቅስቃሴ ሰው ካወቀው
ፀሐይ ከሞቀው ዘለግ ያለ ጊዜ ቢሆንም የእኛዎቹ ኘሮቴስታንቶች
ግን በዚህ ያህል ፍጥነት ወደዚህ እንቅስቃሴ ይገባሉ ብዬ
አልገመትኩም ነበር:: ምክንያቱም ያሉበትና ያደጉበት ኅብረተሰብ
ባሕልና የአኗኗር ሁኔታ ያዝ ያደርጋቸዋል በሚል ግምት:: ይህ
ካሴት ግን ግምቴን ፉርሽ አደረገው::

1. ብልጽግና ገጽ 55





ከሰሜን አሜሪካ ጀርመን የሚገኙ የእምነት አጋሮቹ ጋብዘ
ውት የመጣ ይመስለኛል - ሰባኪው:: «መጋቢ» የሚል የማዕረግ
ስም ከሰሙ በፊት ተጽፎ አንብቤያለሁ:: አንዲት እውቅ የኘሮቴስ
ታንት ዘማሪ እንደሆነች የተነገረኝ ሴት አብራው አለች:: መነሻ
አድርጎት የተነሳበትን የትምህርት ርዕስ እንደ አዝማች ከመደጋገም
ውጪ አብዛኛውን ሰዓት ያሳለፈው የካሪዝማቲክ እንቅስቃሴን
በማሳየት ነው:: ስብከት ከጀመረ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ትምህር
ቱን ገታ አድርጎ ተሰባኪያኑን እንዲነሱ አዘዘ:: ከዚያም ሞቅ
ደመቅ ያለውን ዘፈን መሰል መዝሙር ዘማሪዋ እንድታቀርብ አድ
ርጎ እርሱ ዳንሱን ያስነካው ጀመር:: ተሳታፊዎቹም ዳንስ የሚች
ለው ዳንሱን እስክስታ የሚቀናውም ነጠላ ማገልደም ቀርቶበት
ይሆን እንጂ ሰውነቱ ውልቅልቅ ሲል አስነኩት:: ዘፈን ቀመስ
የሆነው መዝሙር ከተጠናቀቀ በኋላ ሁሉም በየቦታው ተቀመጠ::
እንደአዝማች የሚጠቀምበትን የትምህርት ርዕስ አነበበና ትንሽ
ዲስኩር አድርጎ ቆም ብሎ መንፈሳቸውን ዘና እንዲያደርጉ መንፈስ
ቅዱስ እየዳሰሳቸው መሆኑን አውጆ ሁሉም እንዲስቁ ጋበዘ:: የሳቅ
መንፈስ የኮረኮረው ከጣሪያ በላይ ሳቀ:: ሌላውም በግዱ አገጠጠ::
ብቻ አዳራሹ የእብዶች አንባ መሰለ:: ሰባኪው አስቀድሞ እፍረትና
ፍርሀትን እንዲያስወግዱ ይሉኝታን እንዲሰባብሩ «ይሉኝታ እንክት»
እያሉ በይሉኝታ ገመድ እንዳይታሰሩ በመፈክር ይሉኝታን ስብር
ብሩን እንዲያወጡት አድርጓቸዋል:: ዘማሪዋን አስነስቶ እጁን
ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጎ ለስለስ ያለ ትዝታ የሚሉት ዓይነት
ዘፈን መሰሉ መዝሙረ ሲዘመር ደግሞ ለቅሰው፣ ማጓራቱ፣ መንዘ
ፍዘፉ በተሳታፊዎቹ መታየት ጀመረ:: ይሄ እንዳበቃ ደግሞ «ምን
አለ-ወ'ቴ ምን አለ ሀገሬን ለሰው አልሰጥም አለ» የሚለውን ዜማ
ተከትሎ የራሱን ስም ከቶ ያስጨፍራቸው ጀመር:: አቤት! ክቡር
ሆኖ የተፈጠረው የሰው ልጅ አእምሮ ያለው የሰው ልጅ! ምንም
እንደማያውቁ ሕፃናት ውደቁ፣ ተነሡ፣ ሳቁ፣ አልቅሱ ሲባሉ «ኧረ
ለምን?» የሚል ጠያቂ እንኳን የሌለበት::

በዚህ ካሴት ላይ ያየሁት የኛው ሀገር ካሪዝማቲኮች የሚያ
ደርጉት ድርጊት በውጭዎቹ ዘንድ እጅግ የተለመደ መሆኑን
ከአንዳንድ ጽሑፎች ለማንበብ ችያለሁ:: ዎርድ ኦፍ ፌዝ የተባለ



www.ethiopianorthodox.org

ከፍተኛ ሥራ ለማገኘት አይችሉም:: «ከዝቅተኛ ዘር የሆነ ሰው በጣም ደግና ብልኅ እንዲሁም ጀግና የሆነ እንደሆነ በሚመጣው ሕይወት የተሻለ ዘር ሆኖ ይወለዳል» ሲሉ ያምናሉ:: የዚህንም ሁኔታ ሲገልጹ «ሕይወት ያለው ፍጥረት ሁሉ ነፍስ ያለበት ነው:: የነፍስ መገኛውም የዓለም ነፍስ ከሆነው ከብርሃማን ነው:: ብርሃማን ከቶ የማይሞት ዘላለማዊ በመሆኑ ሕይወት ያለው ፍጥረት ሁሉ የማይሞት ነው:: ስለዚህ ሰው በሞተ ጊዜ ነፍሱ ከሥጋው ተለይታ ወዲያው አዲስ በሚወለደው ሕፃን ሰውነት ውስጥ ትገባለች»

ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ በሂንዱ እምነት አንድ ሰው እየ ተደጋገመ እንደሚወለድ ይታመናል:: ይህንንም የውልደት ሂደት ሂንዱዎች ሲያብራሩ «ከከፍተኛ ዘር የተወለዱት ክፉ በመሥራት ቢኖሩ እንደገና የሚወለዱት ዝቅተኛ ዘር ሆነው ነው:: በሚቀጥለው ሕይወቱ ሁሉ ክፉ ሰው የሚሆን ከሆነ በየጊዜው ዝቅተኛ ዘር እየሆነ ይወለዳል:: ፍጹም በሽተኛ በመሆንም በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ስለሚሰቃይ ላደረገው የክፋት ሥራ ቅጣት ይሆንበታል:: የመጨ ረሻ ደረጃ ላይ ሆኖ ተወልዶ ክፉ ሥራ የሚሠራም ከሆነ ዝሆን ሆኖ ይወለዳል:: ክፉ ዝሆን የሆነ እንደሆነ ደግሞ ከሞተ በኋላ ውሻ ሆኖ ይወለዳል:: ክፉ ውሻ ቢሆን ዝቅተኛ ፍጥረት በመሆን ቁንጫ ወይም ተንኝ ሆኖ ይወለዳል::»

ይህ የደጋግ ሰዎች ነፍስ ወደ ከፍተኛ ዘር የምታድግበት የክፉዎች ነፍስ ደግሞ ወደ ዝቅተኛ ዘር ወይም ወደ እንስሳ የምት ገባበትን ምክንያት የእምነቱ ተከታዮች ሲገልጡ «ደግ መልካም ዋጋ ክፉ ደግሞ የክፋቱ ውጤት የሆነውን ቅጣት ማግኘት እንደ ሚገባ የሚያዝ የሕይወት ሕግ «ካርማ» ስላለ ነው» ይላሉ:: ካርማ ማለት የምግባር ሕግ ማለት ሲሆን ደግ የሠራ ለመልካም ሥራው የሚሆን ዋጋ በሚቀጥለው ሕይወቱ ያገኛል:: ክፉ የሠራም ቀጥሎ በሚገጥመው ሕይወቱ ቅጣቱን ይቀበላል ማለት ነው::

አንድ ሰው እስከመጨረሻው በደግነቱ ከዘለቀ መጨረሻ ላይ ምን ይሆናል? ለሚለው ጥያቄም ሂንዱዎች መልስ አላቸው «ቄስ ከሆነ በኋላ በደግ ሥራው ከገፋ የመጨረሻው ሕይወት ይሆናል እንጂ ተመልሶ መወለድ የለም:: ሆኖም ያቺ ነፍስ እስከመጨረሻው ደግ ሥራ ከመሥራት ያላቋረጠች እንደሆነ የዚህን ዓለም ኑሮ በጨረሰች ጊዜ የዓለም ነፍስ ወደ ሆነው ከብርሃማን ጋር አንድ



ትሆናለች ይህም ኒርቫና ይባላል» ስለዚህ የማንኛውም ሂንዱ ትልቁ ተስፋ ከዓለም ነፍስ ጋር አንድ በመሆን ኒርቫና ውስጥ ለመግባት ነው::

የአዲሱ ዘመን የዳግም ልደት አስተምህሮ ከላይ የተገለጸው የሂንዱ እምነት ግልባጭ ነው:: ከአንዳንድ የቃላት ለውጥና ከፓንቴይስት አመለካከቱ ውጪ በብዙው ተመሳሳይነት አለው:: ሰዎች ሲሞቱ ሌላ ሰው ሆነው ወይም እንስሳ ሆነው እንደሚወለዱ እንዲያምኑ የአዲሱ ዘመን አማኞች ግፊት ያደርጋሉ:: በሕይወት ሕግ ካርማ አማካይነት ኒርቫና ውስጥ መግባት እንዳለ ተስፋ ይሰጣሉ:: በዓለም ያለው ነገር ሁሉ ዑደታዊና በድግግሞሽ ያለ የሚኖር መሆኑን ያትታሉ::

## ሞኒዝም

የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ተለይተው ከሚታወቁባቸው አመለካከቶች ውስጥ አንዱ «ሁሉም ነገር አንድ ነው» የሚለውና በልሳነ ግሪክ «ሞኒዝም» የተሰኘው አስተምህሮ ነው:: «ሞኖ» ማለት በግሪክ ቋንቋ አንድ ማለት ሲሆን «ሞኒዝም» ሁሉም አንድ እንደ ሆነ የሚያስተጋባ ቃል ነው:: በዚህ አስተምህሮ መሠረት በዓለም ያሉት ነገሮች ሁሉ እርስ በእርሳቸው የተንሰላሰሉ የማይለያዩና የሚደጋገፉ እንዲሁም በምንም የማይለያዩ አንድ ናቸው:: ይህም ማለት ጠፈረ ሰማዩ፣ ፀሐይና ጨረቃ፣ ሰው አራዊት፣ እጽዋት፣ ድንጋዩ፣ ተራራው በአጠቃላይ ግዑዙም ሕያውም ሁሉም አንድ ነው:: በፍጥረታት መካከል ምንም ልዩነት የለም የሚል እምነት ነው:: በዚህ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አስተምህሮ መሠረት በእግ ዚአብሔርና በፍጥረት መካከል ልዩነት የለም:: እንዲሁም በሰውና በሌሎች ፍጥረታት መካከል ልዩነት የለም:: ሁሉም ነገር አምላክ ነው የሚለው አስተምህሮዋቸው የመጣው ከዚህ እምነታቸው የተነሣ ነው::

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ የፍጥረታት ፈጣሪ ከፍጡ ራኑ ፍጹም የተለየ ነው:: በፍጥረታት መካከልም ከፍተኛ ልዩነት አለ:: በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረው የሰው ልጅ ከሌሎች [illegible] የከበረ ፍጥረት ነው:: ሌሎች ሁሉ የተፈጠ



www.ethiopianorthodox.org

ሩት ለእርሱ ነው:: እርሱ በሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ላይ የበላይ ነው:: እንስሳት፣ እፅዋት ሌሎች ግዑዛን ፍጥረታት ለእርሱ ተፈጥ ረዋል:: ሰውና መላእክት ግዕዛን /አእምሮ/ ያላቸው ፍጥረታት ሲሆኑ እንስሳት ግን ግዕዛን የላቸውም:: ስለዚህ በሰውና በእንስሳት መካከል የሰማይና የምድር ያህል ልዩነት እያለ ሰውን ከእንስሳ ጋር ፈርጆ አንድ ዓይነት ነው ማለት ኅሊና ያለውና የሚያገናዝብ ሰው የማይቀበለው ተረት ተረት ነው::

በአንዳንድ የምሥራቅ ሀገሮች ዘንድ ለምሳሌ በሕንድ እንደ ሚታመነው የሰው ልጅ ሕይወት ከእንስሳት ሕይወት ከላምና ከአይጥ ተለይቶ አይታይም:: ሰዎች በረሀብና በበሽታ መሬት ወድቀው ሳለ ለላምና አይጥ ልዩ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል:: ይህም ሰውና እንስሳትን አንድ አድርጎ የማመን በመካከላቸው ልዩነት እንደሌለ አድርጎ የማየት ጉዳይ ነው:: የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አራማጆችም ከዚህ ከምሥራቃውያን እምነት የተለየ አመለካከት የላቸውም::

## ግላዊነት

እግዚአብሔርን ያገለለ አመለካከት ሁሉ ወደ ግላዊነት ወይም ራስ ወዳድነት የሚያመራ መሆኑ ግልጽ ነው:: እግዚአብሔር ፍቅር ነውና:: ኃልወተ እግዚአብሔርን ክደው የሚያስክዱ ሁሉ የራሳቸውን ፍላጐት ለመፈጸም የኅሊና አጥር እንዳይኖርባቸውና እንደ ስሜታቸው ለመጓዝ መሆኑ አይካድም:: የአዲሱ ዘመን እን ቅስቃሴ አቀንቃኞችም ሁሉን ቻይ አምላክ መኖሩን ክደው ራሳቸ ውን በአምላክነት ያስቀመጡት ራስን ማዕከል ወደሚያደርገው የግላዊነት አመለካከት ለመራመድ ነው:: ይህ የኒው ኤጆች አፍ ራሽ ተልእኮ ሰዎች ሁሉ እኔ ወደሚለው ጥግ እንዲደርሱና ሌላውን እንዲያገሉ በተለይ ከራሳቸው ውጪ በሌላ መለኮታዊ ኃይል እንዳይመኩና እንዳይታመኑ ለማድረግ ነው:: «ሁሉም ሃይማኖቶች በውስጣችን ያለውን አምላክነት የምንገነዘብበት ምንም ዓይነት መንገድ የላቸውም» በማለት ሁሉንም እምነቶች በመኮነን የሚናገ ሩት:: እያንዳንዱ ሰው አምላክ እንደሆነ እንዲያምን የማነቃቃትና የማደፋፈር ተልእኮ ያለው ይህ እንቅስቃሴ ማንኛውም ሰው ከተ



www.ethiopianorthodox.org



ራው ንቃተ ኅሊና ወደ አምላክነት /መንፈስ/ ይሸጋገር ዘንድ የሚያስችሉ ቴክኒኮች እንዳሉ ይገልጻል:: ሰውነትን በአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማዳበር፣ ልዩ ዓይነት የአመጋገብ ስልትን መከተል በተለይ ቬጅተርያን /ሥጋን የማይመገቡ/ መሆን፣ ሰውነትን አዘው ትሮ መታጠብና ራስን በጽሞና ውስጥ መከተት... የኒው ኤጅ እንቅስቃሴ ቀደምት መሪ እንደሆነች የሚነገርላት ማርሊን ፈርጉሰን «መመሰጥ፣ ዮጋ፣ ሜዲቴሽን፣ ካራቴ፣ ዳንስ፣ ሩጫ የተለያዩ አስማታዊ ተግባራት...» ወደ ከፍተኛው ደረጃ ማለትም ወደ መንፈስነት የሚያሸጋግሩ ድልድዮች እንደሆኑ ገልጻለች::[1]

ራስን አምላክ ለማድረግ በሚደረገው ሩጫ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ኒው ኤጆች የመጀመሪያዎቹ እንዳልሆኑ የታወቀ ነው:: የመጀመሪያው ሰው አዳም ከነበረበት ክብር የተሻረው አም ላክነትን ሽቶ እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰ ነው:: ዛሬም በፍጻሜ ዘመን የተነሱት ዘመንኞቹ ራሳቸውን አምላክ ለማድረግ ቢንጠራሩም አምላክነትን ገንዘብ ማድረግ ፈፅሞ የማይቻላቸው ቢሆንም ዳሩ ግን በክህደት ትምህርታቸው የምዕራቡን ዓለም ማኅ በረሰብ ወደ ጥፋት አዘቅት እያወረዱት ነው:: ግላዊነትን ማዕከል ያደረገው የኒው ኤጆች አስተምህሮ በትምህርት ተቋማት በድርጅ ቶች ውስጥ ሠርጎ እየገባ መሆኑንና የብዙዎችንም ስሜት ገዝቶ መያዙን አንዳንዶች በቁጭት እየተናገሩ ነው:: የኒው ኤጆች የአነ ጋገር ዘይቤዎች ከላይ በተጠቀሱት ተቋማትና በሌሎችም ዘንድ ሠርገው መግባታቸውን ለማመልከት የሞከሩ ሰዎች የሚከተሉትን የአዲሱን ዘመን እንቅስቃሴ አነጋገሮችን በምሳሌነት ይጠቅሳሉ «Self image» «Self esteem» «Self actualization» «Self love» «Self fulfillment» እነዚህ በብዙ ቦታዎች ላይ ጥቅም ላይ የዋሉ የአነጋገር ዘይቤዎች የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አራማጆች ግላዊነት በሰው አእምሮ ሠርጸ እንዲገባ ሆን ተብለው የተደረጉ መሆናቸውን በተቆርቋሪነት የተነሱት ወገኖች ይገልጻሉ::[2]

1. The Aquarian Conspiracy [j.p. Tarcher inc. Los Angeles CA 1980] pp. 86-87
2. Biblical Creation and Society P. 22

በድህነት አረንቋ የተዘፈቀውን ቤተሰቤን መታደግ እንዳለብኝ
ይገባኛል:: ይህን የማደርገው ደግሞ የቀረበልኝን ይህን ሥራ ስሠራ
ነው:: ከራማ ጋር በአውሮፕላን ጉዞአችንን ጀምረናል:: አእምሮዬ
ሰላም አጥቷል:: የመንፈስ እፎይታን አገኝ ዘንድ ጥቂት ውስኪ
ተጎነጨሁ:: ሸለብ አድርጎኝ ሳለ አስፈሪ ህልም አይቼ ባነንኩ::
ያየሁትን ህልም ለራማ ስነግረው ፈገግ ብሎ በአውሮፕላን ስትሔድ
የመጀመሪያህ በመሆኑ ነው ብሎ አጽናናኝ::

ከአውሮፕላኑ እንደ ወረድን ታክሲ ይዘን ራታችንን ወደ
ምንበላበትና ምሽቱን ወደምናሳልፍበት ሆቴል አመራን:: በነጋታው
ራቅ ወዳለ ሌላ ስፍራ እንደምንሔድ ተነግሮኛል:: የት ነው የምን
ሔደው? ምንድር ነው የምሠራው? የነዚህን ጥያቄዎች መልስ
ለማወቅ ያደረግሁት ጥረት ድካም ብቻ ሆኖ ሳይሳካ ቀርቷል::
ስለዚህ የሚሆነውን በዝምታ እስኪሆን ድረስ መጠበቁን መርጫ
ለሁ:: አዲሱን ሥራ ለማከናወን የሚያስችለኝን ትምህርት ወደ
ምማርበት ቦታ በማግስቱ ተጓዝን:: ደበቅ ያለ ትልቅ ቪላ ቤት
ነው:: ከብዙ ሰዎች ጋር ተዋወቅሁ:: ሁሉም የተዋወቁኝ በቅጽል
ስማቸው ነው:: ለእኔ የተመደበው ሰው «ቲ» ይባላል:: ከዚህ
በፊት በዓሊ የተደረገልኝ መልካም ነገር ሁሉ በነጻ የተደረገልኝ
እንዳልሆነ ከእኔ የሚፈለግ ነገር መኖሩን ጠቆመኝ:: አንድ ነገር
ልቀበል ስሻ እኔ ላደርገው የሚገባኝ ነገር መኖሩን ገለጸልኝ:: ራማ
ከአይኔ ከተሰወረ ቆይቷል:: «ቲ» እንዳለኝ ከእኔ የሚፈለገውን
ፈጽሜ ማግኘት የምሻውን መቀበል አለብኝ:: ቤተሰቦቼን ለመርዳት
ገንዘብ ማግኘት:: ገንዘብ ለማግኘት ደግሞ አድርግ የምባለውን
ያለማንገራገር መፈጸም ይኖርብኛል:: ለአስተማሪዬ ማንኛውንም
የተፈለገውን ልፈጽም ዝግጁ ነኝ አልኩት:: ከዚህ ውጭ ሌላ ምርጫ
የለኝም:: ከዚህ በኋላ ባፈገፍግ የሚከተለኝ ምን እንደሆነ ተገንዝቤ
ዋለሁ:: እርሱም ደስ ብሎት የሚያስፈልገኝን ለመቀበል አሁን ዝግጁ
እንደሆንኩ አሳውቆኝ የመጀመሪያውና ዋናው ተግባሬን ለመፈጸም
ምሽቱን እንድጠብቅ አዘዘኝ::

በትልቁ ቪላ የተሰበሰቡት ሰዎች የሚያወሩት ቋንቋ ለእኔ
እንግዳ ነው:: ሁሉም የውጭ አገር ሰዎች ናቸው:: በእርጋታ ወደ
ሌላኛው አዳራሽ እንድንገባ ተደረገ:: በመናፍስት የተሞላ የሚመ
ስል አዳራሽ ውስጥ ስንገባ ፍርሀት ፍርሀት አለኝ:: ሁላችንም ለቀቅ





ያለ ቡናማ የአምልኮ ልብስ ለብሰናል:: አስተማሪዬ አሰቀድሞ
አስተምሮኝ የነበረውን ዜማ እያዜምን ነበር የገባነው:: የአዳራሹ
በር ተዘግቷል:: ከመድረኩ በስተቀር ሌላው በጽልመት ተወርሷል::
ከአለባበሱና ሁኔታው የቡድኑ መሪ እንደሆነ የሚያስገነዝብ አንድ
ሰው ትልቅና ጥቁር ቦርሳ ይዞ በመድረኩ ላይ ወጣ:: በመድረኩ
ላይ በነበረው ጠረጴዛ ላይ ያስቀመጠውን ቦርሳ ሲከፍተው አፉ
የታሸገ ለጋ የሆነ ወጣት በሙሉ ሰውነቱ ተጋድሞ አየሁ:: ወዲያው
በአዳራሹ ያሉ ሁሉ ድምጻቸውን ከፍ አድረገው በማላውቀው ቋንቋ
ያዜሙ ይጮሁ ጀመር:: ሁሉም ቢላዋ የያዘ እጃቸውን ወደ ላይ
አንስተዋል:: የመድረኩ መሪ ካህን ካራውን ወደ ላይ አንስቶ ዝብ
ርቅርቅ ያለ ነገር ከተናገረ በኋላ በጠረጴዛው ላይ ያጋደመውን
የወጣቱን አንገት ደግሞ ደጋግሞ ወጋው:: መላ ሰውነቴን ነዘረኝ::
ሊያስመልሰኝም ፈለገ:: ሰውነቴ በድን ሆነብኝ «በዚህ ምሽት በመ
ካከላችን አንድ አዲስ አባል መኖሩ ይታወቀኛል:: ወደ መድረኩ
ይምጣና የዓለምን ኃይል ይቀበል» ሲል መሪው ካህን ተናገረ::
ይህን ጊዜ ሰውነቴ በላብ ተጠመቀ:: ሰውነቴ ተንዘፈዘፈ እግሬ
ሊከዳኝ ደረሰ:: እንደምንም ራሴን ተቆጣጥሬ ወደፊት ሔድኩ::
«ልቡን ንካና ሊኖርባት ያልተገባትን ምድር ለቆ ሲሔድ የሚኖረ
ውን ኃይል ተገንዘብ» አለኝ:: የሚንቀጠቀጠውን እጄን በወጣቱ
ደረት ላይ አኖርኩት:: ሰውነቱ አሁንም ይሞቃል:: ካህኑ እጁን
በላዬ ላይ ጭኖ ከሟቹ ሰውነት ጋር አጣብቆ በጣም ተጫነኝ::
የዚህን ጊዜ እንግዳ ስሜት ተሰማኝ መላ ሰውነቴ የኤሌትሪክ
ዓይነት ነዝረት ተሰማው:: በዚህ ቅጽበት ሊደረግልኝ የምሻውን
ነገር እንድለምን ካህኑ አዘዘኝ:: ፍላጎቴ የታወቀ ነው ገንዘብ በጣም
ብዙ ገንዘብ::

በአዳራሹ ያሉት ሁሉ በአንድነት ድንገት ሲጮኹ እንግዳ
በሆነ ኃይል ተሞላሁ:: በአዲስና ለእኔም ባልገባኝ ቋንቋ ተናገርኩ::
በዙሪያው ያሉት ሁሉ በጩኸትና በጭብጨባ አጀቡኝ:: «ያለ ብዙ
ውጣ ውረድ በሚገባ ተቀብለሃል... አሁን ከእኛ እንደ አንዱ
ሆነሃል... ዋጋህ ከመድረኩ ጀርባ ይጠበቅሃል» ብሎ አሰናበተኝ::
ሌሎች ተሳታፊዎችን የመባረኩን ሥራም ቀጠለ::

በመድረኩ ጀርባ ብዙ ክፍሎች ነበሩ:: ቁጥር ዘጠኝ የሚለው
ውስጥ ገባሁ:: ቀይ አንሶላ የለበሰ አልጋ በውስጡ አለ:: የክፍሉ



www.ethiopianorthodox.org

መብራት ቀይና ደብዛዛ ነው:: ሕሊናዬ ገና አልተረጋጋም:: ባደረ ግሁት ተግባር የእፍረት ስሜት ይሰማኛል:: ግን ደግሞ ይህን ማድረጌን ማንም አያውቅም:: ስለዚህ ባለጸጋ ሆኜ ወደኬንያ እመለሳለሁ:: የቤተሰቤም ኑሮ በአጭሩ ይለወጣል እያልኩ ራሴን በማጽናናት አልጋው ላይ ጋደም ከማለቴ ሁለት ውብ ሴቶች ከወደበሩ መጡ:: አንደኛዋ የወይን ጠጅ መጠጫ ብርጭቆ ቀይ የወይን ጠጅ የመሰለ መጠጥ ይዛለች:: ሌላኛዋ ደግሞ በማሰሮ የተሞላ ዘይት:: ከተጋደምሁበት ለመነሳት ስሞክር የእኔ መነሳት አስፈላጊ እንዳልሆነ ጻሩ ግን ራሴን ዘና አድርጌ እንድሰጣቸው ጠየቁኝ:: ወይን የመሰለውን መጠጥ የያዘችው ጠጋ ብላ አጠጣችኝ:: አንድ እንደተጎነጨሁ ኃይለኛ ስሜት በሠራአካላቴ ተሠራጨ:: ነፃ የመሆን ስሜት ተሰማኝ:: ስለቤተሰቤ ስጨነቅ የነበርሁት ሰው ከዚህ ቅጽበት በኋላ ለቤተሰቤ ግዴለሽ ሆንኩ:: ሁለተኛዋ በማሰሮ የያዘችውን ዘይት ይዛ በመቅረብ ሰውነቴን በዘይቱ ታሻሸው ጀመር /ማሳጅ/ ልቆጣጠረው የማልችለው የዝሙት ስሜት ተቀሰቀሰብኝ በዚያ ቅጽበት በእነርሱ ቁጥጥር ስር ዋልኩ:: ከዚህ ሰዓት ጀምሮ እነርሱን ከምንም ነገር በላይ እንደምሻቸው ነገሩኝ:: ከዚህ በፊት ተሰምቶኝ የማያውቅ ሰይጣናዊ የሆነ ዝሙታዋ ተግባር ፈጽም ፈጽም ያሰኘኝ ጀመር:: ብዙ ሴቶችን በዝሙት ማወቅ፣ የሥጋ ዘመዶቼን በዝሙታዊ ተግባር የመሻት፣ በሕፃናት ላይ የወሲብ ተግባር የመፈጸም ፍላጎት፤ ከፉኛ በሆነ የዝሙት ስሜት ተከበብሁ::

ሴቶቹ ለዘላለሙ ለእኔ ከአምላክ የተሰጡኝ ገጸ በረከቶች መሆናቸውን እንዲሁም በማንኛውም ጊዜ ማንኛዋንም ሴት በአልጋ ላይ ጥዬ ቀድሞ የተማርኩትን ዜማ በማዜምበት ጊዜ እነርሱ ከእኔ ጋር እንደሚሆኑም ነገሩኝ::

ልቅ የሆነ ዝሙታዊ ተግባር ከመፈጸም ባሻገር ልቤ በፍቅረ ንዋይ እንዲነድም ተደርጓል:: ገንዘብ የሚያስገኝ ከሆነ ማንኛውንም ተግባር ያለ ይሉኝታና ያለ ርህራሄ መፈጸም እንዳለብኝ መመሪያ ተሰጥቶኛል:: በአጠቃላይ ሰይጣናዊ ተግባርን የመፈጸምና የመክበር ተልእኮ ይዤ ወደ ናይሮቢ ተመለስኩ:: ከጆሞ ኬኒያታ አየር ማረፊያ በቀጥታ ያመራሁት ወደ አሊ ቤት ነበር:: «እንኳን ደህና ተመለስህ» በማለት አሊ ሞቀ ባለ ሰላምታ ተቀበለኝ:: «ቤተሰቦቼ ስለሌሉ ዛሬ ምሽቱን ከእኔ ጋር ስለጉዞህ ስታጫውተኝ ታመሻለህ» አለኝ:: ባየሁትና በሰማሁት ነገር አሊ ብዙም አልተገረመም::





በቤተሰቦቼና በጓደኞቼ ፊት ራሴን እንድሰውር ምንም ነገር ለእነርሱ እንዳልተነፍስ አስጠነቀቀኝ:: የተለያዩ የንግድ ሥራዎች ንም አስተማረኝ::

በዚያ ምሽት ከአሊ ጋር ዓለምአቀፋዊ ወደ ሆነ የቁማር ቦታ ሔድን:: በአንድ ምሽት ከሦስት መቶ ሺ በላይ እንዴት እን ደሚሠራ ተማርኩ:: ዳግመኛ ድሀ እንደማልሆን አወቀሁ:: በኮይናንግ መንገድ ስናልፍ አንዲት የ15 ዓመት ልጃገረድ አሳፈርን በእጄ ይዤ የነበረውን የቆርቆሮ ቢራ ሰጠኋት:: ትንሽ እንደተጎነጨች ራስዋን ሳተች:: ወደ መሰዊያው ስፍራ ወሰድናት:: በዚህ ቀን የመበለቱን ሥራ ያከናወንኩት እኔ ነበርኩ:: እንደተለመደው በተ ለያየ አኳኋን አሸጌ በተለመደው መልኩ ለሚመለከታቸው አድርሼ ወደ አዲሱ አፓርትመንቴ ተመለስኩ::

በዚያ ዓመትና በ1997 በአብዛኛው እኔና አሊ በእጽ ማዘዋ ወር ሥራ የተጠመድንበት ወቅት ሲሆን የምንሰዋቸውን ሰዎች እየበለትን አሽገን መላካችንንም አላቋረጥንም ግን በአግባቡ ታሽጎ በመርከብ ተጭኖ ወዴት እንደሚሔድ አላውቅም:: ወዴትና ለምን ዓላማ ተጭኖ እንደሚወሰድ አግባባዊ በሆነው ቀን እንደሚገልጽልኝ ተነግሮኛል::

ለመስዋዕት የማቀርባቸው እንስቶችን መጀመሪያ ሞራላዊ ባልሆነ መልኩ እደፍራቸዋለሁ:: በተለይ ስድስት ዓመት ገደማ የሚሆናቸውን ሕፃናት በግንኙነት ወቅት ራሳቸውን ስለሚስቱ እነርሱን ለመሰዋት የማደንዘዣ መርፌ አልጠቀምም ነበር:: አሊን ሳላማክር በሩዋንዳ በገዛሁት ቤት ከመሬት በታች ባሠራሁት የመሰዊያ ቦታ ብዙዎችን ሰውቻለሁ:: ከቤተሰቤ ፍጹም ርቄያለሁ:: ሜሪያም ከእኔ ጋር ሆነን ሳለ በተፈጠረ አደጋ ሕይወቷን አጥታለች:: በመካከላችን አለመግባባት ተፈጥሮ ስለነበር ቤተሰቦችዋ ለሕይወትዋ ማለፍ ተጠያቂ ሊያደርጉኝ ሞክረው ነበር:: ቤተሰቦቼ ገንዘብ ሲቸግራቸው ቢሮዬ መጥተው ገንዘብ ከመውሰድ ውጪ ከእኔ ጋር ፍጹም ተራርቀናል::

አሁን የተለያዩ መኪናዎች ባለቤት ሆኛለሁ:: ሰማያዊ መርሴዲስ፣ ጥቁር አረንጓዴ ጃጓር፣ ፓጃሮና፣ ጥቁር ቶዮታ:: በተ ለይ ጥቁሯን ቶዮታ መኪናዬን አዘወትራት ነበር:: ምንም በሀብት ብከብርም ውስጤ ግን ሰላም አልነበረውም:: በየመንገዱ ዳር ቆመው



www.ethiopianorthodox.org

ፈለግሀቸው በስተቀር እንስሳትን አትግደል» የሚለው ከሕጋቸው
አንዱ ቢሆንም «አስማትና መተት መፈጸምም» ሌላው የሕይወታ
ቸው መመሪያ ነው:: ለአስማትና ለመተት ተገባር ደግሞ እንስሳ
ትን መስዋዕት አድርጎ ማቀረብ የተለመደ ነው::

ሰይጣኒዝም «ሁሉንም መውደድ» የሚለውን የክርስትናን
መሠረታዊ ትምህርት በሚጻረር መልኩ «ልትወዳቸው የሚገቡህን
ብቻ እንጂ ሁሉንም መውደድ የለብህም:: ይህ ራስን መጉዳትና
አላስፈላጊ ነው» የሚል አስተምህሮን ይከተላል:: በዚህ ትምህርታ
ቸው መሠረት ፍቅር ከጥቅም ጋር ብቻ እንዲሆን ያዛሉ:: ሰይጣ
ኒዝም በምዕራቡ ዓለም በርካታ አባላትን እያሰባሰበ ሲሆን አባላቱ
ከየት ከየት እንደመጡ ለማወቅ በተደረገው ጥናት መሠረት
ከአባላቱ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ማለትም 55 በመቶው
ከፕሮቴስታንት እንደሆኑ ተረጋግጧል:: የተቀሩት ደግሞ 20
በመቶው ከካቶሊክ 10 በመቶው ከአይሁድ፣ አንድ በመቶ የሚሆ
ኑት እምነት የለሾች ሲሆኑ የተቀሩት ከምን እንደመጡ ለመናገር
ፈቃደኛ ያልሆኑ ናቸው::





# ማጠቃለያ

ካለፉት ምዕራፎች እንደተገነዘብነው ዲያብሎስ ግዛቱን በዓለም ላይ እያስፋፋ፤ ዙፋኑንም በሰዎች ልቦና ላይ እየዘረጋ፤ መንፈሱንም በዓለም ላይ እያሰፈነ ነው:: በፍጻሜ ዘመን ደግሞ ይህ እንደሚሆን አቡቀለምሲስ የተባለው ዮሐንስ በራእዩ ላይ እንዲህ ሲል ገልጦታል «ሺውም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል:: በአራቱም በምድር ማዕዘን ያሉትን አሕዛብ ጎግንና ማጎግን እንዲያስታቸው ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል:: ቁጥራቸውም እንደ ባሕር አሸዋ የሚያህል ነው»[1]

ይህ ዘመን ያለምንም ጥርጥር ሰይጣን ከእስራቱ ተፈቶ የተለቀቀበት ጊዜ ነው:: ለዚህም ምስክሩ በዓለም ላይ ሰፍኖ ያለው ሰይጣናዊ ተግባር ነው:: በዚህ ዘመን ላለን እውነተኛ ክርስቲያኖች ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ያሳስበናል «የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ:: መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና:: ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ:: ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ:: እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ የጽድቅንም ጥሩር ለበሳችሁ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነት ጋሻ አንሡ፤ የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው»[2]

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል::

1. ራእይ ፳፥፯
2. ኤፌ. ፮፥፲፩-፲፯

www.ethiopianorthodox.org

